| | |
|---|---|
| ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ<br>ኢየሱስ ክርስቶስ<br>ካህኑ ለዓለም፡ በከመ ሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊ<br>ንጉሠ ጽዮን፥ ወንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ | ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር<br>ድንግል ማርያም<br>እሙ ለአምላክነ፥ ወእምነ ዘዚአነ<br>ንግሥተ ጽዮን፥ ወንግሥተ ነገሥታት ዘኢትዮጵያ |
| **The Triumphant Lion of the Tribe of Judah**<br>**Jesus Christ**<br>**Eternal Priest in the Order of Melche-Zedeq the Ethiopian**<br>**King of Zion and King of Kings of Ethiopia** | **Ethiopia stretches out Her Hands to God**<br>**The Virgin Mary**<br>**Mother of God and Our Holy Mother**<br>**Queen of Zion and Ethiopia** |

ቍጥር ፲/፳፻፰ ዓ. ም.

# ቃለ ዐዋድ!

## እምኢትዮጵያ፡ ዘመንግሥተ እግዚአብሔር።

# የዐዋጅ ቃል!

## ከኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት።

በስመ እግዚአብሔር አብ፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ፤
አሓዱ አምላክ፤ በቅድስት ሥላሴ፤

በስመ እግዝእትነ፥ ወእምነ፥ ወሃይማኖትነ፥ ወሀገሪትነ፥
ወንግሥትነ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ፤

በኃይለ መስቀሉ፡ ዘእግዚእነ፥ ወአቡነ፥ ወመድኃኒነ፥
ወካህንነ፥ ወንጉሥነ ኢየሱስ ክርስቶስ፡
ወልደ-እግዚአብሔር ሕያው፥ ወወልደ ማርያም ሥግው።

ማለትም፡-

በልዩ ሦስትነት፡ አንድ አምላክ በኾነው፡
በእግዚአብሔር አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ ስም፤

እናታችንና ሃይማኖታችን፥ አገራችንና ንግሥታችን
በኾነችው፡ አምላክን በወለደችው፡
በእመቤታችን፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ስም፤

በአምላክነቱ እና በሰውነቱ፡ የእግዚአብሔር አብ እና
የእግዚአብሔር እም፡ ድንግል ማርያም ልጅ በኾነው፡
አባታችንና መድኃኒታችን፥ ካህናችንና ንጉሣችን
ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በመስቀሉ ኃይል።

\+ + +

## ይድረስ፡-

በጌታዬ በፍቅሬ በእግዚአብሔር አብ፥
በልጄ በወዳጄ፡ በእግዚአብሔር ወልድ፥
በሕይወቴ በመድኃኒቴ፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡
የኹለንተና ልጆቼ ለኾናችሁት፡
በኢትዮጵያ ላላችሁትና በመላው ዓለም ለተበተናችሁት፥
በልዩ ልዩ ተግባርና ሙያም ለምታገለግሉ፥
በተለያየ የኑሮ ኹኔታና የሥራ መስክ ለምትገኙ፥
ይልቁንም፡ "የእግዚአብሔር ልጆች" ከሚለው፡
የመጀመሪያ መታወቂያችሁ ጋር፡ "የኢትዮጵያ ልጆች" የሚለውን
የመጨረሻ ስም በመቀዳጀት፡
በስሜ፡ ተጠርታችሁ፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ ርስት ጉልቴ ለኾናችሁት፥
በአጠቃላይ፡ እንደኢትዮጵያ ሥርዓተ-መንግሥት፡
የቤተ-ሕዝቡ፥ የቤተ-ክህነቱና የቤተ-ምልክናው አባሎች ለኾናችሁት፡
ኪዳናውያን ኢትዮጵያውያን እና ኪዳናውያት ኢትዮጵያውያት ልጆቼ!

ይልቁንም፡ በአኹኑ ጊዜ፡ በዓለም ላይ እየተካኼደ ያለውን፡
አስደንጋጭና አስፈሪ ኹኔታ በሚመለከት፡
የሚሰማ መንፈሳዊ ጆሮና የሚያይ መንፈሳዊ ዓይን ላላችሁ፡
በምድር ላይ ለምትኖሩ፡ ለመላው የዓለሙ የሰው ወገኖች ኹሉ፥
ለወንዶቹም፡ ለሴቶቹም፥ ለአዛውንቱም፥ ለወጣቶቹም፥
በየግላችሁም፥ ለኹላችሁም!

በአንድ አምላካዊ ፈጣሪነቱ፥ በሥላሴነት መለኮታዊ ቸርነቱም፡ ሙሽራውና እናቱ፥ መቅደሱም ባደረገኝ፡ በልዑል እግዚአብሔር ስም፡ ዘለዓለማዊው፡ የእናትነት ጸጋዬ: ፍቅሬና ሰላሜ፥ በረከቴና ረድኤቴ፡ በያላችሁበት ይድረሳችሁ!

እንዳለፈው፡ እንደ፱ነኛው የአዋጅ ቃሌ፡ ዛሬም፡ በዚህ **መለኮታዊ ምዕዳኔ***፡ የምናገራችሁና የማናግራችሁ፡ እግዚአብሔር እናታችሁና ሃይማኖታችሁ፥ አገራችሁና ንግሥታችሁ፥ ክህነታችሁና መቅደሳችሁ፥ እመ-ቤታችሁና ምድረ-ርስታችሁ የኾንሁት፡ እኔው፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ድንግል ማርያም ነኝ።**

## መቅድም።

"አፍሪቃና እስያ፥ አውሮጳና አሜሪካ፥ አውስትራልያና ደሴታት" በተባሉት፡ በምሥራቁ ኾነ፡ በምዕራቡ፥ በሰሜኑ ኾነ፡ በደቡቡ የክፍላተ ዓለም አህጉራት ላይ፡ የተፈጥሮ ቊጣዎች በኾኑት፡ በፀሓይ ትኲሳትና በሰደድ እሳት በዐውሎ ነፋሳትና በከባድ ዝናማት፥ በውኃ ሙላቶች ማጥለቅለቅና በበረዶ ውሽንፍር፥ በመሬት መደርመስና መንቀጥቀጥ፥ በድርቀትና በቸነፈርም አስፈሪ ማዕበላትና ደምሳሽ ኃይላት ምክንያት፡ ታላቅ መቅሠፍታዊ ጥፋት፡ ይኸው እየወረደ ይገኛል።

ደግሞም፡ በምድር ላይ ለዝንተ ዓለም ጸንቶ፡ በሰብኣውያን ፍጡሮቻችን መካከል፡ ታላላቅ ፍጅትንና ዕልቂትን፥ ደም መፋሰስንና ሥቃይን፥ የኅብረተሰብ ነውጥንና ስደትን፡ ሲያስከትል የኖረው የእርስ በርስ ጦርነት፡ ባለፉት ወራትና በቅርቡ፥ ሰሞኑንና አኹንም፡ "ሳን ቤርናርንዲኖ" በምትባል፡ በአሜሪካዋ ዩናይትድ ስቴትስ፡ የካሊፎርንያ መንደርና በኤውሮጳ፡ የፈረንሳይ መናገሻ ከተማ በኾነችው፡ በፓሪስ፥ በሌሎችም፡ የመካከለኛው ምሥራቅ ከተሞች፥ እንዲሁም፡ በበረራ ላይ በነበሩ፡ በኹለት የመስኮብ የመንገደኞችና የጦር ጥያራዎች ላይ በተፈጸመው "የአጥፍቶ-ጠፊ ሽብርተኞች" ፍንዳታና ግድያዎች ምክንያት፤ በተባባሰና በተስፋፋ፥ በአስከፊና በአሠቃቂ ኹኔታ፡ ይኸው፡ ዛሬም እየታየና እየተሰማ፥ እየተደረገና እየኾነም ነው።

ከዚህ የተነሣ፡ በመላው ዓለም፡ እጅግ በባሰ መጠን፡ እየተሰማ የቀጠለው፡ የሰዎች የልቅሶና የዋይታ ድምፅ፥ እየተቀጣጠለ ካለው፡ የድንጋጤና የፍርሃት፥ የኃዘንና የትካዜ፥ የሥጋትና የጭንቀት ነበልባል ጋር ተቀላቅሎ፡ እነሆ፡ ጽዋው ስለሞላና ሞልቶም፡ በመፈሰስ ላይ ስለሚገኝ፡ በምድር ላይ የሚኖረው፡ የሰው ዘር የህልውና ፍጻሜ፡ ከመጨረሻው አሳሳቢ ደረጃ እንደደረሰ፡ ለመገንዘብ፡ አሳማኝ ምልክቱ፡ በገሃድ ይታያል።

በዚህ ረገድ፡ **ከኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት**፡ እስካኹን፡ በልዩ ልዩ መልክና ይዘት ሲተላለፍ የቆየውን **መልእክት**፡ "**መለኮታዊ ምዕዳን**" በሚል ርእስ፡ ዛሬ እንደገና፡ በእኔ የዐዋጅ ቃል፡ እንዲህ፡ ይፋ ማውጣቱ የሚያስፈልግ ኾኖ ተገኘ።

---

*__ምዕዳን__ = *ተግሣፅና ማስጠንቀቂያ የተመላበት ትምህርታዊ ምክር ነው።*

## ይህ መለኮታዊ ምዕዳን፡ ለማን የቀረበ ነው?
## የሚያስገኘውስ ፍሬ ምን ዓይነት ነው?

ይህን **መለኮታዊ ምዕዳን፡** እንዲህ፡ በእኔ የዐዋጅ ቃል፡ እንደገና ማስተላለፍ የሚያስፈልግ ኾኖ የተገኘው፡ እንዲያው፡ በከንቱ አይደለም፤ ብርቱና እጅግ አሳሳቢ በኾነ ምክንያት እንጂ። ከዚህ በፊት፡ በአንዳንድ አጋጣሚ ምክንያቶች መነሻነት፡ ይህን የመሰሉ ምክሮችና ማስጠንቀቂያዎች፡ የተላለፉ ቢኾኑም፡ ይህንኛውን መለኮታዊ ምዕዳን፡ ከእነዚያ ኹሉ የተለየ ያደረገው መሠረት፡ ይኸው መለኮታዊ ምዕዳን፡ በአኹኑ ጊዜ የቀረበው፡ በዐዋጁ አርእስት እንደሚነበበው፡ የየአገሮቹን ሰብአውያን መንግሥታት በማካተት ሳይኾን፡ በቀጥታ፡ በመላው ዓለም ወደሚኖረው፡ ወደእያንዳንዱ ወንድ፥ ወደእያንዳንዷም ሴት ግለሰብ ብቻ ያተኮረ በመኾኑ ነው።

እንግዴህ፡ በመላው ዓለም ለምትገኙ፡ ለእያንዳንዳችሁ ወንድና ሴት ግለሰቦች ፍጡሮቻችን፡ የምላችሁን ስሙኝ!

በሕይወተ-ነፍስ ዕውቀታችሁ፥ በሕይወተ-ሥጋ ህልውናችሁና በሕይወተ-መንፈስ ብቅዓታችሁ፡ ይኸው፡ እየኖራችሁበትና በእውን እየተመለከታችሁት ያለውን፥ እየራሳችሁን የሚጨምረውን፡ ይህን፡ የሚታየውንና የማይታየውን፥ ረቂቁንና ግዙፉን፥ ሥጋዊዉንና መንፈሳዊዉን፥ ሰማያዊዉንና ምድራዊዉን፥ የሚንቀሳቀሰውንና የማይንቀሳቀሰውን ፍጥረታተ-ዓለማትን ኹሉ የፈጠረ፥ እናንተ እያንዳንዳችሁም፡ በየቋንቋችሁ፡ ስም ሰጥታችሁት የምታመልኩት፥ ነገር ግን፡ ከጥንቶቹ እስከዛሬዎቹ ድረስ፡ ታማኞች ልጆቻችን በኾኑት፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ዘንድ፡ "እግዚአብሔር" ተብሎ የሚጠራው፡ አንድ አምላክ መኖሩን፡ ለእየራሳችሁ፡ በእውነት የሚያረጋግጥላችሁ እምነት ካላችሁ፥ ወይም፡ በዚህ እምነት፡ በልዩ ልዩ ምክንያት፡ እስካኹን ሳታምኑ ቆይታችሁ፡ አኹን ግን፡ ልታምኑበት የምትሹ ካላችሁ፡ ለእናንተ፡ ለኹላችሁም፡ ይህን እላለሁ፡-

ከኹሉ አስቀድሞ፡ የምንነቱን ዝርዝር፡ ወደፊት በምታገኙት፡ በመለኮታዊው የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖት አጽድቃችሁ የምታጸኑትን፡ ይህን፡ አኹን የሰማችሁትን እምነታችሁን፡ በውስጣችሁ፡ ፍጹምና እውን አድርጉት! በምግባርም፡ በገሃድ፡ በሥራ፡ የምትገልጡት ይኹን።

ቀጥሎ፡ የየግል ሰውነታችሁን፡ በማወቅ ኾነ፡ ባለማውቅ፥ በፈቃዳችሁም ኾነ፡ ያለፈቃዳችሁ፡ በሰብአዊው ሕጋችሁ መሠረት፡ በነፍስ፥ በሥጋና በመንፈስ፡ ጽኑ አማኞቹ፥ ሙሉ ዜጎቹና ፍጹም ታዛዦቹ አድርጋችሁና አሳልፋችሁ ከሰጣችሁት፡ ከእየአገሮቻችሁ፡ ሰብአዊ መንግሥት፡ የእምነት፥ የተገዢነትና የባርነት ቀንበር፡ እየራሳችሁን፡ አኹንም እንደገና፡ በገዛ ፈቃዳችሁና ምርጫችሁ፡ ከላይ በገለጣችሁትና ባረጋገጣችሁት ሃይማኖታችሁ አማካይነት፡ በእግዚአብሔር እውነትና መንፈስ፡ ፈጽማችሁ፡ ነጻ አውጡ።

በመጨረሻ፡ እንዲህ አድርጋችሁ፡ ከእነዚሁ፡ ከእየአገሮቻችሁ፡ ሰብኣውያን የዓለም መንግሥታት፡ የዜግነትና የተገዢነት ቀንበር፡ በነፍስ፥ በሥጋና በመንፈስ፡ ነጻ ያወጣችሁትን፡ የኹለንተና ሰውነታችሁን፡ አኹንም እንደገና፡ በገዛ ፈቃዳችሁና ምርጫችሁ፡ በእግዚአብሔር እውነትና በመንፈስ ቅዱስ አምልኳችሁ አማካይነት፡ ለእኛ፡ ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ መልሳችሁ ታስረክቡናላችሁ።

በዚህ ጊዜ፡ የሚኾነውን ትንግርታዊ ተአምር ገልጬ ላሳውቃችሁ! ይኸውም፡ እንዲህ ነው:-

-በመልካችን ፈጥረን፥ "ከእኛ፡ እንደአንዳችን ኾናችሁም!" ብለን፡ በነፍስ፥ በሥጋና በመንፈስ የተዋሕዶ አካላትና ባሕርያት፡ በእግዚአብሔራዊው ሕይወት፡ ለዘለዓለም እንድትኖሩበት፡ ለእያንዳንዳችሁ፡ በእየግል ሰጥተናችሁ የነበረውን፥ እናንተ ግን፡ በሰይጣናዊው ህልውና፡ ሲማቅቅበት ቆይቶ፡ በመጨረሻ እንዲጠፋበት፡ ለፍጡር የክፋት ባርነት፥ ለሓሰት [ለኃጢኣት] ግዞተኝነትና ለሞት ፍዳ ዳርጋችሁት የነበረውን፡ ያን ሰውነታችሁን፡ አኹን፡ ከዚያ ይልቅ፡ ወደመልካሙ ወደእኛ የፈጣሪ ነጻነት፥ ወደጽድቁ [ወደእውነቱ] ሕይወትና ወደዘለዓለማዊው የትንሣኤ ተድላ ደስታ በመመለሳችሁ፡ እንግዴህ ወዲህ፡ ለአንዴና ለመቼውም ጊዜ፡ ለእኛ ብቻ ተለይታችሁ፡ በኢትዮጵያ፤ የእግዚአብሔር መንግሥታችን ውስጥ የምትኖሩ ቅዱሳንና ቅዱሳት ልጆቻችን፥ ነጋሢዎቻችንና ካህናቶቻችን [አገልጋዮቻችን] መኾናችሁን ትገነዘባላችሁ።

-ከዚህ የተነሣ፡ እንዲያ፡ በገዛ ፈቃዳችሁና ምርጫችሁ፡ በእየግላችሁ፡ አጥታችሁት የነበረውን፡ ያን፡ የእኛ የእግዚአብሔር ልጅ የመኾንን ክብር፥ ለመንግሥታችን ወራሽነት የሚያበቃውን፡ የነጋሢነት ሥልጣንና የመለኮታዊው ክህነት ባለሟልነትን መብት፡ ለእየራሳችሁ፡ መልሳችሁ ትቀዳጃላችሁ። እያንዳንዳችሁ፡ እየራሳችሁን፡ **መልከ ጼዴቅን** ኾኖ ታገኙታላችሁ።

-በዚህ ጊዜ፡ በመላው የሰማይና የምድር ፍጥረታተ ዓለማት ላይ የሰፈነችው፡ **የኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን**፡ ሙሉ ዜጎች ብቻ ሳትኾኑ፡ በእግዚአብሔራዊው ልጅነታችሁ፥ ነጋሢነታችሁና ካህንነታችሁ ምክንያት፡ የባለቤትነት መብትንና ሥልጣንንም ትቀዳጃላችሁ።

-ከዚህ በኋላ፡ ሰዎች፡ "አገር" እያሉ የፈጠሩት ወሰን፥ የሠሩትም ድንበር ሳይከልላችሁ፡ ዓለሙ ኹሉ፥ ምድሪቱም በመላ፡ አህጉራት ጭምር፡ የእየራሳችሁ እንደኾኑ ዐውቃችሁ፥ ሕዝቦችንም ኹሉ፡ ነጭ፥ ቀይ፥ ጥቁር፥ ወይም፡ ካማዊ፥ ሴማዊ፥ ያፌታዊ፥ ወይም፡ አረማዊ፥ ይሁዲ፥ ክርስቲያን፥ እስላም ሳትሉ፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችሁ፡ ኹሉን፥ እያንዳንዱንም፡ በነፍስ ወከፍ፡ "ወንድሜ! እኅቴ!" ብላችሁ፡ እንደየፍላጎታችሁ እየተዘዋወራችሁ፡ በመዝናናት የምትኖሩባቸው ይኾናሉ።

-እንግዴህ ወዲህ፡ የእናንተ የኾነችው፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ፍጥረታትን ኹሉ፥ የሰዎችን መንግሥታት ጭምር፡ አጠቃልላ የያዘችና የምትመራ፥ የምታስተዳድርና የምትጠብቅ መኾኗን አበክራችሁ ስለምታውቁ፡ የሰዎች መንግሥታትም፡ አስፈላጊውንና ተገቢውን በጎ አገልግሎት፡ ለእናንተ እንዲያበረክቱ፡ ዓመፀኞችንም እየተቆጣጠሩ እንዲገዙ፡ በእኛ ዘንድ ተፈቅዶላቸው፡ በእየራሳቸውና ለእየራሳቸው የተቋቋሙና የሚሠሩ ከመኾናቸው በቀር፡ በእናንተ ላይ፡ አንዳችም ሥልጣን እንደሌላቸው ተረድታችሁ፡ መልካሙን፡ የኢትዮጵያዊነት ኪዳናዊ ሕይወታችሁን፡ በሰላምና በደስታ የምትኖሩ ትኾናላችሁ። (ሮሜ. ፲፫፥ ፩-፯።)

-እነዚሁ፡ የእየአገሮቻችሁ፡ ሰብአውያን የዓለም መንግሥታት፡ ምንጊዜም፡ በእኛዪቱ፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ መለኮታዊ የአባትነትና የእናትነት ጥበቃና ቍጥጥር ሥር ያሉ በመኾናቸው፡ እንዲህ፡ በእናንተ፡ በእያንዳንዳችሁ መቀደስ ምክንያት፡ እነርሱ ሰብአውያኑ መንግሥቶቻችሁ ጭምር፡ የተቀደሱ ይኾናሉ። ይህም፡ "የእናንተ፡ ለዚህ ቅድስና መብቃት፡ ለእነዚሁ ለሰብአውያኑ መንግሥቶቻችሁ ሳይቀር ይበጃቸዋል!" ማለት ነው።

-የዚህ የመበጀት እውነታ፡ መሠረታዊ ምክንያቱ፡ ምን ይመስላችኋል? ምክንያቱማ፡ ይኼውላችሁ! በማስተዋል፡ ከቃሌ ስሙት!

-እናንተ ልጆቻችን፡ ከእኛ፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ያገኛችሁት፥ በተፈጥሮም፡ በእየልባችሁ ጽላት ላይ የተጻፈው፥ ከዚህም ጋር፡ በመለኮታዊው እምነትና ምግባር ተመሥርታ፡ በቅዱሱ ኪዳን በተገለጸችው፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን ዘንድ፡ "ሥርዓተ-መንግሥት" የኾነው፡ የህልውናችሁ መመሪያ፡ በእነርሱ፡ በሰብአውያኑ መንግሥቶች ዘንድ፡ በየቋንቋቸው፡ በክርታስ ላይ ጽፈውና ዐትመው፥ "ሕገ-መንግሥት" ብለው ሰይመውም፡ የአገዛዝ ፈሊጣቸውን የሚመሩበት የሰውኛ ሰነዳቸው መኾኑን ዐውቃችኋል።

-እነዚሁ ሰብአውያኑ መንግሥቶች፡ "ሕገ-መንግሥት" ብለው፡ ያለማቋረጥና በየጊዜው፡ የተለያዩ ሕጎችን እያመነጨበት፡ ከሚሠቃዩበት፥ እርስ በርሳቸውም ከሚጋደሉበት፡ የአገዛዝ ፈሊጣቸው ይልቅ፡ መለኮታዊና ተፈጥሮአዊ የኾነው፥ ለእናንተም፡ የህልውናችሁና የሕይወታችሁ መመሪያ አድርጋችሁ የምትኖሩበት፡ ይህ፡ የእኛ "ሥርዓተ-መንግሥት"፡ በሉዓላዊነቱና በፍጹምነቱ፡ እጅግ የበለጠና የተሻለ፥ ኹሉን ያካተተና የተሟላ፥ በዚህ ማንነቱና ምንነቱም፡ እውነተኞች ሰብአውያንና መንፈሳውያን ፍጡራን ኹሉ፡ በእምነትና በገሃድ የተቀበሉት መኾኑን፡ ኹሉም ሊገነዘበው ይገባል።

-ስለዚህ፡ አነስተኛና ዝቅተኛ፥ ሥጋዊና ምድራዊ፥ ውሱንና ሙሱን የኾነውን፡ ሰብአዊዉን ሕግ ለመፈጸም፡ እየራሳችሁ፡ እግዚአብሔራዊው ሕግ ለኾናችሁት፡ ለእናንተ፡ በምንም መልኩና ይዘቱ እንደማይሳናችሁ፡ ለማንም ግልጽ ነው።

-ከዚህ የተነሣ፡ በእነርሱ፡ በሰብአውያኑ መንግሥቶች ዘንድና ከእነርሱ ጋር ብቻ ሳይኾን፡ በማንኛውም የፍጥረት ወገን ዘንድና የፍጥረት ወገን ጋር ጭምር፡ ጥሩ ሕግ አክባሪዎችና ፈጻሚዎች ኾናችሁ፡ በእውነተኛዪቱ ሰላምና ፍቅር፡ ተስማምታችሁ ለመኖር የምትችሉ መኾናችሁን ለማወቅና አስተውሎ ለመገንዘብ፡ ለማንም የሚያዳግተው አይኾንም።

-እነዚሁ ሰብአውያኑ መንግሥቶች፡ የመጨረሻውን ሞትና ጥፋት ከሚያስከትልባቸው፥ ጽዋው እየሞላ በመፍሰስም ላይ ከደረሰው፡ ከክፋት ሥራቸውና ከዚህ ኃጢአታቸው፡ በእውነተኛ ንስሓ ለመመለስ፡ "እምቢ!" ከማለታቸው የተነሣ፡ ከምድረ-ገጽ እስከሚወገዱ ድረስ፡ እናንተ፡ በእኛዪቱ ኢትዮጵያ፡ **የእግዚአብሔር መንግሥታችን ሥር**፡ ከዜግነት አልፋችሁ፡ ልጆቻችንና ነጋሢዎቻችን፥ ካህናቶቻችንና መልእክተኞቻችን ለመኾን የበቃችሁ፡ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት ኾናችኋልና፡ የእነርሱ ሰብአውያን መንግሥታት ተሳታፊዎች ሳትኾኑ፡ በያላችሁበት፥ የሙያ ተግባራችሁን፡ በየግላችሁ እያካኼዳችሁ፡ ኪዳናዊ አገልግሎታችሁን ትፈጽማላችሁ።

እነዚሁ ሰብአውያኑ መንግሥቶች፡ የሚጠይቋችሁን ሕጋዊ ግብርና ቀረጥ፡ በዚያው፡ የራሳቸው በኾነው፡ በገዛ ገንዘባቸው፡ ባግባቡ በመክፈል፥ ሌላውንም፡ የነዋሪነት ግዳጃችሁን በመወጣት፡ የስም ዜጎቻቸው ኾናችሁ መኖራችሁን ለመቀጠል የምትፈቅዱ ብትኾኑ እንኳ፡ ይህንኑ ፈቃዳችሁን፡ በተግባር ላይ ከማዋል፡ ወደኋላ ማለት አያስፈልጋችሁም።

በዚህ አድራጎታችሁ፡ ልጁ ወዳጁ ኢየሱስ መሲሕ*፡ በዘመኑ በነበረው፡ በአረማዊው የሮሙ ቄሣር መንግሥት፡ ግብር እንዲከፍል በተጠየቀ ጊዜ፡ በሓዋርያው በጴጥሮስ አማካይነት፡ ከፍሎ የነበረበትን አብነቱን፥ ደግሞም፡ **"ይከውነነሁ፡ ነህብ ጸባሕተ ዲናር ለነጋሢ፤ አው አልቦ? ለንጉሥ፡ የግብር ገንዘብ መክፈል ይገባናልን? ወይስ፡ አይገባንም?"** ብለው፡ ተቃዋሚዎቹ አይሁድ ፈሪሳውያን በጠየቁት ጊዜ፡ **"ሀቡ፡ ዘነጋሢ፡ ለነጋሢ! ወዘእግዚአብሔርኒ፡ ግበሩ፡ ለእግዚአብሔር! ...ገንዘቡ፡ የንጉሡ ምሥልና ስም የተቀረፀበት ስለኾነ፡ የእርሱ ነውና፡ ለንጉሡ ክፈሉ! የእግዚአብሔር በኾነውም፡ የእግዚአብሔርን ሥራ አድርጉ!"** ሲል፡ በተገቢ መልስነት የሰጣቸውን መመሪያ ተከትላችሁ መፈጸማችሁ ነውና። (ማቴ. ፳፪፥ ፲፭-፳፪፤ ማር. ፲፪፥ ፲፫-፲፯። ሮሜ. ፲፫፥ ፩-፯።)

-እነዚሁ ሰብአውያኑ መንግሥቶች፡ በእናንተ አማካይነት ባገኙት፡ በዚህ ቅድስናቸው ምክንያት፡ አካኼዳቸው፡ እንደቀድሞው፡ ፍጻሜው፡ ሞትና ዕልቂት በኾነው፡ በክፋቱና በኃጢአቱ [በሓሰቱ] ሰፊ ጐዳና ላይ፡ በፃማና በድካም፥ በሥቃይና በፍጅት የሚደረግ ጕዞ መኾኑ ቀርቶ፡ መድረሻቸው ትንሣኤና የዘለዓለም ሕይወት በኾነው፡ በመልካሙና በጽድቁ [በእውነተኛው] መንገድ ላይ የሚካኼድ፡ የሰላምና የፍቅር፥ የደስታና የብልጽግና ብቻ ይኾናል።

---

* **መሲሕ (ግእዝ)** = ክርስቶስ (ግሪክ)።

-እንዲያውም፡ በእናንተ አስተምህሮ፥ የድምፅ ብዛታችሁም ምክንያት፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነትን፡ በተዋሕዶ እምነት ተቀብለው፡ እየራሳቸውን፡ **ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥትነት** ህልውና የሚያበቁበት ዕድል ሊቀርብላቸው፥ ጊዜውም ሊደርስላቸው ይችላል።

ታዲያ! እየራሳችሁን፡ በገዛ ፈቃዳችሁና ምርጫችሁ፡ በእግዚአብሔር እውነትና መንፈስ፡ ከእየአገሮቻችሁ፡ ሰብአውያን የዓለም መንግሥታት፡ የተገዢነት ቀንበር፡ ፈጽማችሁ፡ ነጻ የምታወጡበት፥ ደግሞም፡ በዚሁ፡ በእግዚአብሔራዊዋ እውነትና በመንፈሳዊው አምልኳችሁ አማካይነት፡ እየራሳችሁን፡ ለእኛዋ፡ **ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን፡** ልጅነት፥ ነጋሢነትና አገልጋይነት፡ ፈጽማችሁ የምትሰጡት፡ እንዴትና በምን ዓይነት መሥፈርት ነው? ይኼን መሥፈርት፡ በቅድሚያ ልታውቁት ስለሚገባችሁ፥ ስለሚያስፈልጋችሁም፡ እንዲህ በሚለው ቃሌ አብራራላችኋለሁ:-

በመጀመሪያ ነገር፡ **እነዚህ ሰብአውያን የዓለም መንግሥታት፡** መሠረታዊውና መዋቅራዊው፥ ጠፈራዊውና ጕልላታዊው፥ በጠቅላላ ኹለንተናዊው ምንነታቸውና ማንነታቸው፡ ፈጽሞ፡ **<u>ፀረ-እግዚአብሔራዊ</u>** ነው። ይህንም እውነታ፡ እየራሳቸው፡ "ዓለማዊ"፥ ወይም፡ "ሥጋዊ" [Secularism] በሚሉት ፍልስፍናቸው፡ በይፋ አረጋግጠው ያሳወቁ መኾናቸው፡ በእናንተም ዘንድ፡ የታወቀ እንደመኾኑ መጠን፡ በግልጽ ሲነገር የኖረ፣ አኹንም እየተነገረ ያለ እውነታ ነው።

ይህንኑ፡ <u>የፀረ-እግዚአብሔርነት ፍልስፍናቸውንና መመሪያቸውን፡</u> በእየራሳቸው ሰብአዊ ፈሊጥ፡ በተግባር ላይ ዐውለው የሚሠሩ መኾናቸውን፡ "ሕዝባዊ አገዛዝ" [Democracy] በሚሉት ጥበባዊ ስልታቸው፡ ዜጎቻቸውን አሳምነውና አስፈቅደው፡ በሚያስተዳድሩበት ሰብአዊ ሕገ-መንግሥታቸው ዐውጀዋል።

እነዚሁ ሰብአውያን የዓለም መንግሥታት፡ በዚያ ሕገ-መንግሥታቸው ውስጥ፡ ግልጽ ያደረጉት፡ አንድ ታላቅ የምስክር ሓውልት አለ፤ ያም ምስክርነት፡ "እግዚአብሔር" የሚለው፡ የእኛ፡ የፈጣሪ ስማችን፥ በተለይም፡ የእኔ፡ የኢትዮጵያዋ ድንግል ማርያም ስም፥ ደግሞም፡ እግዚአብሔራዊና የእኛ የኾነው፡ ማናቸውም ዓይነት፡ የእውነትና የሕይወት፥ መልካምና ጠቃሚ መልእክት፡ በመጀመሪያ ነገር፡ በማንኛውም መንግሥታዊ መድረክ ላይ፡ በቃል ተነሥቶ ከመጠራትና ከመነገር፥ በጽሑፍም፡ ሠፍሮ፥ ተጠቅሶም እንኳ ቢኾን፡ በምንም መልክና ይዘት ከመቅረብ፡ በሕጋቸው፡ በጥብቅ የተከለከለና የታገደ፥ ፈጽሞ የማይፈቀድም፥ መኾኑን የሚያረጋግጠው እውነታ ነው።

ከዚህ የተነሣ፡ ምናልባት፡ በአጋጣሚ፥ ወይም፡ በስሕተት፡ ስማችን ተወስቶ፥ ወይም፡ ተጠቅሶ፡ ቃላችን በአንደበት፥ መልእክታችንም በጽሑፍ ቢቀርብላቸው እንኳ፡ ተቀብለው ሊፈጽሙት ቀርቶ፡ ሊያዳምጡትም እንኳ፡ የፈቃደኛነት ዝንባሌው፡ ፈጽሞ እንደሌላቸው፡ በማያቋርጠው ድርጊታቸው፡ በገሃድ ይታያል።

እንዲያውም፡ የዚያ ሕገ-መንግሥታቸው አቋም፡ እርሱ ባስገኛቸው፥ ወደፊትም በሚያስገኛቸው ምድራውያን የሥራ ድርጅቶች አካላት ላይና ቍሳውያት የመመሪያ ባሕርያት ውስጥ፡ እግዚአብሔራዊ የኾነ፡ አንዳችም ዓይነት ፅንሰ-ሓሳብና የህልውና ፍንጭ፡ በምንም መልኩና ይዘቱ እንዳይወሳና እንዳይንፀባረቅ በሚደነግግ፡ ፀረ-እግዚአብሔርነት አስተሳሰብ ላይ የተመሠረተና ተገድግዶ የታነፀ፥ የተዋቀረና የተደመደመ መኾኑን፡ ይኼው እውነታው ያረጋግጣል።

ይህ ኹሉ፡ ሃይማኖታዊ የግብዝነትና የሽንገላ ሥራ፡ በእነርሱ እየተካኼደ ያለው፡ አንዳንዶቹ፡ "In God We Trust!" "በእግዚአብሔር እንታመናለን!" የሚል መፈክራቸውን፡ በገንዘባቸው ወረቀት ላይ ዐትመውና በሰንደቅ ሰሌዳቸው ላይ ቀርፀው፡ የሃይማኖት አቋማቸውን፡ በይፋ ማሳወቃቸውን፡ ከይሉኝታ-ቢስነት ድፍረታቸው የተነሣ ዘንግተውት መኾኑ፡ እጅግ ያስደንቃል!

ስለዚህ፡ <u>ይህ መለኮታዊ ምዕዳን የተላለፈው፡ ለእነዚሁ ሰብአውያን መንግሥታት አይደለም።</u> እነሆ፡ አኹን በገለጽሁላችሁ ምክንያት፡ ለእነርሱ ሊተላለፍ አይቻልም፤ አይሰሙትምና፤ ቢሰሙትም እንኳ፡ አይቀበሉትምና።

ነገር ግን፡ <u>ይህ መለኮታዊ ምዕዳን የተላለፈው፥ ሊተላለፍ ያስፈለገው፥ የተገባውም፡</u> ለእነዚሁ ሰብኣውያን መንግሥታት ሳይኾን፡ በተለይ፡ <u>ለእናንተ፡ የየአገሩ ሕዝቦች አባሎች ለኾናችሁት፡ ለእያንዳንዳችሁ፡ ወንዶችና ሴቶች ግለሰቦች ነው።</u>

## "ሕዝባዊ አገዛዝ" [Democracy] እና "ከፋፍለህ ግዛ!" የሚሉት ፍልስፍናዎች፡ ምንድር ናቸው?

ስሙና ዝክረ-ነገሩ ከዚህ ቀደም ብሎ፡ ከተነሣ ዘንድ፡ በአኹኑ ጊዜ፡ እናንት ዓለማውያንና ሥጋውያን ሰዎች፡ እንደአዲስ ቍም-ነገር፥ ወይም እንደእንግዳ ግኝትና እንደታላቅ ፍልስፍና ቆጥራችሁት፥ አምናችሁበትም፡ በአብዛኛዎቹ የዓለም አገሮቻችሁ፡ እየተወደሰና እየተሠራበት ስላለው፡ "ሕዝባዊ አገዛዝ" [Democracy] ስለምትሉት ዘይቤ፡ በዚህ፡ የዐዋጅ ቃሌ፡ በጥቂቱም ቢኾን፡ ልገልጽላችሁ የሚያስፈልግ እውነታ አለኝ። እርሱም እንዲህ የሚል ነው፦

ይኼ፡ "ሕዝባዊ አገዛዝ" [Democracy] የምትሉት ዘይቤያችሁና ፍልስፍናችሁ፡ ለእኛ፡ ለአብና ለእም፥ ለወልድና ለመንፈስ ቅዱስ፡ ለአንድነታችን መለያና መታወቂያ የኾነውን፡ "እግዚአብሔር" የሚለውን ቃል፡ በስም አጠራሩ ኾነ በፈጣሪነት ግብሩ፡ በምንም መልኩና ይዘቱ የተለያችሁትና የማትፈልጉት፥ የምትቃወሙትና የምትጠሉት መኾናችሁን አረጋግጣችሁና በይፋ ለማሳወቅ ስትሉ፡ በክፉው ሰይጣናዊው መንፈስ፡ ኾን ብላችሁ፡ የፈጠራችሁት መኾኑ፡ በቀደመ ነገር፡ መገለጥ አለበት።

እርሱንም፡ እናንተ፡ በክፉው አስተሳሰባችሁና አድራጎታችሁ፡ እንዲህ እንደዛሬው፡ እጅግ ከማሰነው [ከተበላሸው] አስከፊ ኹኔታው ከመዳረጋችሁ በፊት፡ *ፅንሰ-ሓሳቡ እኮ፡ ጥንት ከመሠረቱ፡ በመልካም ጎኑና እውነተኛ ባሕርዩ፡ "ሥርዓት-መንግሥት" ተብሎ፡ ከእኛዪቱ፡* ***ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን*** *ዘንድ የተገኘ መመሪያ ኾኖ፡ በቀና መልኩና በትክክለኛ ይዘቱ፡ ሲሠራበት የኖረ መኾኑን፡ ዐውቃችሁ ልትገነዘቡት ይገባችኋል። ይህንም፡ የቅዱሱ ኪዳን፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቼ፡ ሕያውት ከተማ በኾነችው፡ በአኵስም፡ ከመጀመሪያው ጊዜ አንሥቶ፡ እስከዛሬ፡ እውን ኾኖ፡ በተግባር ላይ ሲውል፡ ይኸው የምትመለከቱት ነው።*

*ይኸውም፡ ከታማኙ ልጃችንና ነጋሢያችን፥ ካህናችንም ከኾነው፡ ከጻድቁ መልከ-ጼዴቅ ጋር ባደረግነው ቃል ኪዳናችን የተነሣ፡-*

*-እያንዳንዳችሁ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊ እና ኢትዮጵያዊት ልጆቻችን፥ በእየራሳችሁ፡ መልከ-ጼዴቅ ናችሁ፤*

*-በእየውስጣችሁ፡* ***ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር*** *መንግሥታችን አለች፤*

*-በእየግላችሁ፡ የዋናው፡ የቤተ-ሕዝቧ አቋም፡ ሙሉ አባል የመኾንን ማዕርግን ተቀዳጅታችኋል፤*

*-በቤተ-ምልክናው፥ በቤተ-ክህነቱም ዘርፎች ውስጥ፡ ለማንኛውም፡ የአገልግሎት ደረጃ፡ ከአባልነት፡ እስከሊቀ መንበርነት፡ ከዚያም፡ እስከአጼነቱና እስከአጼዪትነቱ ድረስ ላለው የሢመት ዕርከን፡ መለኮታዊቷን እውነታችንንና መንፈስ-ቅዱሳዊ ዕውቀታችንን በተመሉ፡ በእነዚሁ አባላት ልጆቻችን ድምፅ፡ ለመምረጥም ኾነ ለመመረጥ፡ ነጻነቱና መብቱ፥ ሥልጣኑና ባለቤትነቱ፡ በፍጹም ፈቃደኛነትና በሙሉ ጸጋነት የተቀበላችሁት፡ የእያንዳንዳችሁ፡ ኪዳናዊ ሀብት ነው።*

*በሰብአውያኑ መንግሥታት ዘንድ፡ "ሕዝባዊ አገዛዝ"* [Democracy] *የሚሉት፡ ይህ፡ ፀረ-እግዚአብሔር ፍልስፍናና ሃይማኖተ-ቢስ ዘይቤ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖትን መሠረትና መመሪያ አድርጋ በምትኖረው፡ በ*ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር *መንግሥታችን* ዘንድ፡ "*ሥርዓት መንግሥት*" ተብሎ፡ የሚታወቀውና በዘለዓለማዊ ሕያውነት የሚሠራበት መለኮታዊ መርኆ ነው። ባጭር ቃል፡ የሰብአውያኑ *መንግሥታት* "ሕዝባዊ አገዛዝ [Democracy]"፡ በመሠረታዊው አቋሙና በኹለንተናዊው ባሕርዩ፡ **ፀረ-እግዚአብሔርና ሓሳዊ** ሲኾን፡ **የእግዚአብሔርዋ ኢትዮጵያ፡** "*ሥርዓት-መንግሥት*" ግን፡ በመሠረታዊው አቋሟና በኹለንተናዊው ባሕርይዋ፡ **መለኮታዊትና አማናዊት** ናት። ሊታረቅ የማይቻለው፡ የኹለቱ ወገኖች፡ ፍጹም ልዩነት፡ ይህ እውነታ ነው።

በሰብአውያኑ መንግሥታት ዘንድ፡ "ሕዝባዊ አገዛዝ" [Democracy] የሚሉት ፍልስፍና፡ በአዎንታዊው እውነተኛና መልካሙ ገጽታው፡ **የኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን** በኾነው፡ **"ሥርዓተ-መንግሥት"**፡ ዛሬም፡ እንዴት፡ እውን ኾኖና በተግባር ላይ ውሎ እንደሚሠራ፡ ማየት ይቻላል፤ ይኸውም፡ ባለፈው በመጨረሻው ተጠሪያችን፡ በአጼ ኃይለ-ሥላሴ የአገልግሎት ዘመን፡ የርእሰ-አድባራት አኵስም ጽዮን ንቡረ-እድና የአውራጃዋ አስተዳዳሪ አድርገን የሾምነው፡ ኪዳናዊ ልጃችንና አገልጋያችን ኤርምያስ፡ በአኹኑ ጊዜ፡ እያካኼደ ያለውን ተልእኮ ተመልከቱት!

በአኵስም በሚፈጸመው፡ በዚሁ፡ **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር ሥርዓተ-መንግሥት መሠረት፡ አጼው** በሌለበት፡ **ንቡረ-እዱ**፡ የእርሱ ተጠሪ ኾኖ፡ ይወክለዋል። **ቤተ-ሕዝቡ** ደግሞ፡ በታላቁ ልዩ መጥቅዕ [ደወል]፡ የዐዋጅ ጥሪ ተደርጎለት፡ በንቡረ-እዱ፥ ወይም፡ በአፈ ንቡረ-እዱ ሊቀ-መንበርነት የሚሰበሰበው **"ማኅበር"** የሚባለው ጉባኤ ነው። ይህ ማኅበራዊ ጉባኤ፡ ለዓቅመ-አዳምና ሔዋን የደረሱ ወንዶችንና ሴቶችን ያጠቃለለ፥ መላውን የከተማዪቱንና የአካባቢዋንም ሕዝብ ያካተተ ሲኾን፡ በመንፈስ ቅዱሳዊውና በኪዳናዊው የአባሎች ድምፁ፡ የመምረጥንና የመመረጥን ጨምሮ፡ ለማናቸውም ጉዳይ፡ የመጨረሻውን ውሳኔ የሚሰጥ ነው።

ኹለቱ የአገልግሎት ዘርፎቹ ለኾኑት፡ ለቤተ-ምልክናውና ለቤተ-ክህነቱም፡ አባሎቻቸውንና ኹለቱን፡ ሊቀ-መንበሮቻቸውን፡ ከዚሁ፡ ከቤተ-ሕዝቡ አባሎች መካከል፡ በድምፅ፥ ወይም፡ በአንብሮተ-እድ [እጅ በማኖር] መርጦ የሚሠይምላቸው ይኸው ማኅበር ነው።

ታዲያ! በንጽሕናና በታማኝነት ረገድ፡ «እውነተኛው "ሕዝባዊ አገዛዝ [Democracy]" የትኛው ነው?» ትላላችሁ? በፀረ-እግዚአብሔርነትና በሓሰት፥ በሃይማኖተ-ቢስነትና በክፋት ኃይል ተመሥርተው፡ እርስ በርሳቸው በሚናቆሩት፡ በእናንተ ሰብአውያን መንግሥታት ዘንድ የሚሞካሸው ሳይኾን፤ በእርግጥ፡ በእግዚአብሔርዋ እውነትና በመንፈስ ቅዱሳዊው አምልኮ ላይ ተመሥርታ በምትካኼደው፡ **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን** ዘንድ ያለው፡ **"ሥርዓተ-መንግሥት"** መኾኑ፡ ሊታበል ከቶ አይቻልም።

እኛ፡ እንዲህ አድርገን፡ በምሥጢረ ተዋሕዶ ጸጋና በረከት፡ አስማምተንና አንድ አድርገን፡ ለፍጥረታችን የመሠረትነውን፡ መልካሙን ግለሰባዊና ኅብረተሰባዊ የህልውና ሥርዓት፡ የእናንተ ሰብአውያን መንግሥቶቻችሁ፡"ሥጋዊና መንፈሳዊ"፥ "ዓለማዊና ሃይማኖታዊ፥ "ቤተ-ክህነትና ቤተ-ምልክና" [Church and State] በሚል የአገዛዝ ፈሊጣቸው፡ <u>እንዲት</u> የኾነችውን፡ ይህችኑ፡ <u>**ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችንን፡**</u> "ከፋፍለህ ግዛ!" በሚለው፡ ሰይጣናዊ ፍልስፍናቸው፡ **ከኹለት ከፍለው፡** በሰላም ለመኖር፡ ለዘመናት ሲጥሩና ሲግሩ፡ ይኸው አኹንም ይታያሉ። ነገር ግን፡ ሙከራቸው፡ ከንቱ ከመኾን በቀር፡ ፈጽሞ የሚሠምርላቸው አይኾንም።

ለመኾኑ፡ በእኛዪቱ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን ላይ በተፈጸመው ደባ፡ "ከፋፍለህ ግዛ!" የሚለው፡ ይኼ፡ የሰዎች ሰይጣናዊ ፍልስፍና፡ በገሃድና በይፋ፡ መቼ፥ እንዴት እና በማንስ እንደተፀነሰና እንደተወጠነ ታውቃላችሁ? እኔው ልግለጽላችሁ!

ልጇ ወዳጇ ኢየሱስ መሲሕ በተወለደ፡ በ፫፻፳፭ ዓመተ-ምሕረት፡ የሮም ንጉሠ ነገሥታዊ ግዛት ቄሣር ቈስጠንጢኖስ፡ ራሱንና ግዛቱን፡ በዐዋጅ፡ ከጣዖት አምልኮ አረማዊነት ነጻ በማውጣት፡ ለክርስትና ሃይማኖት ካበቃ በኋላ፡ በዚያ፡ አዲስ የክርስትና ሃይማኖቱ መሠረት፡ መንግሥቱን፡ እንዴት ማዋቀር፥ ሕዝቡንና አገሮቹንም፡ እንዴት መምራትና ማስተዳደር እንዳለበት፡ ምክራቸውንና አሳባቸውን እንዲሰጡት፥ ሥርዓቱንም፡ በጽሑፍ አዘጋጅተው እንዲያቀርቡለት፡ በዚያን ጊዜ፡ በግዛቱ ውስጥ፡ በአንዲትነት ጸንታና ቀጥላ በነበረችው፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን የቤተ-ክህነት ዘርፍ ውስጥ እያገለገሉ ያሉ፡ ቍጥራቸው፡ ፫፻፲፰ የኾነ፡ የሃይማኖቱን ዓዋቂዎችና የቤተ-ክርስቲያን መሪዎች ሊቃነ ካህናት ጠርቶ፡ በታናሽ እስያ ባለች፡ "ኒቅያ" በተባለች ከተማው ሰበሰባቸው።

እነርሱም፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችንን የሚወክል፡ ከቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቹ መካከል፡ አንድም ተጠሪ መልእክተኛ፡ ባልተጠራበት፥ ከዚያ የተነሣም፡ ባልተገኘበት፡ በዚያች ከተማ፡ ጉባኤ አድርገው፡ ቄሣሩ ቆስጠንጢኖስ በጠየቃቸው ጉዳይ ላይ፡ በስፋትና በጥልቀት ከተመካከሩ በኋላ፡ ምን አቀረቡለት? ያቀረቡለት፡ ተገቢ የኾነውን፡ ከኖኅ ቀጥሎ፡ ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን፡ በሥዩመ-እግዚአብሔርነት ተቀብቶ፡ በአጼነት ያገለገለንን፡ የኢትዮጵያዊዉን፡ የመልከ-ጼዴቅን መለኮታዊ ሥርዓት አይደለም። ማቅረብ ይገባቸው የነበረው፡ ቄሣሩ ቆስጠንጢኖስ፡ ይህንኑ መለኮታዊ ሥርዓት፡ እንዲያውቀው በማድረግ፥ ቢያስፈልግም በጽሑፍ አዘጋጅተው፡ ያን ዝግጅታቸውን፡ በተግባር ላይ እንዲያውለው የሚመክርና የሚያሳሳብ ውሳኔን ነበር። ነገር ግን፡ የኾነው፡ ይህ አልነበረም።

በዚያ ፋንታ የኾነው፡ ሌላ ኾኖ ተገኘ! ያም፡ የራሳቸው የኾነ፥ እኛ፡ በፈጣሪነታችን፡ አንድ አድርገን፡ በመልካም የሠራነውን መለኮታዊ ሥርዓተ-መንግሥት ያፋለሰና ያቃወሰ ሲኾን፡ እርሱንም፡ እነርሱ፡ "ሥጋዊ" እና "መንፈሳዊ" ብለው፡ ለኹለት የከፈሉት፥ አርእስቱንም፡ "ፍትሓ-ነገሥት" ብለው የሰየሙት፡ አንድ የሰውኛ ሕገ-መንግሥት ነው።

እንዲህ፡ ለኹለት የከፈሏትን፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችንን፡ በአንድ ወገን፡ ራሳቸውን "ቤተ-ክርስቲያን" ብለው በመጥራት፡ መንፈሳዊው ክፍል የኾነውን፡ የቤተ-ክህነቱን ዘርፍ ለራሳቸው ለይተውና አስቀርተው በመያዝ ነበር።

ለቄሣሩ ቆስጠንጢኖስ ደግሞ፡ የቤተ-ሕዝቡን ዘርፍ እንዲገዛበትና እንዲያስተዳድርበት፡ አጽድቀው የሰጡት፡ ራሱን፡ "*መንግሥት*" ብሎ በመሠየም፡ ሥጋዊው ክፍል የኾነውን፡ የቤተ-ምልክናውን ዘርፍ የያዘውን፡ ይህንኑ፡ ፍትሐ-ነገሥቱን ነው።

ይህንም ሲያደርጉ፡ አስቀድመው፡ እርሱን፡ ራሱን፡ የሰበሰባቸውን፡ አዲሱን ክርስቲያን፡ ቆስጠንጢኖስን፡ እንደመልከ-ጼዴቅ ሹመት፡ ከእግዚአብሔር ልጅነቱና ነጋሢነቱ ጋር፡ ለአጼነት የሚያበቃውም፡ የክህነቱ ሥልጣን፡ ከክርስትና ጥምቀቱ ጋር፡ በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ የተሰጠው መኾኑን ሳያስታውቁት፥ እርሱም፡ ያን ጸጋ ለመቀበል ፈቃደኛ መኾኑን ሳያረጋግጡ፡ እንዲያው ዝም ብለው፡ በዚያው፡ በዓለማዊው ቄሣራዊ ሥልጣኑ መቀጠሉን እያወቁ እንደነበረ፡ የድርጊታቸው ውጤት፡ ይኸው፡ እስከዛሬ ድረስ፡ በይፋ እየመሰከረባቸው ይታያል።

ይኸውም፡ በአኹኑ ጊዜ፡ ሰፍኖና ተስፋፍቶ፥ ጸንቶና ሕጋዊ ዕውቅናን፥ ተቀባይነትንም አግኝቶ፡ በመላው ዓለም፡ የሰዎች መንግሥታት ዘንድ እየተሠራበት ያለው ፍልስፍናቸው ሲኾን፡ በዚህ ፍልስፍናቸው መሠረት፡ መንፈሳዊዉን ወገን የሚወክለውን፡ "**ቤተ-ክርስቲያን**"፥ ሥጋዊዉን ወገን የሚወክለውንም፡ "***መንግሥት***"፥ በእነርሱም ቋንቋ፡ "Church and State" ብለው ለፈጠሩት፡ የ"ሕዝባዊ አገዛዝ" [Democracy] ስልታቸው፡ መነሻ የኾነው፡ ያ ፍልስፍናቸው ተመሥርቶ፡ እነሆ፡ በተግባር ላይ መዋል የጀመረው፡ በዚያ ጉባኤ በር-ከፋቺነትና ወጣኝነት መኾኑ ሊታወቅ ይገባል።

ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቼ፡ በዚያ፡ የኒቅያ ጉባኤ ላይ እንዳይገኙ መደረጉ ብቻ ሳይኾን፡ የተገኙት የግብፅ ኦርቶዶክሳውያን፡ የራሳቸውን ግብፃውያን መነኮሳት፡ ራሳቸው መርጠውና ሾመው የሚልኩላቸውን፡ ያለአንዳች ቅሬታ ከመቀበል በቀር፡ እኒሁ፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቼ፡ ከመካከላቸው፡ የራሳቸውን፡ አንድ "ጳጳስ" እንኳ እንዳይመርጡ የተወሰነውም፡ በዚያ፡ የኒቅያ ጉባኤ ላይ ኾኖ፡ ይኸው ድንጋጌ፡ የፍትሓ ነገሥቱ አንዱ አንቀጽ በመኾን፡ በራሳቸው፡ በግብፅ ኦርቶዶክሳውያኑ መነኮሳት "ጳጳሳት" ተጽፎ፥ ይኸው የፍትሐ-ነገሥት መጽሓፍ፡ በእነርሱው እጅ፡ ለኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቼ፡ ያለኀፍረትና ያለይሉኝታ ተሰጥቶ፡ አኹንም ሲነበብ ይኖራል።

ይህ ኹሉ ጥቃት አንሶ፡ እኒሁ፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቼ፡ ምዝላታቸው፡ ኢትዮጵያዊው መልከ-ጼዴቅ በቈረቈራትና ዐፅመ-ርስታቸው በኾነችው፡ በኢየሩሳሌም፡ የደረሰባቸውን ግፍ ተመልከቱት!

በዚያ፡ የራሳቸው በኾነችው፡ በኢየሩሳሌም ከተማ፡ ያላቸውን ቋሚ የመሬት ይዞታ፡ ግብፃውያኑ የኦርቶዶክስ ቤተ-ክርስቲያን መሪዎች የኾኑት መነኮሳት፡ ያለአገባብ በሓሰትና በኃይል ነጥቀው ወሰዱባቸው። እነዚሁ ግፈኞች፡ ይህንኑ ቋሚ ይዞታ፡ ለባለመብቶቹ፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቹ፡ በፍትሕ-ርትዕ፡ እንዲመልሱ በሚጠየቁበት ጊዜያት ኹሉ፡ አኹንም፡ ያለኀፍረትና ያለይሉኝታ፡ በድፍረት የሰጡትን፡ እንዲህ የሚለውን መልስ፡ ሰምታችሁት፥ አንብባችሁትስ የለምን?

እርሱም፦ "እንኳንስ በኢየሩሳሌም ያለው ቦታቸው ይቅርና፡ 'አገራችን' በሚሏትና በስሜ በተጠራችው ኢትዮጵያ፡ ያለው ምድር፥ እነርሱ ራሳቸው፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ሳይቀር፡ ሰውነታቸው ጭምር፡ የማን ኾነና ነው? የእኛ፡ የግብፃውያኑ ኦርቶዶክስ ጳጳሳት አይደለምን?" በሚል፡ የድፍረት ቃል የተመላበት ነው። (ኢትዮጵያ የዓለሙ መፋረጃ፣ በንቡረ-እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ፣ ገጽ ፩፻፳፱-፩፻፴፫፤ ፩፻፷፭-፩፻፷፯።)

ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቹ፡ በአኹኑ ጊዜ፡ በኢየሩሳሌም ካለው የቦታ ይዞታቸው መካከል፡ ከእነዚሁ ከግብፃውያኑና ከመሰሎቻቸው የኦርቶዶክስና የካቶሊክ አብያተ-ክርስቲያናት መነኮሳት፡ የግፍ ዝርፊያና ንጥቂያ ተርፎ፡ በእጃቸው የቀረው፡ ያው፡ እጅግ ጥቂቱ እንኳ፡ እስካኹን ሊቆይ የቻለው፡ በእስልምና መሪዎች ሥልጣንና ኃይል መኾኑ፥ በዚህም ረገድ፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቹ፡ በእነዚሁ፡ በግብፃውያኑ "ጳጳሳት" ዘንድ፡ ለእነርሱ ቅኝ ተገዥነት ብቻ ሳይኾን፥ ባርነት ጭምር እንደተሰጧቸው፡ አኹንም የሚገምቱ መኾናቸው፡ እዚህ ላይ ዐብሮ ሊዘከር ያስፈልጋል።

## እናንተ፡ እነማን ናችሁ?

ለመኾኑ፡ ይህን፡ የዐዋጅ ቃሌን የምትሰሙ፡ እናንተ፡ እነማን ናችሁ? እናንተማ፡ ይህንኑ፡ ፀረ-እግዚአብሔር የኾነውን፡ የሰብአውያን መንግሥቶቻችሁን፡ የእምነት አቋማቸውን ተቀብላችሁትና አምናችሁበት፡ "ሕዝባዊ አገዛዝ" [Democracy] በተባለው ዓለማዊና ሥጋዊ ፍልስፍናቸው አማካይነት፡ "እንደራሴዎቻችን ኾነው እንዲያገለግሉን፡ እነርሱን መርጠን፡ ሥልጣኑንና ኃይሉን፥ መሣሪያውንም ያስጨበጥናቸው፡ እኛ ነን!" ያላችሁት ናችሁ።

አዎን! <u>እናንተማ፡</u> ይህን በማለታችሁ፡ ይኸው ሓሰተኛው የእምነት አቋማችሁ ባስከተለው፡ በዚሁ መቅሠፍታዊው ዘመቻ እየተካኼደና በቅጣቱ ሠይፍ እየተፈጸመ ላለው፡ <u>ለጥቃቱና ለዕልቂቱ፡ እየራሳችሁን፡ በነፍስ ወከፍ፡ ሰለባ አድርጋችሁ ሰጥታችሁ፡ ይኸው፡ ያለማቋረጥ፡ እየተሠየፋችሁና እየወደቃችሁ፥ እየተሠቃያችሁና እያለቃችሁ ያላችሁት ምስኪኖች ናችሁ።</u>

*እንግዴህ፡ በአኹኑ ጊዜ፡ በዚሁ መቅሠፍታዊ ዘመቻና በቅጣቱ ሠይፍ፡ እየተካኼደና እየተፈጸመ ባለው ጥቃትና ዕልቂት ውስጥ፡ እየራሳችሁ፡ በነፍስ ወከፍ፡ ሰለባ ኾናችሁ ለምትወድቁት፡ ለእናንተ፡ በኹለቱም ተፃራሪና ተዋጊ ጎራዎች ዘንድ፡ የየአገሩ ሕዝቦች አባሎች ለኾናችሁት፡ ለእያንዳንዳችሁ ግለሰቦች፡ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችን ኹሉ፡ እኔ፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ በማስተላልፍላችሁ፡ በዚህ መለኮታዊ ምዕዳኔ፡ የምላችሁን ስሙ!*

## እኔ፡ ማን ነኝ?

*አኹን እየተናገርኋችሁ ያለሁት እኔስ፡ ማን ነኝ? አውቃችሁኛል? [ዝምታ!]*

*መልሱልኝ እንጂ! ለምን ዝም ትላላችሁ? አንዳችሁ እንኳ፡ መልሱልኝ እንጂ! [አኹንም፡ ዝምታ!]*

*እንዴ! 'እናውቅሃለን! እናውቅሻለን! እናውቃችኋለን!' ወይም፡ 'አናውቅህም! አናውቅሽም! አናውቃችሁም!' የሚለውን ቃላችሁን በማሰማት፡ ከኹለት አንዱን በሉ እንጂ! ለምን ዝም ትላላችሁ? [እንደገና ዝምታ!]*

*አይዟችሁ! እኔ እኮ፡ ሓሳዊው፥ ወይም፡ ምትሓታዊው መንፈስ፥ ወይም፡ ሥጋ-ለባሹ ፍጡር አይደለሁም። ፈርታችሁኝ እንደኾነ፡ እንድትፈሩኝ ያደረገው፡ በየውስጣችሁ ያለው፡ ክፉው ነውና፡ ቀድሞም፡ ወደእየራሳችሁ፡ በፈቃዳችሁ ያስገባችሁት፡ እናንተው፡ እየራሳችሁ እንደመኾናችሁ መጠን፡ አኹንም፡ በውስጣችሁ የቀረ፡ እውነተኛው መንፈስ ካላችሁ፡ ይህንኑ፡ ክፉውን፥ ሓሳዊውን፥ ወይም፡ ምትሓታዊውን መንፈስ፥ ከእየራሳችሁ ልታስወጡት የምትችሉት፡ እናንተው ስለኾናችሁ፡ በዚያ፡ በእግዚአብሔራዊዋ እውነትና በመንፈስ ቅዱሳዊ የአምልኮ ትጥቃችሁ፡ በቆራጥነት በምትሰጡት ውሳኔያችሁ፡ ከውስጣችሁ አስወግዱት! አለዚያ፡ እኔን ልታውቁኝ፥ ቃሌንም ልትሰሙ አትችሉም። [የባሰ ዝምታ]*

*አዎን! እንግዴህ፡ እንዲህ፡ በቀጠለ ይዘት፡ ዝም ያላችሁት፥ ደግሞም፡ ማወቃችሁንም፥ አለማወቃችሁንም፡ አንዳችሁ እንኳ፡ ልትገልጹልኝ ያልፈለጋችሁት፥ ይልቁንም፡ እያወቃችሁ፡ እንዳላዋቂ ለመኾን፥ ወይም፡ ሳታውቁ ቀርታችሁ ከኾነም፡ ከዚሁ አላዋቂነታችሁ የተነሣ ሳይኾን፡ እንዲያው ባጠቃላዩ፡ ዝም ያላችሁት፡ ስላወቃችሁም፥ ስላላወቃችሁም አለመኾኑን፡ ይህ ኹኔታችሁ ያስረዳል።*

*እውነታው ግን፡ ለኹሉም ጥያቄዎች፡ የምትመልሱት እውነተኛ መልስ፥ ደግሞም፡ ልትመልሱ የምትችሉበት፡ ምንም ዓይነት ምክንያት፥ ወይም፡ ሰበብ እንኳ ስለሌላችሁ ብቻ ነው፡ እንዲያው ባጠቃላዩ፡ ዝምታውን የመረጣችሁት።*

"እናውቃለን!" ብትሉ፡ "ታዲያ! ካወቃችሁ"፥ ወይም፡ "አናውቅም!" ብትሉም፡ "ታዲያ! ካላወቃችሁ፡ ለምን ዝም አላችሁ?" የሚል ተከታይ ጥያቄ እንደሚቀርብባችሁ ስለተገነዘባችሁ አይደለም፡ እንዲህ በዝምታችሁ የቀጠላችሁት? ዝም ሳትሉ፡ መናገር ከጀመራችሁ ደግሞ፡ በዚያን ጊዜ፡ ተከታታይ ጥያቄ ስለሚቀርብባችሁ፡ ተገቢ፥ ወይም፡ በቂ የኾነ መልስን መስጠት ሊኖርባችሁ ነው። ነገር ግን፡ ለጥያቄዎቹ ኹሉ፡ አንድም መልስ ስለሌላችሁ፡ ስለዚህ፡ ዝምታውን መረጣችሁ። አይደለም? ነው እኮ!

እንግዴህ፡ በዚህ ግብራችሁ፡ እናንተ፡ እስካኹንና አኹንም ገና፡ መስላችሁና ኾናችሁ የተገኛችሁት፡ እውነተኞቹና መልካሞቹ፥ የመጨረሻዎቹና የዘላለሞቹ አዳምና ሔዋን የኾንነውን፡ ልጄን፡ ኢየሱስ መሲሕንና እኔን፡ እናቲቱን ድንግል ማርያምን ሳይኾን፡ የዘር ግንዳችሁ የኾኑትን፡ እነዚያኞቹን፡ የመጀመሪያዎቹን መኾኑን አረጋገጣችሁ። እነርሱም፡ ያን፡የሚያውቁትን የፈጣሪያቸውን ደግ ፈቃድ ሳይኾን፡ የፈጣሪያቸው ባላጋራ የኾነውን፡ የማያውቁትን፡ የክፉውን መንፈስ አጥፊ ምክር ተቀብለው የፈጸሙት፡ አዳምና ሔዋን ናቸው።

አኹንም፡ ለዚህ ኾነ፥ ለሌላው ጥያቄዬ፡ ምንም ዓይነት መልስ ልትሰጡኝ የማትፈልጉ፥ የማትችሉም መኾናችሁን ስላወቅሁ፡ እነሆ፡ የ፯ሺ፭፻፰ (ሰባት ሽህ አምስት መቶ ስምንት) ዓመታትን ባስቆጠረው፥ እስከዛሬና አኹንም፡ በዚሁ መልኩ ጸንቶ በቀጠለው፡ በረዥሙ ዘመን፡ የፅመት ዝምታችሁ መካከል፡ ዛሬም፡ ብትሰሙኝም፥ ባትሰሙኝም፡ ለጥያቄዎቼ፡ እኔው ራሴ፡ በእናንተ ስም፡ መልሶቻችሁን እየሰጠሁ፡ የተነሣሁበትን ምዕዳኔን፡ በቀጥታ እቀጥልላችኋለሁ።

አዎን! እውነታችሁን ነው፤ እኔን፡ አታውቁኝም። የት ታውቁኛላችሁ? አታውቁኝም። እንዴትስ ልታውቁኝ ትችላላችሁ? አይቻላችሁም። ከጉዳት በቀር፡ ምንም ዓይነት፡ ረብኅ ጥቅም የሌለውን፡ ሌላውን፡ ጥቃቅኑን ኹሉ፡ ለማወቅ ስታስሱና ስትደክሙ፥ ስትጥሩና ስትግሩ፡ ለመኾኑ፡ እኔን ለማወቅ፡ ጥቂት ያህል እንኳ፡ የፍላጎትና የሙከራ ዝንባሌን አሳይታችኋል? አላሳያችሁም።

እኔን አውቃችሁኝማ ቢኾን ኖሮ፡ ዛሬ፡ እየራሳችሁን ዳርጋችሁት በምትገኙበት፡ ይህን በመሰለው፡ በዚህ ውርደትና ጕሥቍልና፥ መከራና ሥቃይ፡ ስትማቅቁ ትታዩ ነበርን? አትታዩም ነበር።

እናንተ የምትጠሉኝና ስሜ እንኳ እንዲጠራባችሁ የማትፈልጉት እኔ፡ ማን እንደኾንሁ፡ እስኪ፡ እኔው ልንገራችሁ!

ራሴን፡ እንዲህ በራሴ፡ ለእናንተ፡ ልገልጥላችሁ የፈለግሁት፡ እንዲያው አይደለም። በብርቱና በበቂ ምክንያት ነው። እርሱም፡-

- እግዚአብሔር እም በመኾኔ፡ በመንበረ-ጸባዖት ቅድስት ሥላሴነቴና በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥትነቴ፡ እኔ፡ እናንተን የፈጠርኋችሁ፡ የራሴ ፍጡሮቼ፥ የወለድኋችሁም፡ ልጆቼ በመኾናችሁ ነው፤

- ይልቁንም፡ እኔው በሰጠኋችሁ ነጻነትና ሥልጣን፡ በእየራሳችሁ ባደረጋችሁት የተሳሳተ ምርጫችሁ የተነሣ፡ ለክፉው በመገዛታችሁ ምክንያት፡ በእየራሳችሁ ላይ ያመጣችሁትንና የኃጢአታችሁ ዋጋ የኾነውን የሞት ቅጣታችሁን፡ ቅድስት ድንግል ማርያምን በተዋሓድሁበት ሰውነቴ፡ እያንዳንዳችሁን፡ ከእግዚአብሔር ጋር አስታርቄ፡ ከዘላለም ጥፋት ያዳንኋችሁ በመኾኔ ነው፤

- ልጄ ወዳጄ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ ከእኔ በለበሰው ፍጹም ሰውነቱ በተቀበለው፡ ሕማማተ-መስቀሉና ጽዋ-ሞቱ፡ ዘለዓለማዊዉን ሰላም፡ በድል አድራጊነት ያስገኘላችሁ በመኾኑ ነው፤

- ውድ ልጆቼ ስለኾናችሁ፡ የቀደሙት ወገኖቻችሁ፡ እንደእናንተ እንደዛሬዎቹ፡ የምክርና የማስጠንቀቂያ ቃሌን ለመስማት ባለመፈለጋቸው፡ ባለፉት ዘመናት ሲደርስባቸው የነበረውን፡ ያን የመሰለው አሠቃቂ ጥፋት፡ ዛሬ ደግሞ፡ በእናንተ ላይ እያንዣበበ፥ እየደረሰም ስላየሁት ነው፤

- ብትሰሙኝም፥ ባትሰሙኝም፡ ለእናንተ ልጆቼ ካለኝ፡ በርኅራኄዬና በምሕረቴ ከተመላው፡ ከነፍሳዊው፥ ከሥጋዊውና ከመንፈሳዊው የወላጅነት ፍቅሬ የተነሣ፡ ዝም ብዬ መመልከቱ አላስችል ስላለኝ ነው።

አዎን! እኔማ፡ እናንተ፡ በሰውነት፡ ለዘለዓለም፡ በመልካም ሕያዋን ኾናችሁ ትኖሩበት ዘንድ፡ አስቀድሜ፡ ይህን ፍጹም ያማረና የተሟላ ፍጥረተ-ዓለም፡ በጌታዬ በእግዚአብሔር አብና በልጄ በእግዚአብሔር ወልድ፥ በሕይወቴ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም ተዋሕዶ ያዘጋጀሁላችሁ፡ ፈጣሪያችሁ ነኝ። አዎን! እናንተን፡ በወንድነትና በሴትነት ጾታዎች፡ በመልካችን የፈጠርናችሁና ከእኛ፡ ከመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ፡ እንደአንዳችን ለመኾን የበቃችሁበትን፥ የገናናው ክብራችን ተሳታፊዎች ትኾኑ ዘንድ፡ የምንነት አካላችንን አጐናጽፈንና የማንነት ባሕርያችንን አቀዳጅተን ያስገኘናችሁ ነን።

እንዲህ፡ ለእናንተ ስንል፡ በእግዚአብሔር አብ'ነትና በእግዚአብሔር እም'ነት፥ በእግዚአብሔር ወልድነትና በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስነት፥ በመጨረሻ፡ በድንግል ማርያም የሴትነት ጾታና በኢየሱስ መሲሕ የወንድነት ጾታ፡ የእናንተ አድርገን በሰጠናችሁ፡ በሰውነት አካልና ባሕርይ ሳይቀር፡ በዚህ "እኔነት" እና "እኛነት"፡ ለፍጥረታችን የተገለጽን ነን።

ከዚህ የተነሣ፡ መልካሙና ቸሩ ፈጣሪያችሁ ብቻ ሳልኾን፥ የዘለዓለም አባታችሁና እናታችሁ፥ ካህናችሁና መቅደሳችሁ፥ ንጉሣችሁና ንግሥታችሁ፥ አገራችሁና ነፃነታችሁ፥ ሃይማኖታችሁና መንግሥታችሁ የኾንሁት፡ እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝ።

ጥንቱኑ፡ በዚህ ኹኔታ የፈጠርናችሁ እኛ፡ የቀድሞዎቹም ኾኑ የኋለኞቹ ወገኖቻችሁና እናንተ ጭምር፡ ያማሰናችሁትን [ያበላሻችሁትን] እና ያቃወሳችሁትን፥ ያጣመማችሁትንና ያጠፋችሁትን፥ ያሳደፋችሁትንና ያረከሳችሁትን ኹሉ፡ ማንነታችሁንና ምንነታችሁን ሳይቀር፡ በድንግል ማርያም የትስብእት መድኃኒትነቱ እና በኢየሱስ መሲሕ የትስብእት ቤዛነቱ፡ አድሰንና አስተካክለን፥ አቃንተንና አልምተን፥ አንጽተንና ቀድሰን፥ ወደቀደመው ድንግል አካልነቱና ንጽሓ ባሕርይነቱ መለስነው!

<u>እኛ፡ እናንተን፡ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችንን፡ እንዲህ አድርገን፡ ለእኔነትና ለእኛነት ያበቃናችሁ እኮ፡ በዘለዓለማዊነት በሠራነው ዓለምና ሥርዓት፡ እኛን መስላችሁ፡ በፍጹሙ መልካም ሕይወት እንድትኖሩ እንጂ፡ ከሥጋዊው አእምሮአችሁ ከፈለቀው፡ ከዚህ የተሳሳተ እምነታችሁና ክፉ አስተሳሰባችሁ የተነሣ፡ ይኸው አኹን እንደምታዩት፡ ፍጻሜው፡ "ሞትና ዕልቂት" ለኾነው ህልውና፡ እየራሳችሁን፡ እንድታዋርዱና እንድትዳርጉ አልነበረም፤ አይደለምም።</u>

## ስለእግዚአብሔር እውነትና ስለመንግሥቱ የሚነገረውን ቃል፡ የሚሰማው ሰብአዊው ጆሮ፡ የትኛው ነው?

ይህን ቃሌን፡ ልትሰሙ የምትችሉበትን ጆሮ የምታገኙት፡ እስካኹንና አኹንም ከምትኖሩበትና ከምትከተሉት፡ ከሥጋዊው የሰውነት አካላችሁና ባሕርያችሁ አይደለም።

በዚህ በምድራዊው ሕይወታችሁ ሙሉ፡ እናንተ እየሠራችሁበት የኖራችሁበትና አኹንም እየተጠቀማችሁበት ያለው፡ ከሦስቱ፡ የነፍስና የሥጋ፥ የመንፈስም፡ የሰውነት አካላታችሁና ባሕርያታችሁ መካከል፡ የትኛው እንደኾነ ታውቃላችሁ?

አታውቁም። ብታውቁትማ ኖሮ፡ እስከዛሬ፡ እየተላለቃችሁ ስትጓዙበት ከኖራችሁበትና መቆሚያ ከሌለው የጦርነት ጥርጊያ ጐዳና ተርፋችሁ፡ ዛሬ የቀራችሁት ደግሞ፡ እየራሳችሁን ለመጨረሻው ዕልቂት በማዘጋጀት፡ አኹን ካላችሁበት የጥፋት አፋፍ ላይ አትደርሱም ነበር።

ለእናንተ ልጆቼ ባለኝ፡ በእናትነት ርኅራኄዬና ምሕረቴ የማሰማችሁን፡ ይህን ቃሌን፡ ልታዳምጡ የምትችሉበት ጆሮ፡ ይህ አኹን የምትኖሩበት፡ የሥጋዊው የሰውነት አካላችሁና ባሕርያችሁ አባል የኾነው ግዙፉ መስሚያችሁ አይደለም።

በዚሁ፡ በሥጋዊው ጆሮአችሁ የሰማችሁት ነገር ኹሉማ፡ ከእኔና ከመንግሥቴ፡ ፈጽማችሁ ተለይታችሁ፡ የእየራሳችሁን ሰብአዊ መንግሥት በማቋቋም፡ እስከዛሬ፡ በክፉው የምኞት እሳት እየተቃጠላችሁ፡ እንዲህ፡ ከሞትና ከዕልቂት በስተቀር፡ በመልካም ልትኖሩት የምትፈልጉትን የእየራሳችሁን የምትሓት ሕይወት እንኳ ማግኘት ሳትችሉ የቀራችሁበት መኾኑን፡ ይኸው እያረጋገጣችሁት ነው።

ስለዚህ፡ ከሦስቱ የሰውነት አካላታችሁና ባሕርያታችሁ መካከል፡ በዚህ በምድራዊው ሕይወታችሁ ሙሉ፡ እናንተ እየተጠቀማችሁበት ያለው ክፍል፡ ይህን ዓይነቱን የእግዚአብሔርን እውነት፡ ለመስማትም፥ ለማየትም፥ ለማስተዋልም እንዲያስችላችሁ የሰጠናችሁን፡ መንፈሳዊውን የሰውነት አካልና ባሕርይ የሚያስቀድም፥ ወይም፡ የሚጨምር ሳይኾን፡ ሥጋዊውን አካልና ባሕርይ ብቻ ብቻ የተከተለ ስለኾነ፡ ይኼን፡ እኔ፡ አኹን የምነግራችሁን፡ የእግዚአብሔርን እውነታ፡ እንዴት መስማትና ማየት፣ ማስተዋልም ትችላላችሁ? አትችሉም።

ነገር ግን፡ ይህን ቃሌን፡ ልትሰሙ የምትችሉበት ጆሮ፡ ቀደም ብዬ እንደገለጥሁላችሁ፡ ሥጋዊውን ጭምር፡ በንስሓ አስተካክሎና መልሶ አካትቶ፡ ለመልካሙ ሕይወት የሚያበቃችሁ፡ የመንፈሳዊው የሰውነት አካላችሁና ባሕርያችሁ አባል የኾነው መስሚያችሁ ብቻ ነው። በዚሁ፡ በአንዱ፡ በመንፈሳዊው አካላችሁና ባሕርያችሁ፡ የቀሩት ኹለቱ፡ የነፍስና የሥጋ አካላታችሁና ባሕርያታችሁ ሲዋሓዱ፡ በዚህ ጊዜ፡ በዚሁ ሰውነታችሁ፡ በዚሁ ምድራዊ ዓለማችሁ ላይ፡ እንዲህ እንዳኹኑ፡ በሥጋ ህልውና እያላችሁ፡ ክፋትና ኃጢአት፥ ሞትና ዕልቂት የሌለበትን፡ ገነታዊዉን የሰላም ሕይወት፡ በፍጹም ተድላ ደስታ፡ በዘለዓለማዊነት የምትኖሩ ትኾናላችሁ።

አዎን! በዚሁ ምድራዊ ዓለማችሁ፡ እንዲህ እንዳኹኑ፡ በሥጋ ህልውና እያላችሁ፡ ልታገኙት ያልቻላችሁትን፥ ነገር ግን፡ ሞትና ዕልቂት የሌለበትን፡ መልካሙን የሰላም ሕይወት፡ በፍጹም ተድላ ደስታ፥ በጊዜያዊነት ሳይኾን፡ በዘለዓለማዊነት፡ እንድትኖሩት የሚያደርጋችሁን ቃሌን የምትሰሙበትን ጆሮ የምታገኙት፡ ከሰውነታችሁ መንፈሳዊ አካላችሁና ባሕርያችሁ ብቻ ነውና፡ እርሱን፡ በብረት ኳንንቸር ቆልፋችሁበት፡ ከደበቃችሁበት ውሳጣዊ ሰውነታችሁ አውጡትና ተጠቀሙበት! ጣፋጭ ፍሬውን፡ በቅጽበት አግኝታችሁ፡ ትመገቡታላችሁና።

## ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ከምታደርገው በጎ ጋር፡ ሰብአውያን መንግሥታት የሚያደርጉት፡ ሊነጻጸር አይችልም።

ቀድሞ፡ አይሁድ፡ በነቢዩ ሳሙኤል ዘመን እንዳደረጉት፡ ታዲያ! ዛሬም እናንተ፡ በእኔ፡ በኢትዮጵያ ስም እየተጠራች ያለችውን፡ ይህችኑ፡ የእኛን እግዚአብሔራዊት መንግሥት፡ ንቃችሁና "አንፈልጋትም!" ብላችሁ፡ በራሳችሁ ሥጋዊ ፍልስፍናችሁ ያቋቋማችኋቸው ሰብአውያን መንግሥቶቻችሁ፡ ምን እያደረጉባችሁ እንደኾኑ አታዩምን?

እነዚህ ሰብአውያን መንግሥቶቻችሁ፡ ምን አደረጉላችሁ? ምን አስገኙላችሁ? ምንስ አተረፉላችሁ? እነርሱው ለቀፈቀፉትና ላመጡት ጠንቀኛ መከራ፥ እየራሳቸውን እየሠወሩ፡ እናንተን፡ ምስኪኖች ልጆቻችንን ግን፡ አጋልጠውና አሳልፈው መስጠታቸውን አትመለከቱምን? (፩ሳሙ. ፰።)

*የእናንተ ሰብአውያን መንግሥቶቻችሁ፡ ያደረጉላችሁ፥ ያስገኙላችሁና ያተረፉላችሁ፡ ፍጻሜው፡ ምን ኾኖ ተገኘ? ፍሬውስ ምን ዓይነት ኾነ? የኾነውማ! ኹሉም ዓይነት፡ የፍጥረት አካልና ባሕርይ፡ በመልካሙ የዘለዓለም ሕይወት መኖሩን ይቀጥል ዘንድ፡ በእኛዪቱ* **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** *በኩል የተደረገውን፡ በጎ ዝግጅት ኹሉ በመፃረር፡ እነዚሁ ሰብአውያን መንግሥቶቻችሁ፡ ያን፡ መለኮታዊና ሕያው፥ ፍጥረታዊና ዘለዓለማዊ የኾነ ዝግጅታችንን፡ በማፈራረስ ብቻ ሳይወሰኑ፡ በእርሱ ቦታ፡ ሰብአዊና ምውት፥ ሓሳዊና ጊዜያዊ የኾነ ድርጅታቸውን፡ "መንግሥት" ብለው ማቋቋማቸው ነው።*

*በዚህ የድፍረት አድራጎታቸው፡ ለሰማዩና ለምድራዊው ፍጥረታተ-ዓለማታችን ህልውናና ምግብና፡ ባለቤት ኾና ትመራና ታስተዳደር ዘንድ፡ በእኛ በቅድስት ሥላሴነት አምሳል፡ ሦስት የአገልግሎት ዘርፎች ያሏት ኾና፡ በአንዲት አካልነት የመሠረትናትን* ***<u>ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችንን፡</u>*** *እንደሌለች መቍጠራቸውን፡ በእምነታቸውና በምግባራቸው በማረጋገጥ አሳይተዋል።*

*ይኸ ብቻ አይደለም፤ ቀደም ብዬ እንደገለጥሁላችሁ፡ የአንዲት አካልነትና የሦስት ባሕርይነት አቋሚንና ሥርዓቷን ጭምር፡ "ሥጋዊና መንፈሳዊ"፥ "ዓለማዊና ሃይማኖታዊ፥ "ቤተ-ክህነትና ቤተ-ምልክና"* [Church and State] *በሚል የአገዛዝ ፈሊጣቸው፡* ***<u>አንዲት</u>*** *<u>የኾነችውን፡</u> ይህችኑ፡* ***<u>ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችንን፡</u>*** *በምቅዋመ-ሕጋቸው፡ ከኹለት በመክፈላቸው፡ ይህንኑ፡ የድፍረት ድርጊታቸውን፡ በበለጠ ምስክርነት አጽንተውታል።*

*እኛ፡ እንዲህ አድርገን፡ በምሥጢረ ተዋሕዶ ጸጋና በረከት፡ አስማምተንና አንድ አድርገን፡ ለፍጥረታችን የመሠረትነውን፡ መልካሙን ግለሰባዊና ኅብረተሰባዊ የህልውና ሥርዓት፡ የእናንተ ሰብአውያን መንግሥቶቻችሁ፡* **"ከፋፍለህ ግዛ!" በሚለው፡ ሰይጣናዊ ፍልስፍናቸው፡** *ለማቃወስ በመሞከር፡ እነሆ፡ ማብቂያ የሌለውን ጠንቀኛ ችግር ቀፍቅፈው፡ ፍጥረታችንን ሲያምሱት ይገኛሉ።*

*ከዚህ የተነሣ፡ በይበልጥ፡ በሰብአውያን ፍጡሮቻችን መካከል፡ ይኸው፡ ሲካኼድ የሚታየውን፡ በጾታና በሰብእና፥ በዘርና በጐሣ፥ በመልክና በቀለም፥ በእምነትና በዕውቀት፥ በልደትና በሀብት፥ በሥልጣንና በአስተዳደር፥ በመሳሰለው ኹሉ፡ መራራውን የእርስ በርስ መለያየትንና መከፋፈልን፥ መከፋፋትንና መበላለጥን፥ መበዳደልንና መናናቅን፥ መበዛበዝንና መጨቋቈንን፥ መጠላላትንና መጨካከንን፥ ደም መፋሰስንና መጋደልን፥ ጭቆናንና ስደትን፥ ረሀብንና በሽታን፥ ማፈራረስንና ማውደምን፥ በመጨረሻም፡ ሞትንና ይኸው እየደረሰባችሁ ያለውን አሠቃቂ ዕልቂት ያስከተለባችሁን፡ መርዛም ትምህርትን ማስፋፋት፥ ክፉ ባህልንም መትከል ኾነ! የዚህም ውጤት፡ አኹን፡ በገሃድ እየተፈጸመ ባለው፡ በአጠቃላዩ የህልውና ቀውስ እየታየ ነው። ይህን እውነታ ለማስተባበል፡ ከቶ የሚቻል አይደለም።*

ታዲያ! እኒህ ተማምናችሁባቸው የመሠረታችኋቸው መንግሥቶቻችሁ፡ ከዚህ ኹሉ የመከራና የሥቃይ ዐዘቅት፡ የታል ያወጧችሁና ያዳኗችሁ! ለምንስ አያወጧችሁም? አያድኗችሁምም? ይኼ በሥጋዊ ጥበባችሁና ብልሃታችሁ፡ ተመካክራችሁ የምትደነግጉት ሕጋችሁና የምትመራረጡበት ሥልጣናችሁ፥ የምታቋቁሟቸው ድርጅቶቻችሁና ያከማቻችሁት፡ ወርቃችሁና ገንዘባችሁ፥ ሀብታችሁና ንብረታችሁ፥ የጥፋት መሣሪያችሁና የሠራዊት ኃይላችሁ ኹሉ፡ ለመቼ ሊኾናችሁ ነው? ለምንስ፡ ከዚህ ኹሉ ጥፋትና ዕልቂት አያድናችሁም?

እንግዴህ፡ እየተካኼደ ካለውና በተለያየ መልክና ይዘት እየከበደ ከሚመጣው፡ መከራና ሥቃይ፥ ፍጅትና ዕልቂት፡ **ከእኛዪቱ፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** በቀር፡ ሊያድናችሁና ሊያተርፋችሁ፥ ሊሠውራችሁም የሚቻለው፡ ምንም ዓይነት ሰብአዊና ፍጥረታዊ ኃይል፥ ወይም፡ ማንም ሥጋዊና መንፈሳዊ ፍጡር፡ በምድርም፥ በሰማያትም እንደሌለ ልታውቁት ይገባችኋል።

እንዲያው ለመኾኑ፡ ቀደም ብዬ እንዳብራራሁላችሁ፡ ይህን ፍጥረተ-ዓለም ካለመኖር፡ ወደመኖር አምጥተንና አከናውነን፡ ካዘጋጀን በኋላ፡ እናንተን፡ ከእኛ፡ እንደአንዳችን በኾናችሁበት መልካችንና ባሕርያችን ከፈጠርናችሁ በኋላ፡ እናንተና ፍጥረቱ ኹሉ፡ እርሱን እየተነፈሳችሁ፡ በሕይወት እንድትንቀሳቀሱበት፥ በተለይ፡ እናንተ፡ ከእኛ፡ በተፈጥሮ ባገኛችሁት የዕውቀት ኃይል የሠራችሁትን የተለያየ መንኰራኵርና ሠረገላ፡ በየብስ እንድታሽከረክሩበትና በባሕር እንድትቀዝፉበት፥ በሰማይ ላይ እንድትበሩበትና በኃይል ምንጭነቱም እንድትጠቀሙበት ያስቻላችሁን፡ ነፋሱን ፈጥሮ እያነፈሰላችሁ ያለው፡ ከቶ ማነው? የትኛው ሰብአዊ መንግሥታችሁ ነው፡ ይኼን ትንግርት የፈጸመላችሁ? ይኼ የእናንተ መንግሥት ነውን? አይደለም። ታዲያ! ማነው? ይህችው፡ የእኛዋ፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** አይደለችምን? አዎን! እርስዋ ነች።

ደግሞስ፡ እናንተና ፍጥረቱ ኹሉ፡ በብርሃኑ ፀዳል፡ ኹሉን እንድታዩበትና እንድትመላለሱበት፥ እንድትሞቁትና በኃይል ምንጭነቱም እንድትጠቀሙበት ያስቻላችሁን፡ ፀሓዩን እያወጣላችሁ ያለው፡ ከቶ ማነው? ይኼ የእናንተ መንግሥት ነውን? አይደለም። ታዲያ! ማነው? ይህችው፡ የእኛዋ፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አይደለችምን?** አዎን! እርስዋ ነች።

አኹንም ደግሞ፡ ዝናሙን አዝንሞና ምንጮችን አፍልቆ፡ ዥረቱንና ወንዙን፥ ባሕሩንና ውቅያኖሱንም ኹሉ፡ በውኃ የሞላና ያጥለቀለቀ፥ እናንተና ፍጥረቱ ኹሉ፡ ጠጥታችሁ የምትረኩበትን፥ ታጥባችሁ የምትነጹበትን ጸጋ ሰጥቶ፡ በሕይወት መኖርን እንድትቀጥሉ፥ በኃይል ምንጭነቱም እንድትጠቀሙበት ያስቻላችሁን፡ ይኼን ኹሉ፡ የውኃ ሙላት እያፈሰሰላችሁ ያለው፡ ከቶ ማነው? ይኼ የእናንተ መንግሥት ነውን? አይደለም። ታዲያ! ማነው? ይህችው፡ የእኛዋ፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** አይደለችምን? አዎን! እርስዋ ነች።

እንዲህ፡ የምትኖሩባትን ምድር፡ አሳምሮና አሟልቶ፥ አዘጋጅቶና አከናውኖ፡ በዐፈርዋ ላይ፡ በተፈጥሮ የበቀለውንና በወፍ-ዘራሽነት የወደቀውን፥ በእናንተም እጅ የተዘራውን፡ ልዩ ልዩ ጥራጥሬ የሚያስገኘውን አዝርዕቱን፥ ቅጠላቅጠል የሚያስገኘውን አትክልቱን፥ እንዲሁም፡ ፍራፍሬ የሚያስገኘውን ዕፀዋቱን፡ ይኸን ኹሉ የእህል፥ የበቈልትና የዛፍ ዓይነት፡ በነፋሱ ሕያው አድርጎና አጐንቍሎ፥ በዝናምም አብቅሎ፥ ለልምላሜ የደረሰውን ቡቃያም፡ ለአበባነትና ለፍሬያማነት አብቅቶና በፀሓይ አብስሎ፥ በጠቅላላ፡ እንዲህ፡ ኹሉን አበርክቶና አትረፍርፎ፡ እየመገበ፡ በተድላ በደስታ ለመኖር ያስቻላችሁን፡ መብሉንና መጠጡን፥ ልብሱንና የኑሮ ሲሳዩን ኹሉ፡ በተፈጥሮ እያበረከተላችሁና እያቀረበላችሁ ያለው፡ ከቶ ማነው? ይኼ የእናንተ መንግሥት ነውን? አይደለም። ታዲያ! ማነው? ይህችው፡ የእኛዋ፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** አይደለችምን? አዎን! እርስዋ ነች።

ይኸን ኹሉ፡ ያልተቋረጠና ምንጊዜም የማይቋረጥ፡ ፍጹም መልካሙንና እጅግ የተትረፈረፈውን በረከት፡ እያደረገላችሁ ያለው፡ የትኛው መንግሥታችሁ ነው? እስኪ ንገሩኝ!? ከየትኛዎቹም ሰብአውያን መንግሥቶቻችሁ መካከል፡ ይህን ያደረገላችሁ፥ ወይም፡ "ሊያደርግላችሁ ይቻለዋል!" ተብሎ ሊታሰብ የሚቃጣ፡ አንድ መንግሥት እንኳ አይኖርም፤ የለምና። ሊኖርም የሚቻል አይደለምና።

## ሥነ ፍጥረት፡
## ስትገልጥ የኖረችውን ምሥጢሯን አለማወቅ ይጎዳል።

ቀደም ብዬ የዘረዘርሁላችሁን፡ ያን ኹሉ፡ ያልተቋረጠና ምንጊዜም የማይቋረጥ፡ ፍጹም መልካም የኾነውንና እጅግ የተትረፈረፈውን የተፈጥሮ ጸጋ፡ በሥነ-ፍጥረት ሠሪነቷና ባለቤትነቷ፡ አዘጋጅታና አከናውና፡ መጠን በሌለው ቸርነቷና በሰፊው ልግሥናዋ፡ እንዲህ እንደምታዩት፡ እስካኹን፡ ስታበረክትላችሁ የኖረችው፥ ዛሬም፡ እያበረከተችላችሁ ያለችው፥ ወደፊትም፡ ለዘለዓለም የምታበረክትላችሁ፡ ይህችው፡ የእኛዪቱ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ናት።**

በዚህ አንጻር ደግሞ፡ እናንተ፡ ቀድሞም ኾነ፡ ዛሬ፡ በሃይማኖተ-ቢስነትና በሃይማኖታዊ ግብዝነት፡ ያለኀፍረትና ያለይሉኝታ፥ በድፍረትና በማናለብኝነት፡ በዚህችው፡ በእኛዪቱ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን** ላይ እያካኼዳችሁት ያለውን የመሰለ፡ ፀረ-እግዚአብሔር ተግባርን በምትፈጽሙበት ጊዜያት ኹሉ፡ ስለሚደርስባችሁ የማይቀር ፍዳ፡ ፈጽማችሁ ያላወቃችሁትና ያልተገነዘባችሁት፥ ነገር ግን፡ ልታውቁትና ልትገነዘቡት በብርቱ የሚያስፈልጋችሁና የሚገባችሁ፥ ይኹን እንጂ፡ ልታውቁትና ልትገነዘቡት ያልቻላችሁትና ያልፈለጋችሁት፡ አንድ ዓቢይ ቋሚ እውነታ አለ።

እርሱንም፡ በእውነት ዐውቃችሁትና ተገንዝባችሁት ቢኾን ኖሮ፡ እስካኹን፡ የደረሰባችሁ ክፉ ነገር ኹሉ፡ ትምህርትና መቀጣጫ ኾኗችሁ፡ ከዚሁ፡ ከተደጋጋሚው ክፉ ነገር ኹሉ ድናችሁ፡ በመልካም ለመኖር፡ በእጅጉ ልትጠቀሙበት በቻላችሁ ነበር፤ እናንተ ግን፡ እየራሳችሁን፡ በግልም ኾነ በኅብረት፡ በንስሓ ለማስተካከል ፈቃደኞች ባለመኾናችሁ፥ እንዲያውም፡ በዚሁ ዓመፀኝነታችሁ፡ በበለጠ ጸንታችሁ መቀጠልን፡ እንደጀብደኝነት ቈጥራችሁ፡ ሙያ በማድረጋችሁ፡ ይኸው፡ በእየራሳችሁ ላይ፡ ከባድ ጉዳትን እያስከተላችሁ ትገኛላችሁ።

ያ፡ አንድ ዓቢይ ቋሚ እውነታ ያልኋችሁ፡ ምን እንደኾነ ላስታውቃችሁ? እኛ፡ ይህን ዓለም፡ ከአለመኖር ወደመኖር፡ በእውንነትና በግዝፈት፡ ወደምድራዊው ህላዌ ላመጣነው ፍጥረታችን መልካም ሕይወት፡ የማይናወጽና ዘለዓለማዊ መመሪያ ኾኖ እንዲያገለግል የመሠረትነው፡ መለኮታዊ ሥርዓት ነው። ይህ ፍጹም ሥርዓት፡ በሥጋና በነፍስ፥ በመንፈስም፡ መልካም ለኾነው አስተሳሰብ፥ አነጋገርና አድራጎት ኹሉ፡ መልካሙን ዋጋ፡ አብዝቶ የሚከፍል ሲኾን፡ ልክ፡ በዚሁ መልክና ይዘት፡ ክፉ ለኾነው አስተሳሰብ፥ አነጋገርና አድራጎት ኹሉ ደግሞ፡ ክፉውን ዋጋ፡ አሟልቶ የሚከፍል ነው።

ሥነ-ፍጥረት፡ ይህን መለኮታዊ ሥርዓቷን፡ በማይዛባው ትክክለኛነቷ፡ በነፍስና በሥጋ፥ በመንፈስም፡ እንዲህ፡ እውን አድርጋ፡ በተግባር ላይ በምታውልበት ጊዜ፡ እናንተ፡ በተፃራሪ አሳብ ተነሣሥታችሁ፡ ይህን የተቀደሰ ሥጋዊና ነፍሳዊ፥ መንፈሳዊም ሥርዓቷን፡ ልታቃውሱባት በምትሞክሩበት ጊዜያት ኹሉ፡ እርሷም በበኲሏ፡ የሰፊ ትዕግሥቷ ጽዋዋ ሞልቶ መፍሰስ ሲጀምር፡ ራሷን ለመጠበቅና መልሳ ለማስተካከል፥ አጥፊውንም ለመቅጣት፡ የታወቀ የቍጣ ጅራፏን አውጥታና ሠይፏን መዝዛ፡ ተገቢ ፍርዷን፡ በየመልኩ ትፈጽማለች።

አያችሁ ልጆቼ! ሥነ-ፍጥረት፡ ባለፉት ዘመናት፡ ስታደርገው እንደኖረችው ኹሉ፡ በአኹኑ ጊዜም፡ ይህን ኹሉ የቁጣ መቅሠፍቶቿን፡ በእናንተ ላይ፡ እንዲህ፡ በተከታታይ የምታወርድባችሁና እያወረደችባችሁ ያለችው፡ ለምን እንደኾነ፡ እውነታውን ዐወቃችሁት አይደለምን? አዎን! ዐወቃችሁት። እያያችሁትም ነው። በሥጋዊውና በነፍሳዊው፥ በመንፈሳዊውም አስተሳሰባችሁና አነጋገራችሁ፥ አድራጎታችሁም ኹሉ፡ የእርሷ፡ የሥነ-ፍጥረት መልካም ከኾነው፡ ከቅዱሱ መለኮታዊ ሥርዓቷ ውጪና የተለየ የኾነ፡ ክፉ አስተሳሰብና አነጋገር፥ አድራጎትም፡ ከእናንተ መንጭቶ ሲገኝ፤ ውጤቱ፡ በዚሁ የሥነ-ፍጥረት መለኮታዊ ሥርዓታችን መሠረት፡ ይኸ፡ አኹን፡ በእናንተ ላይ እየተፈጸመ ያለውን የመሰለ፡ የተፈጥሮ ቍጣና የመቅሠፍት ውርጂብኝ መኾኑ አይጠረጠርም።

ይህ በመኾኑ፡ ምን ያስደንቃል? ምንስ ያስገርማል? አያስደንቅም፤ አያስገርምም። ምክንያቱን፡ በመጠኑ ላስታውቃችሁ።

እናንተ፡-

-እኛ ያስገኘናትን፡ ራሷን ፍጥረትን፥ ሥነ-ፍጥረትንም፡ በራሷ እንደተገኘች፥ ወይም፡ ፈጣሪና ባለቤት እንደሌላት በመቍጠርና የእናንተ፡ የራሳችሁ እንደኾነች በማስመሰል፥ የእኛን የእግዚአብሔርን መኖርና ፈጣሪነት እስከመካድ ደረሳችሁ፤

-ይኼ ብቻ ሳይኾን፡ የእየራሳችሁን፡ በእኛ መልክ የመፈጠራችሁን ክብር ሳይቀር፡ ፈጽሞ አዋርዳችሁ፡ ከዝንጀሮ የዘር ሓረግ እንደተወለዳችሁ አመናችሁ፤

-ይልቁንም፡ አስቀድመን ባዘጋጀንላችሁ፡ በዚች የገነት ዓለማችሁ ላይ፡ በእኛ መልክና አርአያነት፡ በሠራንላችሁ የጋብቻ ሥርዓት፡ ተጋብታችሁና ተዋልዳችሁ በመበርከት፡ በዝታችሁ፥ ከፍጡሮቻችን ኹሉ፡ የተለየ አድርገን ባጐናፀፍናችሁና ባቀዳጀናችሁም መልካም ሕይወት፡ ተደስታችሁ ትኖሩ ዘንድ፡ የተፈጠራችሁበትን፡ ይህን፡ የወንድነትና የሴትነት ጾታችሁን፡ ኢተፈጥሮአዊና ኢሃይማኖታዊ በኾነ አስነዋሪ ኹነታ ለወጣችሁ፤ እየራሳችሁንም፡ ለግብረ-ሰዶም ክፉ ልማድና የኃጢአት ድርጊት ዳረጋችሁ፤ ይህንኑም፡ ክፉ ልማድና የኃጢአት ድርጊት፡ እርስ በርሳችሁ፡ በእየገመናችሁ ስትፈጽሙት መኖራችሁ አንሶ፡ አኹን ደግሞ፡ የይፋ ተቀባይነትና ዕውቅና ያገኘ መኾኑን በማረጋገጥ፡ በየአገሮቻችሁ፡ ሰብአውያን መንግሥቶቻችሁ አማካይነት፡ ሕጋዊ ተፈጻሚነት እንዲኖረው ዐሳወጃችሁ፤

-እነዚህን ስሑታንና ሰይጣናውያን የኾኑ እምነታችሁንና ግብራችሁን፡ እንደመልካም ዕውቀትና ሙያ ቆጥራችሁ፡ ወገኖቻችሁ ለኾኑት ሕዝቦቻችሁ፡ በብዙኃን መገናኛዎቻችሁ አማካይነት፥ ለሕፃናት ለልጆቻችሁም ሳይቀር፡ በእየትምህርት ቤቶቻችሁ አማካይነት፡ ማስተማርንና ማሠራጨትን ብቻ ሳይኾን፡ በመንግሥታት መሪዎቻችሁ አማካይነት፡ ለሌሎች ሰብአውያን ፍጡሮቻችን ጭምር፡ እንደዋና ተልእኳችሁ አድርጋችሁ ማስተላልፍን፡ "ሥራዬ" ብላችሁ፡ ይኸው፡ ተያያዛችሁታል፤

-ከዚህም በቀር፡ ለአዲስ ዓመታችሁ መግቢያና ለዘመን መለወጫ የዐውደ ዓመት በዓላችሁ ማክበሪያ የኾነውን፡ የእኔንና የልጄ የወዳጄ፡ የኢየሱስ መሲሕን፡ የልደታት ዕለት፡ <u>ከመስከረም ፩ ቀን፡</u> የተለያዩ የጣዖታትና የርኩሳን መናፍስት፥ የሓሳውያን አማልክትም መመለኪያ የኾኑ ቀኖችን ወደያዘችው፡ ወደDecember (ዲሴምበር= ታኅሣሥ) ወርና ወደJanuary 1 (ጃኗሪ= ጥር ፩ ቀን) በመለወጥ፡ በድፍረትና በማናለብኝነት የምታደርጉትን፥ እያደረጋችሁ ያላችሁትንም ፀረ-እግዚአብሔር ሥራ፡ እነሆ፡ ቀጥላችሁበታል።

ታዲያ! እናንተ፡ በእኛ ላይ፡ ይህን ኹሉ ክህደትና ዓመፅ፥ በደልና ክፋት፡ በባሰና በተጠናከረ ይዞታ መፈጸማችሁን፥ የዚህም ጥፋታችሁ ጽዋ ሞልቶ መፍሰሱን ስትመለከት፡ <u>ሥነ-ፍጥረት፡</u> ምን ታድርግ? እንዴትስ ዝም ትበል? ከእኛ፡ በፍጹምነት ተከውና በተሰጣት፡ በቅዱሱ መለኮታዊ ሥርዓቷ መሠረት፡ ተገቢና አስፈላጊ የኾነውን፥ ፍትሕ-ርትዕንም የተመላ የቅጣት ግዳጇን፡ እንዲህ ትፈጽማለች።

በተለይ፡ "ክርስቲያን ነኝ!" የሚለው፡ የግብዙ ዓለም ወገኖች የኾናችሁት፡ እናንተ ልጆቼ፡ አኹን፡ ከዚህ ቀደም ብዬ ያወሳሁትን፡ የዘመን መለወጫችሁ የኾነውን፡ የእኔንና የልጄ የወዳጄን፡ አንዱን የልደት ጣምራ በዓል፡ ለኹለት ከፍላችሁ የምታከብሩት፡ መቼና እንዴት እንደኾነ፡ በአንክሮ፥ በተዘክሮ ተመልከቱት!

እናንተ፡ እነዚህን የተከፋፈሉ በዓሎቻችሁን የምታከብሯቸው፡ እናንተ ጭምር ትደሰቱበት ዘንድ፡ እኛ አስቀድመን፡ አመቻችተን ባሰናዳነው፥ የፍጥረተ-ዓለሙ አካላት የኾኑት፡ ኅዋዉና ምድሪቱ ኹሉ፡ መልካሙንና ተስማሚውን፡ የአየርና የሙቀት ጠባያት ብቻ ሳይኾን፡ ለጥቢው ወራት የተፈጥሮ ጸጋዎች በኾኑት፡ በፀሓይ ለስላሳ ብርሃን ተመልተው፥ እርሱንም፡ በምልዓት ተጐናፅፈው፥ በሚያብረቀርቁ የሰማይ ከዋክብትና በተለያዩ ቀለማት የተንቈጠቈጡ አበቦችን ተላብሰውና በእነርሱ ተሸልመው በሚያሸበርቁበት፡ በትክክለኛ ዕለቱ፡ በመስከረም ፩ ቀን፡ አይደለም።

ነገር ግን፡ እነዚህኑ የተከፋፈሉ በዓሎቻችሁን የምታከብሯቸው፡ እኛ፡ የሠራነውን የተፈጥሮ ሥርዓት፡ በፀረ-እግዚአብሔርነታችሁ፡ ኾን ብላችሁ ለማፍረስ በመነሣሣት፡ ይህንኑ፡ መስከረም ፩ ቀንነቱን፡ በሓሰት አቃውሳችሁና ለውጣችሁ፥ *"የኢየሱስ ክርስቶስ፡ የልደቱና የአዲስ ዓመት መባቻ (መግቢያ) ቀኖች ናቸው!"* ብላችሁ፡ በየዓመቱ፡ ሰው ብቻ ሳይኾን፡ እንስሳትና አራዊት፥ አዕዋፋትና አዝርዕት፥ አትክልትና ዕፀዋት ሳይቀሩ፡ ከበረዶው ቅዝቃዜ፥ ውሽንፍርና ምልዓት የተነሣ፡ የሥነ ፍጥረት አባል የኾነው ፍጡር ኹሉ፡ በየቤቱና በየበዓቱ፥ በየጎሬውና በየዋሻው በሚከተቱበት፡ በታኅሣሥና በጥር ወሮቻችሁ እንዲኾን አደረጋችሁ።

ስለዚህ፡ በተቃወሱት ቀናት በምታከብሯቸው፡ በእነዚህ በዓሎቻችሁ ጊዜያት ኹሉ፡ ይልቁንም፡ በዘንድሮው ዓመት፡ በእየአንዳንዳችሁና በኹላችሁም ላይ፥ በባሰ ኹኔታም፡ አውሮጳዊት በኾነችው፡ በእንግሊዝ አገር፥ በአሜሪካና በአውስትራሊያ ክፍላተ-ዓለምም የደረሰው፡ አስፈሪ የሰደድ ቃጠሎና አውዳሚ ዐውሎ ነፋስ፥ አጥለቅላቂ የዝናም ማዕበልና የውኃ ሙላት፥ አስደንጋጩም የመሬት መደርመስ፡ ሊፈጸም፡ አስፈላጊና ግድ ኾነ። የዚህ የግዙፉ ዓለም ሥነ-ፍጥረት መሠረታውያን ንጥረ-ነገሮች የኾኑት አራቱ አካላትና ባሕርያት፡ በየግላቸውም፥ በኅብረታቸውም ተቆጡ፤ ቁጣቸውንም ገለጹ፤ የቁጣ ሠይፋቸውን መዘዙ፤ የፀሓይዋ ቁጣ፡ በእሳቱ፥ የአየሩ ቁጣ፡ በዐውሎ ነፋሱ፥ የውኃው ቁጣ፡ በአጥለቅላቂ ጎርፉ፥ የመሬቷ ቁጣ፡ በነውጥ መደርመሱ እየተከሠተና እየተፈጸመ ነው።

በታላቅ ደስታና ሓሤት፥ ሰላምና ፍቅር፥ ዕረፍትና መዝናናት በአንድነት ሊከበሩ በሚገባቸው፡ በእነዚህ የዕለታት በዓላት ቀኖች፡ የሥነ-ፍጥረት ቍጣና መቅሠፍታዊው ቅጣት፡ እንዲህ፡ በዚህ መልኩና ይዘቱ፡ መከሠቱና መፈጸሙ፡ የሚያስገርም፥ የሚያስደንቅምም አይኾንም።

ይህ፡ የሥነ-ፍጥረት፡ የግዳጇ አፈጻጸም፡ በዐዋጇ መግቢያ ላይ የጠቃቀስሁላችሁን፡ የተፈጥሮ ቍጣዎች በኾኑት፡ በፀሓይ ትኵሳትና በሰደድ እሳት ቃጠሎዎች፥ በዐውሎ ነፋሳትና  በከባድ ዝናማት፥ በውኃ ሙላቶች ማጥለቅለቅና በበረዶ ውሽንፍር፥ በመሬት መደርመስና መንቀጥቀጥ፥ በድርቀትና በቸነፈርም አስፈሪ ማዕበላትና ደምሳሽ ኃይላት ምክንያት፡ እየወረደ ያለውን፥

ደግሞም፡ ታላላቅ የእርስ በርስ ፍጅታችሁንና ዕልቂታችሁን፥ በማይነጥፍ ጠባችሁና ጦርነታችሁ ሰበብ የቀጠለውን፡ ደም መፋሰሳችሁንና ሥቃያችሁን፥ የኅብረተሰብ ነውጣችሁንና ስደታችሁን፥ ረሀባችሁንና ደዌያችሁን የመሰለ፡ ተፈጥሮአዊዉንና ሰው-ሠራሹን የቁጣ መቅሠፍት ያጠቃልላል።

እናንተ ግን፡ በተለይም፡ "ክርስቲያን ነኝ!" የሚለው፡ ግብዙ ዓለም፡ እውነታው፡ ይህ መኾኑን እያወቃችሁ፥ ወይም፡ ብታውቁትም እንኳ፡ በእኛ ላይ ካላችሁ ጥላቻና ተቃውሞ የተነሣ፡ "ይህ ኹሉ ሰው-ሠራሹና ተፈጥሮአዊው መዓትና መቅሠፍት የደረሰብን፥ እየደረሰብንም ያለው፡ በዚህ ምክንያት ነው!" አትሉም። ወይም፡ "ይህ የሚኾነው፥ ወይም፡ እየኾነ ያለው፡ ለምንድር ነው?" ብላችሁም እንኳ አትጠይቁም፤ ልትጠይቁም አትፈልጉም። ምክንያቱም፡ ጥያቄያችሁ፥ መልሱም፡ እንዳለ በሙሉ፡ ወደእኛ መርቶ እንደሚያደርሳችሁ ስለምታውቁት ነው። ይህ እንዲኾን ደግሞ አትፈልጉም። ወደእኛ ከደረሳችሁ፡ መልሱ፡ ምን እንደሚኾን ታውቁታላችሁና፤ ያንንም፡ በፀረ-እግዚአብሔርነታችሁ ምክንያት፡ አትፈልጉትምና።

እውነታው፡ ይህ ከኾነ፡ ታዲያ! ቀደም ብዬ የገለጽሁላችሁን፡ ያን ኹሉ፡ ያልተቋረጠና ምንጊዜም የማይቋረጥ፡ መልካም የተፈጥሮ በረከት እያደረገላችሁ ያለው፡ "ማን ነው?" ትላላችሁ? አይዟችሁ! ማንንም ሳትፈሩ፥ ይሉኝታም ሳይዛችሁ፡ እስኪ፡ እውነቱን ተናገሩ! እስኪ፡ እውነቱንም ፍረዱ!

ከቅዱሱ መንፈሳችን ከፍለን፡ በተፈጥሮ፡ የሰጠናችሁና ምንጊዜም በውስጣችሁ የማይለየው፥ እናንተ፡ "ኅሊና" የምትሉት፡ የእየራሳችሁ መንፈስ፡ ሥራችሁን ስለሚያውቅ፡ የእርሱን ትዝብትና ወቀሳ ስለፈራችሁና ስላፈራችሁ፡ እናንተ፡ እውነቱን ለመናገር እንደማትደፍሩ ዐውቃለሁ። ስለዚህ፡ በዚህ ረገድ ያለውን እውነት፡ እናንተ መናገር ካልደፈራችሁ፡ እኔ እናገርላችኋለሁና፡ ብቻ እናንተ፡ በእውነት፡ ከልብ ኾናችሁ ስሙኝ!

እንግዴህ፡ ቀደም ብዬ እንዳመለከትኋችሁ፡ የእግዚአብሔርን እውነት ለመስማት፥ ሰምቶም፡ በምግባር ለማዋል፡ ዝግጁና ፈጣን በኾነው በመንፈሳዊው ጆሮአችሁ የምታዳምጡኝ ከኾነ፡ የምላችሁ፡ ይኼ ነው፡- እየተካኼደ ካለው፥ በተለያየ መልክና ይዘትም እየከበደ ከሚመጣው መከራና ሥቃይ፥ ፍጅትና ዕልቂት፡ ልታድናችሁ፥ ልትሠውራችሁም የሚቻላት፡ ይህችው፡ እናንተ፡ በክህደትና በዓመፀኛነት፥ በአምልኮ አመንዝራነትና በሓሳዊነት፡ የናቃችኋትና ያቃለላችኋት፥ ያገለላችኋትና የተዋችኋት፡ የእኛዪቱ፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ብቻ እንደኾነች ዕወቁት!

ታማኞቹ የቅዱሱ ኪዳን ልጆቼ፡ ኢትዮጵያውያኑና ኢትዮጵያውያቱ፡ በምስጋና ጸሎታቸው፡ "ብኪ ድኅነ ዓለም! ወበወልድኪ ኮነ ሰላም! ፍጥረተ ዓለሙ፡ በአንቺ ዳነ! በልጅሽም፡ ሰላም ኾነ!" እያሉ፡ ዘወትር ከሚዘምሩልኝ፡ ከእኔ በቀር፡ አዎን! ሌላ አዳኝ፡ ከቶ የለም።

ዘለዓለማዊቷ ሕይወት፡ ለፍጥረተ-ዓለማቱ፡ ለመጨረሻው ጊዜ በተገለጠችበት፡ በዚያ የፍጻሜ ዘመን፡ ቀደም ብሎ፡ እኛ፡ "ዐዋጅ-ነጋሪ" አድርገን የላክነው፡ ታማኙ የአደራ ልጄ፡ ዮሐንስ መጥምቅ፡ "ነስሑ! እስመ ቀርበት መንግሥተ-ሰማያት።

...ለክፉዎች ሰዎች ተሠውራ የቆየችው፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ እነሆ፡ ልትገለጥ ቀርባለችና፡ ከየኃጢአታችሁ፡ በንስሓ ተመልሳችሁ፡ ተቀበሏት!"

እርሱንም ተከትሎ፡ "መጽአ እግዚእ ኢየሱስ ገሊላ፤ ወሰበከ፡ ወንጌለ መንግሥተ-እግዚአብሔር። ወይቤ፤

...ጌታ ኢየሱስ፡ የእግዚአብሔርን መንግሥት ምሥራች እየሰበከ፡ ወደገሊላ መጣ፤ እንዲህ ሲል፡-" ተብሎ የተጻፈለት፡ ልጄ ወዳጄ፡ ኢየሱስ መሲሕም፡

"በጽሓ ጊዜሁ! ወቀርበት መንግሥተ-ሰማያት! ነስሑ ወእመኑ በወንጌል!

...ለክፉዎች ሰዎች ተሠውራ የቆየችው፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ልትገለጥ እነሆ ቀረበች! አዎን! የመገለጫዋ ጊዜ፡ እነሆ ስለደረሰ፡ ከየኃጢአታችሁ፡ በንስሓ ተመልሳችሁ፡ ተቀበሏት!" ብሎ፡ ኹለቱም፡ በእኔ የሴትነት አንቀጽ፡ የሰበኳት፡ ያች መንግሥተ እግዚአብሔር፡ ይህችው፡ አኹን እያናገርኋችሁ ያለሁት፡ እኔዋ፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ነኝ።

(ማቴ. ፫፥ ፩-፪፤ ፬፥ ፲፯። ማር. ፩፥ ፲፬-፲፭።)

አዎን! ለእናንተ፡ ለሕይወታችሁና ለህልውናችሁ፥ ለጤንነታችሁና ለደኅንነታችሁ ከምታደርግላችሁ፡ ፍጹም ጥበቃና እንክብካቤ ጋር፡ ይህን ኹሉ ቸርነትና ልግሥና እያደረገችላችሁ የምታኖራችሁ፡ ይህችው፡ የእኛዪቱ፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ብቻ ናት። እናንተ፡ በእየራሳችሁና በእየወገናችሁ ያቋቋማችኋቸው፡ ሰብኣውያን መንግሥቶቻችሁ አይደሉም። ይህን ትክዳላችሁን? አትክዱም። በየአፍታው፡ በገሃድና በግዘፍ እየኾነና እየተደረገ ያለ እውነታ ነውና።

# የዐዋጅ ቃሌ፤

## ስለ"ሦስተኛው" የዓለም ጦርነታችሁ።

የዛሬ ፲፬ [ዓሥራ አራት] ዓመታት፡ በመስከረም ፩ ቀን፥ ፲፱፻፺፬ ዓመተ-ምሕረት [በፈረንጆቹ አቆጣጠር፡ በSeptember 11፣ 2001 (9/11)]፡ **"፫ኛው የዓለም ጦርነት"** ኾኖ፡ በእስላሙ ዓለምና በክርስቲያኑ ዓለም መካከል የተጀመረውን፡ ይህን፡ ግልጽ **"የሃይማኖት ጦርነት"** በሚመለከት፡ ከዚህ በፊት፡ በአገልጋዩ ልጃችን፡ በኤርምያስ አማካይነት፡ በይፋ ተላልፎና ለይፋ ምንባብ በቅቶ የቆየውን መልእክታችንን ታስታውሱታላችሁ።

አኹንም፡ ያንኑ መልእክታችንን በማዘከርና ዓላማ በማድረግ፡ ቀድሞ፡ **"ኵሎ ዘይቤለክሙ ግበሩ!" "ልጄ ወዳጄ ኢየሱስ መሲሕ የሚላችሁን ስሙት! አድርጉትም!"** ባልኋችሁ፡ ትስብእታዊ አንደበቴ፡ እነሆ፡ ዛሬ ደግሞ፡ እኔው ራሴ፡ በመንፈስ ቅዱሳዊው የዐዋጅ ቃሌ አቅርቤላችኋለሁና፡ በሚሰማው እግዚአብሔራዊውና ኢትዮጵያዊው የልጅነት ጆሮዋችሁ ስሙት! (ዮሐ. ፪፥ ፭።)

እርሱም፡ ለቅድስት ሥላሴነቴ፡ መንበረ-ጸባዖት፥ ለእግዚአብሔር አብነቴ ሙሽሪት፥ ለእግዚአብሔር ወልድነቴ እናት፥ ለእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስነቴ ሕይወት ለኾነችው፡ ለእግዚአብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ የማንነቷና የምንነቷ መገለጫ በኾነችው፡ "ኢትዮጵያ" በሚለው መለኮታዊና ዘለዓለማዊ ስያሜ የምትጠራው፡ ይህችው እግዚአብሔራዊት መንግሥታችን፡ በዐዋጅ የምታሰማችሁ መለኮታዊ ምዕዳኗ ነው።

፩. "ሦስተኛው" የምትሉት፡ የዓለም ጦርነታችሁ፡ እነሆ ተጀምሮአል። ይኼም ጦርነት፡ እስላሙ ዓለም፡ "ጂሃድ" ብሎ፡ በክርስቲያኑ ዓለም ላይ እያካኼደ ያለው፥ ክርስቲያኑም ዓለም፡ እየተከላከለ ያለው፡ የሃይማኖት ጦርነታችሁ ነው።

"ይኹን እንጂ፡ "እስላሞች ነን!" የሚሉት ጦረኞች ወገኖች፡ ሃይማኖታዊነቱን፡ "ጂሃድ" ብለው፥ ገሃድነቱን፡ በይፋ ያሳወቁ ሲኾኑ፡ "ክርስቲያኖች ነን!" የሚሉት ግን፡ ለሥጋዊው ጥቅማቸውና ዓላማቸው ሲሉ፡ እውነተኛ ምንነቱን፡ በሓሰት ሠውረው፡ በተለመደው ሸንጋይነታቸው፡ ሰለባዎች እየኾኑ ለሚወድቁት ሕዝቦቻቸው፡ በተራ "የአክራሪዎች" ውጊያ እያስመሰሉ ሲያቀርቡት ይታያል።

ይኼው ጦርነት፡ በይፋ የተጀመረው፡ ባለፈው መስከረም ፩ ቀን፥ ፲፱፻፺፬ ዓመተ-ምሕረት፥ [በፈረንጆቹ አቆጣጠር፡ በSeptember 11 (9/11), 2001] ነው። መቸም፡ መስከረም ፩ ቀን፡ ከፍጥረተ-ዓለሙ ልደት ጀምሮ፡ እስከመለኮታዊው የትስብእት ልደት ድረስ፡ አያሌ የእግዚአብሔር ድንቃድንቅ የሥነ ፍጥረት ሥራዎች የተፈጸሙባት፡ የዓመት መባቻ [መግቢያ ዕለት] መኾኗን የማያውቅ የለም።

በተለይ፡ ያች፡ የ፲፱፻፺፬ ዓመተ ምሕረቷ መስከረም ፩ ቀን ፥ [በፈረንጆቹ አቆጣጠር፡ የ2001ዋ September 11 (9/11)] ግን፡ እርሷ፡ መለኮታዊና ዕፁብ የኾነ፡ አስደንጋጭ መልእክትና ምልክትነት ያላት መኾኗን፡ አበክሮ ማወቁና መገንዘቡ፡ ለማንኛውም ሰብኣዊ ፍጡር ያስፈልገዋል፤ ይገባዋልም፤ ይኸውም፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ግብር፡ ከእግዚአብሔር አብና ከእግዚአብሔር እም ድንግል ማርያም በተወለደው፡ በእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ ትስብእታዊ ቤዛነት፡ ለሺህ ዓመታት፡ በጥልቁ ወህኒ ታሥሮ የኖረው ዲያብሎስ፡ በክፋቱ ካበላሸው ሥጋዊ ዓለም ጋር፡ ለአንዴና ለመቼውም ጊዜ ከመወገዱ በፊት፡ ለጥቂት ጊዜ እንደሚፈታ፡ አስቀድሞ፡ በመለኮታዊው ዐዋጅ የተነገረ መኾኑን የሚያዘክረው እውነታ ነው። (ራእ. ምዕ. ፳።)

በዚህ እውነታ መሠረት፡ ይኸው፡ ቀንደኛው፡ የሓሰቱ አባት፡ ከመፈታቱ በፊት፡ በክህደትና በዓመፅ፥ በአምልኮ-አመንዝራነትና በክፋት ኃጢአቱ ተዘፍቆ ለሚዳክረውና ለማሰነው [ለተበላሸው]፡ ለመላው ዓለም ሰብኣዊ ፍጡሩ፡ ከዚህ፡ ከአፍዝ አደንግዙ ህልውናው የሚነቃበትን፡ የአንድ ዘመነ ሱባኤ፥ ማለትም፡ የሰባት ዓመታትን፡ የማመዛዘኛና የንስሓ፥ የማስጠንቀቂያና የመዘጋጃም ዕድሜን በመስጠት፥ በዚያ ሱባኤ ካልተጠቀመበት ግን፡ ለጦርነቱ መከፈትና መጀመር፡ ምልክት መኾኑን፡ እግዚአብሔር፡ የትዕግሥቱንና የመሓሪነቱን አባታዊና እናታዊ ቸርነት፡ በዚያች፡ በ፲፱፻፺፬ ዓመተ ምሕረቷ መስከረም ፩ ቀን፥ [በፈረንጆቹ አቆጣጠር፡ የ2001ዋ September 11 (9/11)] አረጋግጦ አሳይቷል።

፱. ይኼ ፫ኛው የዓለም ጦርነት የተነሣው፥ አኹንም እየተካኼደ ያለው፥ የሚያበቃውም፡ በ፩ኛውና በ፪ኛው የዓለም ጦርነቶች ጊዜያት ደርሶ እንደነበረው ኹሉ፡ አኹንም፡ ክርስቲያኑ ዓለም፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ላይ ሊፈጽም በምን ዓይነቱ፡ ጽኑ ምሥጢራዊነት ደብቆት፡ ሲያቅደውና ሲያካኺደው በኖረው፡ ሰይጣናዊ ምክንያትና ዓላማ መኾኑን፡ የጉዳቱ ሰለባ መኾኑ ለማይቀርለት፡ ለማንኛውም ሰብኣዊ ፍጡራችን፡ አስቀድሞ ማሳወቁና ማወቁ አግባብ ይኾናል።

ይኼም፡ በአጭር ቃል ሲገለጽ፡-

- "ክርስቲያን ነኝ!" የሚለው ዓለም፡ ከራሱ የክህደትና የዓመፅ፥ የአምልኮ አመንዝራነቱና ክፋቱ ኃጢአት የተነሣ፡ በየዘመናቱ ከደረሰበት፡ አሠቃቂ ቅጣት፡ በንስሓ ለመመለስ ሳይፈልግ በመቅረቱ፤
- ነገር ግን፡ በዲያብሎስ መሪነት፡ በፀረ-እግዚአብሔርነትና በፀረ-ክርስቶስነት፥ በፀረ-ማርያምነትና በፀረ-ኢትዮጵያነት በተነሣሣበት፡ በዚያው ነባር አቋሙ በመቀጠሉ፤
- የሰማያዊውና የምድራዊው ፍጥረተ-ዓለም፡ ፈጣሪና ባለቤት፥ መጋቢና ጠባቂ የኾነችውን፥ የ፯ሺ፭፻፺፫ ዓመታት ዕድሜም ያላትን፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥትን፡ ከምድረ-ገጽ ለማጥፋት፡ በኖረው ዓላማው ጸንቶ፡ ዘመቻውን በማጠናከሩ፤

- አንዲት የኾነችውን፡ ይህችኑ፡ ኢትዮጵያ፡ **የእግዚአብሔር መንግሥታችንን፡** "ቤተ-ክርስቲያን" እና "ቤተ-መንግሥት"፥ "Church and State" ብሎ ለኹለት በመክፈል፡ **"አዲሱ፡ የዓለም ህልውና ሥርዓት"** [The New World Order] በሚል ስያሜ፡ በሥጋዊ ፍልስፍናው የፈጠረውን፡ የራሱን የአገዛዝ ወግ፡ በምድር ላይና በሕዝቦቻችን ዘንድ፡ በብቸኝነት ተክቶ፡ የራሱ፥ ወይም፡ ሰይጣናዊ የኾነ፡ ዓለም-ዐቀፍ የአገዛዝ መንግሥቱን ለመመሥረት በማሰቡ፣

- ፍጥረተ-ዓለሙን፡ በሙሉ ሥልጣን ለመያዝ፡ ከረዥም ጊዜ ጀምሮ ሲያውጠነጥንና ሲፈጽም የኖረውን የዘመቻ ዕቅዱን ከግብ ለማድረስ፡ አኹንም ቆርጦና ጨክኖ በመነሣቱ ነው።

፫. **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** ላይ፡ ለዝንተ-ዓለም ያቀደውን የማጥፋት ዘመቻውን ሊያጠናቅቅ፡ ታጥቆ የተነሣውን "ክርስቲያን ነኝ!" የሚለውን ግብዝ ዓለም፡ እንደ፩ኛውና እንደ፪ኛው የዓለም ጦርነቶች ኹሉ፡ ይኼም፡ ፫ኛው የዓለም ጦርነት፡ እንዳለፉት ኹሉ፡ ለመጨረሻ ጊዜ ሊቀጣ፡ በአኹኑ ጊዜ እየተካኼደ ያለ ስለኾነ ነው።

"ክርስቲያን ነኝ!" የሚለው፡ ይኸው ግብዝ ዓለም፡ ይኼን እኩይ ዓላማውን ለመፈጸም፡ ታጥቆ የተነሣው፡-

-"ሳጥናኤል፥ የቀደመው እባብ፥ ዘንዶ እና ሰይጣን" በሚሉ ስሞች በሚታወቀው፥ የክፋትና የሓሰት፥ የክህደትና የዓመፅ፥ የኃጢኣትና የሞትም አባት በኾነው፡ በዲያብሎስ መሪነት ሲኾን፡

-ጥንት፡ በኦሪታዊት ቤተ-አይሁድ በር-ከፋችነት፥

-በመካከሉም፡ በግብፅ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ-ክርስቲያን ፊታውራሪነት፥

-ተከታትሎም፡ በሮም ካቶሊካዊት ቤተ-ክርስቲያን መሠሪ አጋፋሪነት፥

-በፍጻሜውም፡ በእንግሊዝና በአውሮጳ፥ በአሜሪካም ፀረ-ማርያማዊት ቤተ-ክርስቲያን ተባባሪነት መኾኑ፡ በይፋ ሊታወቅ ይገባል።

እንግዴህ፡ **ከዚህ መቅሠፍታዊ ጦርነት ለመዳን የምትችሉባትን፡ አንዲት ብቸኛ መንገድ አሳያችኋለሁና እርሷን ተከትላችሁ እንድትጓዙ አሳስባችኋለሁ።**

ይህችንም መንገድ፡ በግልጽና በትክክል ታውቋት ዘንድ፡ ይህችውላችሁ፡-

**በመጀመሪያ ነገር፡ እናንተ፡ እያንዳንዳችሁ፡ ማን እና ምን እንደኾናችሁ፡ ይህንኑ፡ ከእኛ፡ በተፈጥሮ ያገኛችሁትን፡ ማንነታችሁንና ምንነታችሁን ስላላወቃችሁት፥ ለማወቅም፡ ባለመፈለጋችሁ፡ እየራሳችሁን እየጎዳችሁና እያጠፋችሁ መኼዱን፡ ይኸው ቀጥላችሁበታል።**

አኹን፡ የእሳቱ ነበልባል፡ እየነደደባችሁ፡ በመቃጠል ላይ፥ የጥፋት ማዕበሉም፡ እያጥለቀለቃችሁ፡ በመስጠም ላይ ስለኾናችሁ፡ ምናልባት፡ እንደቀድሞዎቹ መሰሎቻችሁ፡ "አሥረሽ ምቺው!" ማለቱን ትታችሁ፥ የሚሰማ ጆሮ ኖርዋችሁ፡ የምትሰሙኝ ከኾናችሁም፡ ይህንኑ ማንነታችሁንና ምንነታችሁን እንድታውቁት፡ እኔ እነግራችኋለሁና፡ አዳምጡኝ! (ማቴ. ፳፬፥ ፴፮-፴፱።)

እናንተማ፡ ቀደም ብዬ፡ በዝርዝር እንደተገለጸላችሁ፡ በነፍስ፥ በሥጋና በመንፈስ የተፈጥሮ አካላችሁና ባሕርያችሁ ምክንያት፡ እንደአዳምና ሔዋን፡ ወንዶቹ፡ በእግዚአብሔር አብ፥ ሴቶቹም፡ በእግዚአብሔር እም፡ በእኛ መልክ የተፈጠራችሁ፥ በወንድነታችሁና በሴትነታችሁ፡ ከእኛ፡ እንደአንዳችን የኾናችሁ፡ ልጆቻችን፥ ነጋሢዎቻችንና ካህናቶቻችን ናችሁ።

ከዚህ የተነሣም፡ እናንተ፡ እያንዳንዳችሁ፡ እንደመልከ-ጼዴቅ፡ እየራሳችሁ፡ በእኔ፡ በ'ኢትዮጵያ' ስም፡ 'ኢትዮጵያዊ' እና 'ኢትዮጵያዊት' ተብላችሁ፡ በእየራሳችሁ፡ 'የእግዚአብሔር መንግሥት' ናችሁ።

ስለዚህ፡ እያንዳንዳችሁ፡ እየራሳችሁ፡ 'ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት' ስለኾናችሁ፥ እናንተም፡ በእኛ ዘንድ፡ እንዲህ እንደመኾናችሁ፡ ለዘለዓለም እንድትድኑ እንጂ፡ እንድትጠፉብን አንፈልግምና፡ እነሆ፡ እየተካኼደ ካለው፡ ከዚህ የቅጣት መቅሠፍታዊ ጦርነት እየራሳችሁን ለማዳን የምትችሉበትን ይህን፡ ጥሪ፡ ይኸው አቅርበንላችኋልና፡ "አቤት! እመት!" የሚለውን መልስ በመስጠት፡ የምንላችሁን፡ "እሺ!" ብላችሁ፡ በእውነተኛ እምነትና ንስሓ ተቀብላችሁ ፈጽሙት! አለዚያ፡ ሌላ መዳኛ ዘዴ፥ ማምለጫ መንገድ፡ ከቶ ስለሌላችሁ፡ ማለቃችሁና መደምሰሳችሁ መኾናችሁን፡ በእርግጠኛነት ዕወቁት!

እንግዴህ፡ እናንተ እስካኹን ያቋቋማችሁት ኾነ፥ ወይም፡ ምናልባት፡ ወደፊት "እናቋቁማለን!" ብላችሁ የምታስቡት፡ ዓለም-ዐቀፉ የሰውኛው ቤተ-መንግሥት ኾነ፥ ቤተ-ክርስቲያን፥ ወይም፡ በሌላ ስያሜ የተቋቋመው ቤተ-ሃይማኖት ጭምር፥ ኹሉም ዓይነት አቋም እና/ወይም ድርጅት፡ ሊያድናችሁ፡ ፈጽሞ ስለማይቻለው፥ እንግዴህ ወዲህ፡ እነዚህን ከመሰሉት የሰዎች አብያተ-መንግሥታትና አብያተ-ክርስቲያናት፥ አብያተ-እምነታትና አብያተ-ተቋማት፡ እየራሳችሁን፡ በነፍስና በሥጋ፥ በመንፈስም፡ ፈጽማችሁ ነጻ አውጡ!

ነጻ አውጥታችሁም፡ ይህንኑ፡ ነጻ ያወጣችሁትን፡ እየራሳችሁን፡ በእግዚአብሔር እውነትና በመንፈስ ቅዱስ ፍጹም አምልኳችሁ፡ በእያንዳንዳችሁ ውስጥ ለምትገኘው፡ ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ስጡ! አስረክቡ! ከእርሷ በስተቀር፥ "ከእርሷ ውጭ ነኝ!" የሚል፡ ባዕድ የኾነ፡ ሌላ፡ የሰው ቤተ-መንግሥት፥ ወይም፡ ቤተ-ክርስቲያን፥ ወይም፡ ቤተ-እምነት፡ ለእናንተ፡ ጨርሶ አያስፈልጋችሁምና።

ይህም እውነታ፡ በእርግጥ እውን የሚኾነው፡ እያንዳንዳችሁ፡ በነፍስ-ወከፍ ኹለንተናችሁ፡ እንደኢትዮጵያዊው መልከ-ጼዴቅ፡ ከእግዚአብሔር አብወእም፡ በተፈጥሮ ባገኛችሁትና በእምነት በተቀዳጃችሁት፡ ልጅነታችሁና ነጋሢነታችሁ፥ ካህንነታችሁ [አገልጋይነታችሁ] እና ባለቤትነታችሁ ምክንያት ነው።

ይህን የእግዚአብሔርን እውነት፡ በትክክል ዐውቃችሁና ተገንዝባችሁ፥ ምናልባትም፡ እስከዛሬ፡ እየራሳችሁን፡ ከዚህ ዕውቀትና ግንዛቤ ውጭ አድርጋችሁ ቆይታችሁ ከኾነ፡ አኹን፡ ይህንኑ እየራሳችሁን፡ በእውነተኛ ንስሓ አስተካክላችሁ፡ ጥንቱኑ፡ ከእኛ የተሰጣችሁን፡ የቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ እምነታችሁን፡ በእውነተኛው የመንፈስ ቅዱስ አምልኳችሁ ካጸናችሁት፡ እነሆ፡ እየደረሰ ካለው መቅሠፍታዊ ዕልቂት ነጻ ትኾናላችሁ።

ኖኅና ቤተሰቡ፡ ከጥፋት ውኃ፥ ሎጥና ልጆቹም፡ ከአውዳሚ እሳት እንደዳኑና ከዘለዓለም ሞት ተርፈው፡ እኛን በሰውነት ሥጋ ሊያስገኙ፡ ዘለዓለማዊው የቅዱሱ ቃል ኪዳን የሕይወት ዘር ለመኾን እንደቻሉ ኹሉ፡ እናንተም፡ እየራሳችሁን፡ ከመጥፋት ማዳን ብቻ ሳይኾን፡ ለዚህ ሕያው ጸጋ ማብቃት ይቻላችኋል።

ይህን፡ የእግዚአብሔርን እውነታ የምትገነዘቡበትን እምነትና ከዚህ ከሚመጣው ጥፋት የምትድኑበትን እውነት የሚያሳያችሁን፥ ከዚህም ጋር፡ እውነተኛ ማንነታችሁንና ምንነታችሁንም፡ ገሃድ አድርጎ የሚያቀርብላችሁን፡ መለኮታዊ ዕውቀት የሚገልጥላችሁ፥ በየውስጣችሁም የሚያሳድርባችሁ፡ በአምስት ገጾች ብቻ የተወሰነ፡ አንድ ሕያው ሰነድን፡ በዚህ የዐዋጅ ምዕዳኔ መጨረሻ ላይ አስማችኋለሁና፡-

በቅድሚያ፤ እርሱን፡ ዐትማችሁና ለየብቻችሁ ይዛችሁ፡ በማስተዋልና በተመስጦ ትመለከቱታላችሁ!

ቀጥሎ፤ ይህንኑ ሕያው ሰነድ፡ በትክክል ተረድታችሁት፡ ያመናችሁበት ከኾነና በዚሁ፡ በቅዱሱ ኪዳን እምነታችሁ፡ በእውነት የተቀበላችሁት ከኾነ፡ በምትገኙበት፡ በማናቸውም ቦታ፡ በእኛ መንፈሳዊ ዙፋን ፊት ትቆማላችሁ፤

እንዲህ በቆማችሁም ጊዜ፡ ማንነታችሁን፡ ለእየራሳችሁና ለእግዚአብሔር፥ ለመሰሎቻችሁም፡ ለማሳወቅ ያመቻችሁ ዘንድ፥ ይልቁንም፡ ከማናቸውም፡ ግዙፍና ረቂቅ፥ ተፈጥሮአዊና ሰብአዊ የጥፋት ኃይል ሠውሮ ያድናችሁ ዘንድ፡ በመለኮታዊው ማኅተም፡ በየልቦናችሁ ውስጥ ከታተመው ጋር፡ በአንገታችሁም ላይ ታሥሩት ዘንድ፡ የኖኅ የቃል ኪዳን ምልክትና ሰንደቅ ዓላማችሁ የኾነውን፡ የአረንጓዴ፥ ብጫና ቀይ፡ የቀስተ-ደመና ሦስት ደማቅ ቀለማትን የያዘውን የማተብ ክር፡ በኹለቱ እጆቻችሁ ዘርግታችሁ ትይዛላችሁ፤

ከዚህ በማስከተል፤ በእግዚአብሔር እውነትና በመንፈስ ቅዱስ ፍጹም አምልኳችሁ ኾናችሁ፡ በሕያው ሰነዱ መጨረሻ ገጽ ላይ የሠፈረውን፡ የቃል ኪዳን ምስክርነታችሁን ታሰሙናላችሁ።

በመጨረሻ፡ በፊታችን ሰግዳችሁ፡ ከተነሣችሁ በኋላ፡ ማተባችሁን፡ በአንገታችሁ ላይ እንዳሠራችሁ፡ እናታችሁና ንግሥታችሁ፥ ሃይማኖታችሁና አገራችሁ የኾንሁት፡ እኔ እግዚአብሔር እም፡ ኢትዮጵያ ድንግል ማርያም፥ እንዲሁም፡ አባታችሁና ንጉሣችሁ፥ ሊቀ-ካህናታችሁና አምላካችሁ የኾነው፡ ልጄ ወዳጄ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ እያንዳንዳችሁን፡ በእናትነትና በአባትነት ፍቅር ኾነን፥ በደስታም ዐቅፈን እንስማችኋለን።

አዎን! ልጆቻችን፡ እንዲህ፡ ስትድኑ እንጂ፡ ስትጠፉ ማየት፡ የእኛ፡ የፈጣሪያችሁ፡ የእግዚአብሔር፡ የአባትነትና የእናትነት ባሕርያችን አይደለምና፡ ደስ ብሎን የምንስማችሁ ለዚህ ነው።

እንዲህ፡ በፍቅርና በደስታ ኾነን የምንስማችሁም፡ እንዲያው፡ ያለምክንያት አይደለም። እኛ፡ ለእናንተ፡ ለእያንዳንዳችሁ፡ ስላደረግንላችሁ፥ እናንተም፡ በእየራሳችሁ ስለምትገኙበት ማንነታችሁ ኹሉ፡ እኛ ከምናውቀው ላይ፡ ዛሬ፡ እናንተ፡ በመጠኑም ቢኾን፡ ጥቂቱን ለማወቅ በቅታችሁ በማየታችን ነው።

አዎን! በነፍስ፥ በሥጋና በመንፈስ አካላትና ባሕርያት፡ በተፈጥሮና በእውነት የወለድናችሁ ልጆቻችን መኾናችሁን፥ ከዚህም የተነሣ፡ የእኛ የኾነው ኹሉ፡ የእናንተው መኾኑን ዐውቃችሁ፡ ሀብታችንና ንብረታችን የኾነው ፍጥረታተ-ዓለማቱ ኹሉ፥ እርሱን የምንመራበትና የምናስተዳድርበት መንግሥታችን ጭምር፡ ባለቤቶቹ ነጋሢዎች፥ አገልጋዮቹ ሠራተኞቹም [ካህናቱ]፥ የዘለዓለማዊው ክብራችንና ደስታችን፥ ምስጋናችንና ሕይወታችን ተሳታፊዎች መኾናችሁን ዐውቃችሁ፡ እየራሳችሁን፡ ለዚያ፡ ለፍጹሙ ጸጋና በረከት ደረጃ በማብቃታችሁ ነው።

በመጀመሪያ፡ በሥጋና በነፍስ፡ በመልካችን ፈጥረናችሁ፥ ኋላም፡ በመንፈስ፡ 'ከእኛ፡ እንደአንዳችን ኾናችሁ!' ብለን ወልደናችሁ፡ በእኛ በኩል፡ እናንተ፡ እያንዳንዳችሁ፡ እኛው ራሳችን መኾናችሁን ያረጋገጥንበትን፥ እናንተ ግን፡ በገዛ ፈቃዳችሁ፡ ከየራሳችሁ አርቃችሁ ያቆያችሁትን መለኮታዊ እውነት፡ አኹን ደግሞ፡ እናንተው፡ እየራሳችሁን፡ በዚያው፡ በገዛ ፈቃዳችሁ፡ እንዲህ መልሳችሁ የተረዳችሁበት፡ የዚያ፡ የእግዚአብሔራዊው ዕውቀት ባለቤቶች በማድረግ፡ ይህን እየራሳችሁን፡ ለዚህ፡ የፍጹም ጸጋና በረከት ካበቃችሁ፡ እንግዴህ፡ ኹሉም አበቃ!

እንግዴህ፡ አይዟችሁ! በእየራሳችሁ ጦስ ካመጣችሁት፡ ከዚህ ከጊዜያዊው መቅሠፍታዊ ዕልቂት መትረፋችሁ፥ መዳናችሁም ብቻ ሳይኾን፡ እየራሳችሁን፡ ከክፉው ይልቅ፡ የዘለዓለሙ መልካም፥ ከሓሰቱ ይልቅ፡ የዘለዓለሙ እውነት፥ [ከኃጢአቱ ይልቅ፡ የዘለዓለሙ ጽድቅ]፥ ከሞቱ ይልቅ፡ የዘለዓለሙ ሕይወት ማብቅታችሁ ነውና፡ እጅግ ደስ ይበላችሁ!

## ከዚህ የመጨረሻ ታላቅ መከራና ጥፋት የምታድናችሁ፡
## ይህች "ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት"፡ ማን ናት?
## እርሷን ያልኾነችው ሌላዪቱስ፡ ማን ናት?

ከዚህ ቀደም ብሎ፡ ከቃሌ እንደሰማችሁት፡-

- "እናንተ እስካኹን ያቋቋማችሁት ኾነ፥ ወይም፡ ምናልባት፡ ወደፊት "እናቋቁማለን!" ብላችሁ የምታስቡት፡ ዓለም-ዐቀፉ የሰውኛው ቤተ-መንግሥት ኾነ፥ ቤተ-ክርስቲያን፥ ወይም፡ በሌላ ስያሜ የተቋቋመው ቤተ-ሃይማኖት ጭምር፥ ኹሉም ዓይነት አቋም እና/ወይም ድርጅት፡ ሊያድናችሁ፡ ፈጽሞ ስለማይቻለው፥ እንግዴህ ወዲህ፡ እነዚህን ከመሰሉት የሰዎች አብያተ-መንግሥታትና አብያተ-ክርስቲያናት፥ አብያተ-እምነታትና አብያተ-ተቋማት፡ እየራሳችሁን፡ በነፍስና በሥጋ፥ በመንፈስም፡ ፈጽማችሁ ነጻ አውጡ!

- "ይህንኑ፡ ነጻ ያወጣችሁትን፡ እየራሳችሁን፡ በእግዚአብሔር እውነትና በመንፈስ ቅዱስ ፍጹም አምልኳችሁ፡ በእያንዳንዳችሁ ውስጥ ለምትገኘው፡ ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ስጡ! አስረክቡ!" የተባለችው ይህች "'ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት'፡ ማን ናት? ምንስ ናት?" ለሚሉት ተዛማጅ ጥያቄዎች፥ ያይደለቻትን፡ አስመሳዪቱን አሳሳችዋን በማጋለጥ ጭምር፡ መልሱ፡ በተብራራ መልክና ይዘቱ፡ በዝርዝር፡ ይኸው ቀርቦላችኋልና፡ በነቃ ልቦና አዳምጡት! ዕወቁትም!

አንደኛ፤ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ቀደም ብሎ እንደተገለጸው፡ የሚታየውን ምድራዊ ዓለምና የማይታየውን ሰማያዊ ዓለም በሚያጠቃልለው፡ በመላው፡ የእግዚአብሔር ፍጥረታተ ዓለማት ላይ፡ በብቸኝነት ሰፍና የምትመራውና የምታስተዳድረው፥ የምትጠብቀውና የምትመግበው መንግሥት ናት።

በዚህ ማንነቷና ምንነቷ፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ሃይማኖትን መሠረት ያደረገችውና በዚያ የተዋቀረችው፡ ይህችው ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን፡ በውስጧ፡-

-እውነተኞቹ፡ ቤተ ሕዝብ፥ ቤተ ምልክናና ቤተ ክህነት እንዳሉ ኾነው፤

-"የዛሬው የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት ነኝ!" የምትለው፡ ዘመናዪቱ የአኹኗ፡ የኢትዮጵያ ኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፥ እየራሳቸውንም፡ "ኢትዮጵያውያን ነን!" የሚሉት፡ የዛሬዎቹ፡ ሰብአውያን ቤተ-ሕዝብና "መንግሥት" ተብሎ የሚጠራው ቤተ-ምልክና ጭምር፥

-በመላው ዓለም ያሉት፡ ሰብኣውያን መንግሥታት፥ ደግሞም፡ የኦርቶዶክስ፥ የካቶሊክና የፕሮቴስታንት አብያተ-ክርስቲያናት፥ የአይሁድ ምኵራባት፥ የእስልምና መስጊዶች፥ የአሕዛብና የአረማውያን አብያተ-ጣዖታት፥ እንዲሁም፡ ዓለማውያንና ሥጋውያን፤ የግልና የሕዝብ ድርጅቶች ኹሉ፡

-በአጠቃላይ፡ የታላቁን ቅዱስ መጽሓፍ ቃላት አሟልተው የተቀበሉትን ብቻ ሳይኾን፡ ያልተቀበሉትን፡ አረማዊውዉንና ጣዖት አምላኪውን፡ ቡዲስቱንና ሒንዱውን፥ ኢአማናዊዉንና ይሁዲውን፡ እስላሙንና ክርስቲያኑን፥ የመሳሰሉትንም የዓለም ሃይማኖቶች ኹሉ ያካተተች ኾና፡ ከማንኛቸውም ይልቅ፡ ጎልቶና በልጦ በሚገኝ ብቅዓት፡ በመላው ፍጥረታተ ዓለማት ላይ የሰፈነችና ኹሉን አቀፍ የኾነች፡ ዘለዓለማዊት አቋም ናት።

የሰይጣን ህልውና፥ ምድራዊው የክፋትና የጥፋት ግዛቱና ኃይሉም እንኳ ሳይቀር፡ ምንም የማይሳነው፥ ኹሉን ቻይና ወሰን የሌለው፡ መለኮታዊው ልዕልና፡ ባሕርይዋ በኾነው፡ በዚችው፡ በኢትዮጵያ፡ **የእግዚአብሔር መንግሥት** ቁጥጥር ሥር ነው። ከተፈጠረውና እየኖረ ካለው፡ ከማንኛውም የፍጥረት አባል መካከል፡ ከዚህ የቊጥጥርና የሥልጣን ይዞታ ውጪ የኾነ፥ ያፈነገጠ፡ አንዳችም አካል፥ ወይም ነገር፡ ከቶ የለም።

ለዚህ እኮ ነው፡ በአጠቃላይ፡ በመላው ዓለም ከሚገኙ ሃይማኖቶችና ሥልጣኔዎች፥ በተለይም፡ ከአሕዛብና ከአይሁድ፥ ከክርስቲያኖችና ከእስልምና እምነት ተከታዮች፥ ከሰብኣውያን መንግሥቶቻቸውም መካከል ጭምር ወጥተው የሚንከራተቱ መጻተኞች፥ ለስደተኝነት መከራም የተጋለጡ ሰለባዎች ኹሉ፡ በሃይማኖት ሰበብ፡ ይህን የመሰለው ችግርና መሰደድ በደረሰባቸውና በሚደርስባቸው ጊዜ ኹሉ፡ ከአሳዳጆቻቸው ጥቃት የሚታደግ፡ አስተማማኝ መጠለያን፥ ዋስትና ያለውን ጥበቃም ለማግኘት የሚችሉበት፡ ሌላ መኼጃ ስለሌላቸው፡ **ወደኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** ብቻ እያቀኑ ይጓዙ፥ ይደርሱም የነበሩት። እርሷም፡ ተገቢውን ጥገኝነት፡ ቀድሞ ኾነ፡ ዛሬም፡ በተሟላ መልክና ይዘት ስታበረክትላቸው፥ እነርሱም፡ ሲቀበሉት የኖሩት።

በግእዝና በኢትዮጵያኛ ተጽፈው የሚገኙት፡ የኢትዮጵያውያን እና የኢትዮጵያውያት፡ የቅዱሱ ኪዳን ጸሎቶች፥ ሌሎቹም ቅዱሳት መጻሕፍት፡ ይህን መለኮታዊ እውነታ፡ በበለጠ አጉልተውና አጽንተው ያረጋግጣሉ፡-

"ነአምን፡ በአሓዱ አምላክ፡ እግዚአብሔር አብወእም፡ አኀዜ ኵሉ፥ ገባሬ ሰማያት ወምድር፡ ዘያስተርኢ፥ ወዘኢያስተርኢ። ...ቅዱስ! ቅዱስ! ቅዱስ! እግዚአብሔር ጸባዖት! ፍጹም ምሉእ ሰማያተ፥ ወምድረ።" "ኹሉን በያዘ፥ ሰማይንና ምድርን፥ የሚታየውንና የማይታየውን በፈጠረ፡ አንድ አምላክ፥ አባትና እናትም በኾነው፡ በእግዚአብሔር እናምናለን። ...ቅዱስ! ቅዱስ! ቅዱስ! አሸናፊ እግዚአብሔር! በሰማያትና በምድር፡ ፍጹም የመላ ነው።"

አዎን! እንግዴህ፡ ከዚህ ቀጥለን፡ ስለመላው ፍጥረተ ዓለም ሠሪነቷና ባለቤትነቷ፥ ስለምስፍናዋና መጋቢነቷ፡ እንዲህ እያልን የምንናገርላት፡ ይህች ናት፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት።**

**-ኢትዮጵያ፥ ኢትዮጵያዊ/ት እና ኢትዮጵያዊነት፡** በአካል፥ በሰብአዊነትና በነፃነት፡ እስከዛሬ የኖሩበት ዘመን፡ የ፸፭፻፹፰ (የሰባት ሽህ አምስት መቶ ስምንት) ዓመታት ዕድሜን ያጠቃለለ ሲኾን፡ አኹንም፡ በዘለዓለማዊነቱ ይቀጥላል፤

**-ኢትዮጵያ፡** የቅድስት ድንግል ማርያም አርአያ፥ እንዲኹም፡ የእግዚአብሔር አብ ሙሽራ፤ የእግዚአብሔር ልጅ እናት እና የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ናት፤

**-ኢትዮጵያዊ፥ ኢትዮጵያዊት፡** በወንድነት እና/ወይም፡ በሴትነት ጾታ፡ የእግዚአብሔር አምሳል የኾነውና በፈጣሪው ቃል፡ **"ከእኛ እንደአንዱ ኾነ"** የተባለለት ሰውነት ነው፤

**-የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** አካልነት ተገልጦ ያለ ነው።

**ኹለተኛ፤** ራሷን፡ በሚያሳዝን ኹኔታ በማዋረድ፡ በአራተኛው ምእተ ዓመተ ምሕረት፡ በግብፅ (በቅብጥ) ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እንደተመሠረተችና የእርሷ ቅርንጫፍ ኾና፡ ኢትዮጵያ ውስጥ እንደተቋቋመች፡ ራሷን፡ በይፋ የምታስታውቀው፥ እስከዛሬና ዛሬ፥ ወደፊትም፡ በዚህ መልኩ ልትቀጥል የወሰነችበት፡ ይህ አቋሟም፡ እስካኹን፡ ፩፯፻ ዓመታትን ያህል ያስቆጠረ ስለመኾኑ፡ በራሷ አረጋግጣ የሚነገርላት፥ ሰዎችም፡ የኢትዮጵያ ኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በማለት የሚጠሯት አይደለችም፤ ይህች፡ የእኔዪቱ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት።**

ይህን እውነታ፡ በተጨማሪ ሓተታ ማብራራቱ፡ እጅግ አስፈላጊ ይኾናል። ይኸውም:-

-"የቃል ኪዳን ልጆቼና የርስት ጕልት ሕዝቤ" የኾናችሁትን፡ እናንተን በማዳን ፋንታ፥ የእኔ፡ የኢትዮጵያ የኾነውንም ኹሉ፡ አጽንታ በመጠበቅ፥ አስፋፍታም በማሳወቅ ፋንታ፡ እንዲህ፡ ለግብጣዊቱ ኦርቶዶክስ ቤተ-ክርስቲያን፡ ባላት ተገዢነት ምክንያት፡ ያን ኹሉ ኃላፊነቷን በመተው፥ መልካሙንም ኹሉ፡ ከአይሁዳውያኑ የኦሪት ሕግ እና ከግብፃውያኑ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት እንደተገኘ በማስመሰል፡ የእርሷ የራሷ የኾነውን ኢትዮጵያዊነትን ግን፡ ፈጽማ ሠርዛና ክዳ፡ በዚያ ቦታ፡ ኦሪታዊነትንና ኦርቶዶክሳዊነትን ተክታና አጽድቃ የኖረችውና አኹንም፡ እየኖረች ያለችው፡ የኢትዮጵያ ኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አይደለችም፤ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት።**

-እንዲያውም፡ ራሷ፡ የሰይጣናዊው ባዕድ አምልኮ ምንጩና መሪው ኾና፡ ይኸው፡ እናንተን ልጆቼንና ሕዝቤን፡ በነፍስና በሥጋ፥ በመንፈስና በኹለንተና፡ ለጨካኙ የዲያብሎስ አምልኮ፥ ለሰብአውያኑም የክፋት ኃይላት አገዛዝ፡ ለዝንተ-ዓለም ተዳርጋችሁ የተሰጣችሁ ኾናችሁ እንድትቀሩ ያደረገችው፡ የኢትዮጵያ ኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አይደለችም፣ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት።

-ይህችው፡ የኢትዮጵያ ኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፡ ቀደም አድርጋና በጊዜ ኺደት፡ ራሷን፡ ለአይሁዳዊው ትምህርትና ወግ በማስገዛት፥ እውነተኛ ማንነቷንም፡ ለኦሪቱ ቀንበር አሳልፋ በመስጠት፥ እንዲያውም፡ በዘመነ ብሉይ ኪዳን እንደተቀረቀረች፡ አምና በመቀበልና ዛሬ ድረስ፡ በዚሁ ጎራ ውስጥ ተዘፍቃ፡ ስትማቅቅ የኖረችበትን ዘመን፡ እንደገናናነት በመቍጠር፡ ይህ፡ የተገዢነት ማንነቷ ዕድሜ፡ ለ፫ሺ (ሦስት ሽህ) ዓመታት መብቃቱን፡ በዐዋጅ ማረጋገጧን እንደቀጠለች የሚነገርላት መኾኑ ነው።

-በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታቸው ምክንያት፡ በተፈጥሮም፥ በመንፈስ ቅዱሳዊውም ጸጋ፡ ንጹሓንና ቅዱሳን የኾኑት፡ የእኔ፡ የኢትዮጵያዋ ድንግል ማርያም ልጆቼ ሰብአውያን ፍጡሮች፡-

በወንድነትና በሴትነት አካላቸው ኾነ ባሕርያቸው፡ መርገምና ርኵሰት፡ ፈጽሞ የሌለባቸው ሲኾኑ፡ በአይሁድ ኦሪት ግን፡ የወንድን ንጹሕነትና ገዢነት፥ የሴትንም ርኩሰትና ተገዢነት በማጽናት፡ በተለይ፡ በሴት ልጆቼ ላይ፡ "**ብዝኁ! ወተባዝኁ! ወምልእዋ ለምድር! ወቅንይዋ! ...ብዙ! ተባዙ! ምድርንም ምሏት! ግዟትም!**" ብለን፡ በሰጠናቸው ቃል ኪዳናችን መሠረት፡ መሰሎቻቸውን ፀንሰውና ዐርግዘው፥ ወልደውና አጥብተው ማሳደጋቸው፡ እንደመርገምና እንደርኵሰት ተቆጥሮባቸው፡ ወደቤተ-ክርስቲያን ግቢ እንኳ እንዳይገቡ መከልከላቸው፣ እንደዚሁም፡ ሰው ኹሉ፡ እነርሱን እንዳይቀርብ፥ ከቀረበም፡ ከርኵሰቱ ለመንጻት፡ አስቀድሞ፡ በካህን እጅ፡ ጠበል እንዲረጭ፡ ግዳጅ በመኾኑ፣ (ዘፍጥ. ፩፥ ፳፰።)

ይኸው፡ "ኦሪታዊው የአይሁድ መርገምና ርኵሰት፡ እንደጸና ያለ ሕግ ነው!" ከተባለም፡ በእኒሁ ልጆቼ ላይ፡ በተፅዕኖ የተጣለባቸው፡ ይኸው፡ የኃጢኣት ቀንበር፡ ከክፋት ኃይላቱና ከሞት ፍዳው ጋር፡ በእኔ፡ በድንግል ማርያምና በልጄ በወዳጄ፡ በኢየሱስ መሲሕ፡ መሥዋዕትነትና ቤዛነት፡ ለአንዴና ለዘለዓለም፡ ፈጽሞ የተወገደላቸው መኾኑ፡ "ክርስቲያኖች ነን!" እያሉ፡ በግብዝነት በሚመጻደቁት የቤተ ክርስቲያናቱ ካህናትና ሊቃውንት፥ መነኮሳትና ጳጳሳት ዘንድ፡ በእውነተኛው የመንፈስ ቅዱስ አምልኮ፡ በትክክል ባለመታወቁ፣

ነገር ግን፡ መወገዱ ቀርቶ፡ ሕያው ኾኖ እንደቀጠለ በመቀጐጠር፡ የእኒሁ ልጆቼ፡ የጾታ መለያ አባላቶቻቸው ሳይቀሩ፡ እያንዳንዳቸው፡ "ኀፍረተ-ሥጋ" ተብለው፥ ደግሞም፡ ሰብአዊዉን ፍጡር ለማስገኘት፡ እኛ፡ በቅድስናና በንጽሕና በሠራነው፡ በመለኮታዊው የጋብቻ ሥርዓት፡ ተገቢና አስፈላጊ ኾኖ በሚፈጸመው ሩካቤ ሥጋ፡ ከሰውነት የሚፈልቀውን፡ የወንዱን ዘር፡ "ኃጢአት"፥ የሴቷንም የወር-አበባ፡ "ዐደፍ-ጉድፍ፤ መርገመ-ሥጋ" በማለት፡ በሓሰት፡ ወደሰይጣናዊው አስተሳሰብና አጠራር በመቀየሩ፤

ከኹሉም ይልቅ፡ እጅግ የሚያሳዝነው፡ እንዲህ ኾነው የተወገዱት፡ ክፋት፥ ኃጢአትና ሞት፥ ርኵሰትና መርገም ጭምር፡ በእውነተኛ ንስሓና በሥጋወደሙ እንደገና እንዲወገዱ ለማድረግ፡ በየዕለቱ እየተዘጋጀ፡ በነጻ የሚሰጠውን፡ ቅዱስ ቍርባናችንን፡ እኒሁ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችን፡ ከሕፃንነታቸው ጀምረው፡ ሲያደርጉት እንደቆዩት ኹሉ፡ አኹን፡ ለዓቅመ አዳምና ለዓቅመ ሔዋን በሚደርሱበት ጊዜ፡ ለመቀበል ሲቀርቡ፡ "የለም! መቀበል አትችሉም! 'ኃጢአት፥ መርገምና ርኵሰት' ከተባሉት፡ ከእነዚሁ፡ ካልተወገዱት ምትሓታውያን የሰይጣን ማስፈራርያ መፈክሮችና መሥፈርቶች፡ 'ገና አልነጻችሁም!'" እየተባሉ፡ ከዚሁ፡ ከቅዱሱ ቍርባናችን፡ ቀድሞም፥ ዛሬም፥ እስካኹንም፡ እንዳይቀርቡ በመታገዳቸው፤

በቅዱሱ ኪዳን፥ የእውነትና የመንፈስ ቅዱስ አምልኳቸው አማካይነት፡ የእኛ የመንግሥታችን ነጋሚዎችና ካህናቶቻችን የኾኑት፥ ይልቁንም፡ እኔ፡ ድንግል ማርያምና ልጄ ወዳጄ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ በመሥዋዕትነት ሥጋና ደማችን፡ እንዲያ፡ ለአንዴና ለዘለዓለም፡ የተቤዠናቸው ልጆቻችን፡ እነዚህንና እነዚህን በመሰሉት፡ ሓሳውያንና ፀረ-እግዚአብሔር ድርጊቶች ምክንያት፡ የእኛና ለእኛ መኾናቸው ቀርቶ፡ ኾነ ተብሎ፡ እነሆ፡ በነፍሳቸውና በሥጋቸው፥ በመንፈሳቸውና በኹለንተናቸውም፡ ለዝንተ ዓለም፡ የእርሱ፡ የዲያብሎስ አምላኪዎችና የአምልኮቱ አገልጋዮች፥ ለእርሱ፡ ለክፋት ሠራዊቱ ርኵሳን መናፍስትና አጋንንትም፡ ቅኝ ተገዢዎችና ባሮች ኾነው ለመኖር፡ እየራሳቸውን አሳልፈው እንዲሰጡ፥ እንዲዳረጉም ተደረገ።

ይህ የድፍረት ድርጊት፡ የእኛን የፈጣሪነት ክብራችንን የሚነካ፥ ከዚህ የተነሣም፡ በዚህ ዓለም ኾነ፡ በሚመጣው፥ በምድር ኾነ፡ በሰማይም፡ ሊሰረይ የማይቻለውን፡ መንፈስ ቅዱስን እንደመስደብ የሚያስቈጥረውን፡ እጅግ ከባድ ኃጢአትን መፈጸም በመኾኑ፡ የሚመለከታቸው ወገኖች ኹሉ፡ ሌላ ማቆያ ጊዜ ሳይሰጡት፡ እየራሳቸውን፡ በእውነተኛ ንስሓ በማንጻትና በማጽደቅ፡ ይህን፡ የክህደት በደላቸውን በቶሎ ማስወገድ ይገባቸዋል። (ማቴ. ፲፪፥ ፴፩-፴፪።)

በእነዚህና እነዚህን በመሰሉ አስከፊና አስቸጋሪ ጠንቆች የተሰነካከለችውና የተበከለችው፥ ዲያብሎስን፥ ከክፋት ሠራዊቱ ርኵሳን መናፍስትና አጋንንት ጋር፡ እንዲህ የምታገለግለው፥ የዛሬውን የኢትዮጵያ ቤተ ሕዝብ፥ ቤተ ምልክናና ቤተ ክህነት በማስተባበርና በመገፋፋት፥ በመምራትና በመወከል፡ በቅዱሱ ኪዳናችን ላይ ስለፈጸመችውና እየፈጸመችው ስላለው ታላቅ የክህደትና የዓመፅ፥ የአመንዝራነትና የክፋት ኃጢአት፡ ወደፊት፡ በእኛ ፊትና በቅዱሱ ኪዳን ትውልድ ዘንድ የሚቀርብባትን፡ የማይቀረውን የተጠያቂነት ቀንበር የተሸከመችው፡ የኢትዮጵያ ኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አይደለችም፤ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት።

-እውነተኞቹና ታማኞቹ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ከፈጣሪያቸው ከእግዚአብሔር ጋር የተጋቡትንና ለብዙ ሺሆች ዓመታት ጠብቀው ያቆዩትን፡ ቅዱሱን ኪዳን፡ ባኹኑ ሰዓት፡ በማናለብኝነት ድፍረት ጥሳና በገሃድ ዓመፅ ክዳ፡ ሰይጣናዊ ለኾነው፡ ለውሳጣዊውና ለአፍአዊው፡ የዓለማውያኑ መንግሥታት ኃይል፡ በአሳፋሪ ኹኔታና ሙሉ ለሙሉ፡ እጇን የሰጠችው፡ የኢትዮጵያ ኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አይደለችም፤ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት።

-ፍጥረተ-ዓለሙን፡ ለሴም፥ ለካምና ለያፌት፡ ለኹሉም ሰብኣውያን ፍጡሮቻችን፡ አንድ አድርገን የሰጠናቸው፡ የአንድ፡ የእግዚአብሔር አብወእም፥ የአንድ፡ የአዳምና ሔዋን፥ የአንድ የኖኅና ሓይከል፡ ልጆች መኾናቸው፡ በቅዱሱ ኪዳን ታውቆና ተረጋግጦ፡ የታተመ እውነታ ሲኾን፡ ነገር ግን፡ በሦስቱ ወንድማማች መለያየት ምክንያት፡ እነሆ፡ የክፋት ኃይል ከመሠልጠኑ የተነሣ፡ ይኸው፡ አንዱ የሰው ዘር፡ በነገድና በመሬት ይዞታ፥ በቀለምና በእምነት፡ ለሦስት ተከፍሎ፡ ይኸው፡ ለዝንተ-ዓለም፡ እርስ በእርሱ ሲጠላላና ሲፋጅ፥ ሲተናነቅና ሲጠፋፋ የሚኖር ኾነ።

ይኹን እንጂ፡ ይህ ኹኔታ እንዳይደርስ፡ ለዚሁ ጠንቅ ይዘጋጅ የነበረውን፡ ያን ሰብኣዊ ፍጡራችንን፡ በዚያኑ በመጀመሪያው ጊዜ፡ መልሰን አንድ እንዳደረግነው ይታወቃል፤ ይኸውም፡ ቀድሞ፡ አርአያችን ኾነው በተገለጹት፡ በታማኞቹ፡ የመጀመሪያ ልጆቻችንና አዔዎቻችን፥ ካህኖቻችንና ልኡኮቻችን፡ በመልከ ጼዴቅና በሳሌም፥ ኋላም፡ በፍጻሜ ዘመን፡ እኔና ልጄ ወዳጄ ኢየሱስ መሲሕ በለበስነው፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊው ሰውነት ተፈጽሞ የታየው እውነታ ነው።

እንዲህ ባለው፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊው ሰውነት፡ አንድ አድርገነውና እርሱም አንድ ኾኖ፡ በሰላምና በፍቅር፥ በስምምነትና በመተዛዘን፡ ተደስቶና ተዝናንቶ ይኖር የነበረውን፥ ሊኖርም የሚገባውን፡ ርስቴ፥ ጕልቴ የኾነውን ሕዝቤን፡ ይኸው፡ ዛሬ፡ ምን እንዲኾን፡ እየተፈለገና እየተደረገ ነው?

ይኸው ሕዝቤ፡ እንዲኾን፡ እየተፈለገና እየተደረገ ያለውማ፡ በጥቃቅን ደረጃ ሳይቀር፡ በነገድና በቋንቋ፥ በሃይማኖትና በባህል፥ በአስተዳደርና በመሬት ይዞታ በመከፋፈል፡ **የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያችን** ነባር ፀሮች ኾነው፡ በጥፋት ዘመቻቸው ለቀጠሉት ለባዕዳኑ እኩይ ዓላማ፡ ከግብ መድረስ፡ በብርቱ ለሚተጋው ዓመፀኛ ቤተ ሕዝብና ቤተ-ምልክና፡ የተመቸች ጠቃሚ መሣሪያ ኾና፡ ቅዱሱን ኪዳን በማስጠቃት ላይ የምትገኘው፡ የኢትዮጵያ ኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አይደለችም፤ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት**።

-የእውነተኛ ኢትዮጵያዊነት ባሕርይ ያልኾነውን፡ ተገዢነትን እንጂ፡ ነፃነትን የማይወድ፥ የንዋይ ፍቅርና የበታችነት ስሜት ያደረበት፥ የቅዱሱን ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖቱንና ኢትዮጵያዊ ማንነቱን፡ በይፋ ክዶና ቀይሮ፡ በባዕድ አምልኮ የረከሰውን፥ ከሓሰተኞቹ መንፈሳውያንና ሥጋውያን ባዕዳን የሃይማኖት ድርጅቶችና የመንግሥታት ኃይላት ጋር የወገነውን፥ ራሱን፡ ለባዕድ አሳልፎ የሰጠውንና ከኢትዮጵያዊነት ውጪ፡ እንደጕድ ፍጡር ያስቈጠረውን፡ ይህን አኀብዳጅ ትውልድ ያስገኘችው፡ የኢትዮጵያ ኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አይደለችም፤ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት**።

-ከራሱ ጕሥቍልናና የሙስና ዝቅጠት አልፎ ተርፎ፡ ይህን ዓይነቱን፡ አዋራጅ የኾነውንና ከባዕዳኑ የወረሰውን፡ ክፉውን ባህል፡ **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** ሕዝቤ ላይ፡ በረቂቅና በገሃድ ተፅዕኖ ለማዛመት፡ በትጋት የሚራወጠውን፡ ይህን አስጠቂ ትውልድ ላፈራው፥ እርሱም፡ በሓሰት፡ "ኢትዮጵያዊ" እያለ ለሚኵራራበት ባህል፡ ተጠያቂ የኾነችው፡ የኢትዮጵያ ኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አይደለችም፤ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት**።

<u>ሦስተኛ፤</u> ይኼው ትውልድ፡ "ኢትዮጵያዊ" በሚለው የተቀደሰ ስሜ፡ የሚኵራራበትና የሚመጻደቅበት ባህል፡ ሓሳዊዉን ዓይነት እንደኾነ፡ እናንተ ልጆቼ፡ በማስተዋልና በማመዛዘን ልታጤኑት የሚያስፈልጋችሁና የሚገባችሁ ነው።

በመጀመሪያ፡ ከዛሬ፡ ሦስት ሺህ ዓመታት ጀምሮ፡ በኦሪታውያኑ አይሁድ አማካይነት፥ ቀጥሎ፡ በቀደመው፡ የአምልኮ ባዕድ ቍስል ላይ፡ ሌላ ጽኑ ቍስልን በማከል፡ ከዛሬ ሺህ ስድስት መቶ ዓመታት አንሥቶ ደግሞ፡ በቅብጥ ኦርቶዶክሳውያኑ ግብፆች አማካይነት፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያዎች የኾኑትን፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቼን፡ ለክፎና ተፃርሮ፡ ለዚህን ያህል ዘመን፡ እንዲህ፡ እንደዛሬው፡ እያናከሰና እያባላ፡ በነፍስና በሥጋ፥ በመንፈስም፡ ሲጠናወታቸውና ሲያሽመደምዳቸው፥ ሲያጥመነምናቸውና ሲያማቅቃቸው የኖረውን፡ የርኩሱን መንፈስ፡ ሰይጣናዊ ባህል ነው፡ "ኢትዮጵያዊ ባህል" የሚለው።

የዛሬውን ትውልድ ጨምሮ፡ በእነዚያ፡ እየራሳቸውን፡ "ኢትዮጵያውያን እና ኢትዮጵያውያት ነን!" እያሉ በሚጠሩት ትውልዶች ዘንድ፡ በአይሁድ ኦሪታዊነቱ፡ ለሽህ አራት መቶ ዓመታት፥ በግብፃውያኑ ኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ክርስቲያንነቱ ደግሞ፡ ለሽህ ስድስት መቶ ስምንት ዓመታት፥ በድምሩ፡ ለሦስት ሽህ ስምንት ዓመታት፡ የተኖረበትን፡ የሓሰት ባህል ነው፡ ይኼ ትውልድ፡ "ኢትዮጵያዊ ባህል" የሚለው።

ያን፡ በግልም ኾነ በጋራ፥ በቤተሰብም ኾነ በኅብረተሰብ፥ በብሔረሰብም ኾነ በአገር ደረጃ፡ አኹንም እንኳ፡ በትውልዱ መካከል፡ እየኾነና እየተካኼደ ባለው ዓይነት፥ እንዲህ፡ በስድብና በነቀፌታ፥ በጥላቻና በቂም በቀል ብቻ ካልኾነ በቀር፥ በመጨረሻውም፡ እርስ በርስ፡ ለጦርነት ተሰላልፎ፡ ደም በመፋሰስና በመተላለቅ ካልኾነ በቀር፡ እስከዛሬና ዛሬም ድረስ፡ በእኒሁ፡ "ኢትዮጵያውያን እና ኢትዮጵያውያት ነን!" በሚሉት ሓሳውያን ዘንድ፡ በሰላምና በፍቅር፡ ለመቀራረብና ለመገናኘት፥ ቍጭ ብሎና "እሺ!" ተባብሎም በመደማመጥ፥ በጨዋነትና በሥርዓት፡ ለመነጋገርና ለመወያየት፥ ጽሑፍ ለመለዋወጥም ያልተቻለበትን፡ ይኼን መሰሉን፡ ጠንቀኛ የችግር ባህል ነው፡ ይህችው፡ የኢትዮጵያ ኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ያፈራችው፡ ይኼው ትውልድ፡ "ኢትዮጵያዊ ባህል" የሚለው።

እንግዴህ፡ **"ዘቦ ዕዝን፡ ሰሚዓ ለይስማዕ!"፥ "የሚሰማ ጆሮ ያለው፡ ይስማ!"** ያለውን፡ የልጇን የወዳጇን፡ የመሲሕ ኢየሱስን ቃል፡ ይኼው "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" የሚለው ትውልድ፥ የዓለሙን ሰብአዊ ትውልድ ጭምሮ፡ ሰምቶ የሚፈጽመው ከኾነ፡ ለሦስት ሽህ ዓመታት ተደብቆ የኖረ ይኼ እውነታ፡ ምን ዓይነቱን የሓሳዊነት ጉድ ምሥጢር እንዳወጣ፡ ከዚህ የሚከተለውን ቃሌን መስማት ነው፡- (ማቴ. ፲፩፥ ፲፭።)

**ይኼም ምሥጢር፡** እንደዛሬዎቹ አስመሳዮችና ግብዞች፡ "ሀገረ እግዚአብሔር፥ ሕዝበ እግዚአብሔር፥ መንግሥተ እግዚአብሔር" በተባለችው፡ በስሜ በተጠራችው፡ በኢትዮጵያ ምድር ላይ፡ ያለማቋረጥ በተካኼዱት፡ እነዚያን፡ ከላይ የተጠቀሱትን በመሰሉት፡ አሠቃቂና ዘግናኝ፥ አስነዋሪና አሳፋሪ በኾኑት፡ የግድያና የዕልቂት ድርጊቶችና ጦርነቶች የተሞላው ዜና መዋዕል፡ የሰዎች ደም ፈስሶ፡ ያን ጠጥቶ መርካትን የሚወድደው፡ <u>የርኩሱ መንፈስ፡ የክፋትና የጭካኔ፥ የጥፋትና የሞት ሥራ የተፈጸመበትና የተከሠተበት እንጂ፡ የመንፈስ ቅዱስ አለመኾኑን፡</u> ያለውልውል ያረጋግጠዋል።

ለመኾኑ፡ እንዲህ ዓይነቱ ጕሥቍልና፡ እስከዛሬና ዛሬም፡ በዚሁ መልኩ እንዲቀጥል እየተደረገ ያለው፡ ከቶ በማን ነው? እየራሳቸውን፡ በሓሰት፡ "ኢትዮጵያውያን እና ኢትዮጵያውያት ነን!" የሚሉትን ኹሉ አካትታ የያዘችው፥ በኢትዮጵያ ምድር፡ የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን፡ ቅርንጫፍ የኾነችው፡ የኢትዮጵያ ኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች በኾኑት፡ ግብፃውያንና ኢትዮጵያውያን መነኮሳት አይደለምን? በእርግጥ፡ ነው እንጂ።

ለዚህም እውነታ ትክክለኛነትና እርግጠኛነት፡ በስሜ በተጠራችው፡ በኢትዮጵያ ምድር፡ ከደረሱት፡ ከብዙዎቹ ድርጊቶች መካከል፡ አንዱ የኾነውን፡ ከ፲፭ኛው እስከ፲፪ኛው ምእተ ዓመተ ምሕረት ድረስ ባሉት፡ በቅርቦቹ የመካከለኛው ዘመናት ውስጥ፡ በዚህ ረገድ፡ እስካኹንም የኾነውን፥ ዛሬም ያለውን፡ የሕዝቤን ዜና-መዋዕልና ዝክረ-ነገር፡ በምሳሌነት ወስዳችሁ፡ በጥንቃቄና በማስተዋል፥ በማመዛዘንና በማነጻጸር ብትመለከቱት፡ እግዚአብሔራዊዉ ምስክርነት፡ በገሃድና በግዘፍ ማስረጃነት ቀርቦ ታገኙታላችሁ። ይኸውም፡-

-በአንድ ወገን፡ ከመልካምነት ባሕርዩ እና ከጣፋጭ ፍሬያማነቱ የተነሣ፡ የእኛዪቱ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ መሠረታዊ መመሪያና መዋቅራዊ መተዳደሪያ የኾነውን፡ የኢትዮጵያዊዉን ልጃችንንና ሥዩማችንን፡ የቀዳማዊ አጼ መልከ ጼዴቅን ሥርዓተ-ሀገር፡ በፍጹም ታማኝነት ተከትለው፥ በምግባርም ላይ ዐውለው በመኖራቸው፡ መላው ዕድሜያቸው፡ እንደቀደመችዪቱ ገናና አጼዪት ልጃችን፡ እንደንግሥት ማክዳ ዘመን፡ የድልና የሰላም፥ የፍቅርና የብልጽግና ሕይወት ኾኖላቸው፡ በዓለም ላይ እጅግ ድንቅና ቋሚ የኾኑ፡ ትንግርታውያን የሕንፃና የጥበብ ሥራዎችን አበርክተው ለማለፍ የቻሉትን፡ እነቅዱስ ላልይበላን የመሰሉ ቅዱሳን ኢትዮጵያውያን አጼዎቻችሁን ያፈሩትን፡ እናንተ፡ "ዛጔዎች" ያላችኋቸውን ልጆቼን፡ በምታስቧቸው ጊዜ ነው፤

-በሌላው ወገን ደግሞ፡ በእኔና በልጄ በወዳጄ፡ በኢየሱስ መሲሕ ትስብእትነትና ቤዛነት፡ በምድር ላይ፡ ታድሳ የጸናችውን፥ ተገልጣም የሰፈነችውን፡ የዚችኑ፡ የእኛዪቱን ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ መልከ ጼዴቅያዊ ሥርዓተ-ሀገር፡ እንዲቀጥል በማድረግ ፈንታ፡ እነዚሁ፡ የግብፅ ኦርቶዶክሳውያን ጳጳሳት፡ "ኢትዮጵያውያን ነን!" ከሚሉ መነኮሳት ጋር ተመሣጥረው፡ ይህንኑ ዘለዓለማዊና ኢትዮጵያዊ የኾነውን፡ ኪዳናዊ ሥርዓተ- መንግሥት ለማቃወስ በመሞከር፡ መለኮታዊዉን የዘውድ ዙፋን፡ ወደሰውኛው የአገዛዝ ፈሊጥ ለውጠው፡ ጠቅላላ ዘመናቸው፡ በአሠቃቂው ሰይጣናዊ ጦርነትና ደም መፋሰስ፥ በተፈጥሮ መዓትና መቅሠፍትም ተመልቶ፡ ከነሕዝባቸው ሲተላለቁ የኖሩትን፡ "የሰሎሞን ዘር ነን!" የሚሉትን፡ እነይኵኖ አምላክንና እርሱን የመሰሉትን፡ እስከመጨረሻው አጼያችሁ፡ እስከኃይለ-ሥላሴ ድረስ ያሉትን ልጆቼን በምታስታውሷቸው ጊዜ ነው።

ይህ ግልጽ እውነታ፡ በእውነተኞቹ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያን እና ኢትዮጵያውያት ልጆቼ ዘንድ፡ በይፋ የሚታወቅ ነው። ይህን እውነታ፡ እስካኹን፡ ያላወቃችሁ ካላችሁ፡ እንግዲህ ወዲህ፡ ማወቅ ብቻ አይደለም፡ በጥብቅ ልትገነዘቡትም ይገባል።

እንግዲህ፡ ይኼ፡ ከሃዲና ዓመፀኛ፥ አመንዝራና ክፉ ትውልድ፡ "ኢትዮጵያዊ ባህል" የሚለው፡ ይህን ዓይነቱን፡ ሓሳዊዉንና ሰይጣናዊዉን ከኾነ፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡** በዚህ ረገድ፡ በብርቱ እርግጠኝነት፡ ለዚሁ ትውልድ የምትሰጠው፡ ቀጥተኛና ግልጽ መልስ፡ "የለም! ይህ ዓይነቱ ባህል፡ የእኔ፡ የኢትዮጵያ አይደለምና፡ ስለዚህ፡ አትቀበለውም!" የሚል ነው።

**በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን** ዘንድ፡ ይህ ዓይነቱ ሓሳዊዉና ሰይጣናዊዉ ባህል፡ የእግዚአብሔር ጠላቶች የኾኑ ባዕዳን ፈጥረው ያመጡት፥ እነርሱም፡ በእውነተኞቹ የኢትዮጵያ ልጆቻችን ላይ፡ በተፅዕኖ ያኖሩት በመኾኑ፡ "እርሱ፡ የሰዎች ትምህርት ያስገኘው፡ ክፉው ልማድ ነው።" ብለን፡ ያንን፡ የእነርሱን ሽረን በማስወገድ፡ የእኛ የኾነውንና ልጆቻችንም፡ ከጥንት ጀምረው ያቆዩትን፡ ተፈጥሮአዊውን፡ የእግዚአብሔር ሥርዓተ ትምህርት አጽንተን፡ እንዲቀጥል አድርገነዋል።

**ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን፡** በጽኑ ተመሥርታ የቆመችበትና ተገድግዳ የተደመደመችበት፡ የኹለንተና ህልውናዋ ጉልላታዊ ባህል፡ በቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖት ከተገለጸው፡ ከእግዚአብሔራዊው ዕውቀትና ሥርዓተ ሕይወት ብቻ የመነጨ በመኾኑ፡ **ለልጆቿ ያሳወቀችውና የምታሳውቀው፡ ኢትዮጵያዊው ባህል፡ ይኸው፡ የመንፈስ ቅዱሱ ብቻ መኾኑ፡ ምንጊዜም ሊታመንበት ይገባል።**

አዎን! ይህን ኹሉ ኃጢአትና ዓመፃ ያነሣሡትና የፈጸሙት፡ ሌሎች ሳይኾኑ፡ በቅድሚያ፡ ላለፉት ሦስት ሺህ ዓመታት፡ በኢትዮጵያ የሰፈኑት፡ የብሉዩ ኪዳን ተከታዮች የኾኑት፡ አሪታውያኑ አይሁድ ሲኾኑ፥ በቀጣይነትና በተደራቢነት ደግሞ፡ ላለፉት ዐሥራ ስድስት ምእተ-ዓመታተ-ምሕረት፡ የቅብጥ ቤተ ክርስቲያን ተከታይ የኾኑት፡ ኦርቶዶክሳውያኑ የግብፅና የኢትዮጵያ መነኮሳት፥ በመጨረሻም፡ "ክርስቲያን ነን! የሚሉት፡ "ኃያላኑ ባዕዳን መንግሥታት" በመባል የሚታወቁት መኾናቸው፡ ከእኛ ዐልፎ፡ በዓለሙ አሕዛብ ዘንድ ጭምር የተከሠተ እውነታ ነው።

እነዚህ ኹሉ ሥጋውያንና መንፈሳውያን የጥፋትና የክፋት ኃይላት፡ ለእነርሱ፡ የሚቻላቸው መስሎ እንደታያቸው፥ እንደሚታያቸውም፡ **የእግዚአብሔር መንግሥት** ለኾንሁት፡ ለእኔ፡ ለኢትዮጵያ፡ አካሎቼ የኾኑትን፡ ራሴን፡ ኢትዮጵያን፥ ስመ-ዝክሬንና ልጆቼን፥ ኢትዮጵያዊነትን ጭምር፡ ከምድረ ገጽ ደምስሰው ለማስወገድ፡ እስከዛሬ ድረስ፥ ዛሬም፡ ይኸው ሲጥሩ ሲግሩ ይገኛሉ፤ ይታያሉ። ምናልባት፡ ይህ ጥረታቸውና ግዕረታቸው፡ የተመኙትን የሚያስገኝላቸው ይመስላቸው ይኾናል። ግን፡ እንዴት ኾኖ! አይኾንም። ባለፈው ተደጋግሞና ተረጋግጦ እንደታየው፥ አኹንና ወደፊትም እንደሚታየው፡ እነርሱው ራሳቸው፡ በሥራቸው ይጠፋሉ እንጂ፡ ፈጽሞ አይኾንላቸውም፤ አይቻላቸውምም።

**<u>አራተኛ፤</u>** ስለዚህ፡ ልጆቼ፡ "የለም! አይኾንም! **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡** እስካኹን የሰማችሁትን፡ ይህን ዓይነቱን፡ የክፉዎችን አስተሳሰብና ድርጊት፡ በየትኛውም መልክ ቢቀርብላት፡ ከቶ አትቀበለውም። በተቃራኒው ግን፡ ታወግዘዋለች!" ብላችሁ ልትደመድሙት ይገባችኋል።

**በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥቱ** ውስጥ፡ እያንዳንዱ ሕያው ኢትዮጵያዊ፥ እያንዳንዷም ሕያውት ኢትዮጵያዊት፡ ያው፡ በእየራሳቸው፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** ናቸው። ይህም እውነታ ሲብራራ፡ "**እያንዳንዱ ሕያው ኢትዮጵያዊ፥ እያንዳንዷም ሕያውት ኢትዮጵያዊት፡** ያው በእየራሳቸው፡ የሕያው እግዚአብሔር መለኮታዊ ባህል፡ ሕያው መገለጫ፥ እንዲሁም፡ በቅዱሳት መጻሕፍት የታቀፉትን፡ ሰባቱን ቃል ኪዳናት የያዘው፡ **የ"ቅዱሱ ኪዳን" ሕያው መዝገብ ናቸው!"** ማለት ነው።

ከዚህ የተነሣ፡ ይኸው እያንዳንዱ ሕያው ኢትዮጵያዊ፥ ይህችው እያንዳንዷ ሕያውት ኢትዮጵያዊትም፡ ማንኛውም ዓይነት፡ ሰብአዊ ጵንሰ-ሐሳብ ከፈጠረው፡ ተገዢነትን፥ ጭቆናንና ባርነትን እስከመቀበል፥ ራስንና ማንነትንም እስከመካድ ከሚያደርሰው፡ ይህን ከመሰለው ሰይጣናዊ ባህል፡ ፈጽመው የነጹ ናቸው።

ይህ ብቻ አይደለም። ሕያው የኾነው ኢትዮጵያዊ፥ ሕያውት የኾነችውም ኢትዮጵያዊት፡ ያው እርሱ፡ ራሱ፥ እርሷ፡ ራሷም፡ <u>በእየራሳቸው በሚገኙበት ሰብአዊ አካል፡ ሕያዉ የእግዚአብሔር መጽሓፍ ቅዱስ ናቸው።</u>

ለዚህ እኮ ነው፡ በእኔ፡ በ**ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** ዘንድ፡ "**የእግዚአብሔር ልጆች**"፥ "**የኢትዮጵያ ልጆች**" የተባሉት ልጆቻችን፥ በእየራሳቸውም፡ መጽሓፍ ቅዱስ፡ ሕያው የኾነበትን ሰብአዊ አካል የተላበሱት፡ እውነተኞቹ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ምንጊዜም፡ ሰው የጻፈው መጽሓፍ ቅዱስ፡ ፈጽሞ አስፈልጓቸው የማያውቀው። እንዲህም፡ የተባለላቸው። ይህንም እውነታ፡ እንዲህ በሚለው እግዚአብሔራዊው ቃላችን፡ አስቀድመን አሳውቀናል፦

**"እምድኅረ እማንቱ መዋዕል፡ ይቤ እግዚአብሔር፦ "እወዲ ሕግየ፡ ውስተ ኅሊናሆሙ፤ ወእጽሕፎ፡ ውስተ ልቦሙ። ወእከውኖሙ አምላኮሙ፤ ወእሙንቱኒ፡ ይከውኑኒ ሕዝብየ። ወኢይምህር እንከ፡ እኑ፡ ወእኅዋሁ፡ እንዘ ይብል፦ 'አእምርዎ ለእግዚአብሔር!' እስመ ኵሎሙ የአምሩኒ፤ ንኡሶሙ፥ ወዐቢዮሙ።""**

**"ከእነዚያ ወራት በኋላ፡ እግዚአብሔር፡ እንዲህ አለ፦ "ሕጌን በልቦናቸው አኖራለሁ። በልባቸውም እጽፈዋለሁ። እኔም፡ አምላክ እኾናቸዋለሁ። እነርሱም፡ ሕዝብ ይኾኑኛል። እያንዳንዱ ሰው ባልንጀራውን፥ እያንዳንዱም ወንድሙን፡ 'እግዚአብሔርን እወቅ!' ብሎ አያስተምርም፤ ከታናሹ ጀምሮ እስከታላቁ ድረስ፡ ኹሉ ያውቁኛልና።""**

(ኤር. ፴፩፥ ፴፩-፴፬፤ ዕብ. ፰፥ ፰-፲፪፤ ፲፥ ፲፰-፲፯።)

<u>አምስተኛ፤</u> በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን ውስጥ፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቻችን፡ ከእንግዲህ ወዲህ፡ እየራሳቸውን፡ "አግዓዚ፥ ዐምሓራ፥ ወይንም ክርስቲያን" በማለት አይጠሩም። እየራሳቸውን የሚጠሩት፡፡ በቀላሉ፡ "**ኢትዮጵያዊ**"፥ ወይም፡ "**ኢትዮጵያዊት**"፡ በማለት ብቻ ነው።

ይህ የኾነበት ምክንያት፡ "አግዓዚ፥ ዐምሓራ፥ ወይም፡ ክርስቲያን" የሚባለው፡ ቀድሞ፡ አረማዊ፥ ወይም፡ አሕዛብ፥ ወይም፡ ጣዖት አምላኪ፥ ወይም፡ ኢ-አማኒ (በእግዚአብሔር የማያምን)፥ ወይም፡ እንዲያውም፡ ይሁዲ፥ ወይም፡ እስላም ከኾነው መካከል እንኳ ሳይቀር፡ ስለክርስቶስ ተምሮና አውቆ፡ የተማረውንና ያወቀውንም፡ ተቀብሎትና አምኖበት፡ የጥምቀቱ ሥርዓት ተካኺዶ ሲጠናቀቅ፡ "አግዓዚ፥ ዐምሓራ፥ ወይም፡ ክርስቲያን" የሚል ስያሜ ስለሚሰሰጠው ነው።

እንዲህ እንደመኾኑ፡ ይህ፡ አማናዊ ምክንያት፡ በእርግጥ፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቻችንን ብቻ ለይቶ፡ ከዚህ ውጪ የሚያደርጋቸው ከመኾኑ በስተቀር፡ አግዓዚዎች፥ ዐምሓሮች፥ ወይም፡ ክርስቲያኖች የነበሩትንና ያልነበሩትን፥ የኾኑትንና ያልኾኑትን ኹሉ፡ በእርግጥ አካትቶ የሚመለከት እንደኾነ መገንዘቡ፡ ለማንም አያዳግትም።

አዎን! መመሪያቸው፡ ብሉይ ኪዳን ከነበረው፡ ከአይሁድ ኦሪታዊ እምነት አስቀድሞ፡ እነዚህ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቻችን፡ ዓለምን የፈጠርነውንና የምናስተዳድረውን፡ አንድ አምላክ የኾንነውን፡ እኛን እግዚአብሔርን ያመልኩ ነበረ። ይህም ማለት፡ እነርሱ፡ የእኛ የእግዚአብሔር አማኞችና እኛን እግዚአብሔርን የሚያመልኩ፡ የእኛ የእግዚአብሔር ልጆችና ካህናት (አገልጋዮች) ናቸው። ይህ ብቻ አይደለም፤ ከዚህ በተጨማሪ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ወራሾች ነጋሢዎችም ናቸው እንጂ።

ወዳጆችንን አብርሃምን አስተምሮ፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት እንዳበቃው፡ እንደታማኙ ልጃችን፡ እንደኢትዮጵያዊው ካህን ንጉሥ፡ እንደመልከ ጼዴቅ፥ እንዲሁም፡ ለእውነተኛው መልእክተኛችን፡ ለሙሴ፡ ተመሳሳዩን ምግባር ፈጽሞለት፡ ለዚያ፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ታላቅ ጸጋና ክብር እንዳበቃው፡ እንደትጉሁ አገልጋያችን፡ እንደኢትዮጵያዊው ካህን ንጉሥ፡ እንደዮቶር ኹሉ፡ ማለት ነው።

"ንግሥተ ሳባ" በሚል ስያሜ፡ በገናንነትዋ፡ እጅግ ታዋቂና ተደናቂ የኾነችው፡ ተወዳጇ ሥይምተ-እግዚአብሔር ልጃችን፡ አጼዩት ድንግል ማክዳ፡ ከላይ የተጠቀሱት፡ ስመ ጥሩዎቹ ቀደምቶቿ፡ እንዳደረጉት ኹሉ፡ እርሷም፡ የታዛዣችን፡ የንጉሥ ዳዊት ልጅ ለነበረው፡ ለእስራኤላዊው ንጉሥ ሰሎሞን፡ ዘለዓለማዊ ሕይወቱን በሚመለከት፡ ገላልጻና አብራርታ ላስረዳችው እግዚአብሔራዊው ዕውቀት፥ ላበረከተችለትም፡ የተትረፈረፈ ኢትዮጵያዊ ጸጋና በረከት፡ ሌላዩቱና መልካሚቱ፡ ኢትዮጵያዊት ተምሳሊት ናት።

በዚህ ኹሉ፡ በኢትዮጵያዊው ጸጋና በረከት ባለቤትነት መሠረት፡ በአንዱ፡ በቅዱሱ ኪዳን አጠቃላይነት፥ "ኪዳነ-ልቡና፥ ኪዳነ-ኦሪትና ኪዳነ-መንፈስ ቅዱስ" በተባሉት በሦስቱ፡ የኪዳን ማኅተሞችም አማካይነት፡ ለመላዎቹ፡ የአዳምና የሔዋን ልጆች የተሰጡትን፡ ሰባቱን ኹሉ ቃል ኪዳናት፡ ከፍጥረት መጀመሪያ አንሥተው፡ በመቀበልና በመጠበቅ፥ እስካኹንና አኹንም፡ በምድር ላይ፡ በእኛ፡ በእግዚአብሔር እምነትና አምልኮ ጸንተው የሚገኙና የቀጠሉ፡ በእርግጥ፡ የእኔ፡ **የቅዱስ ኪዳኗ ኢትዮጵያ ልጆች ብቻ ናቸው።**

አንዱ፡ የቃል ኪዳናቱ ኹሉ መካተቻ፡ "ቅዱሱ ኪዳን" በሚል ስያሜ ይታወቃል።

ሦስቱ፡ የኪዳን ማኅተሞች የተባሉት ደግሞ፡- <u>የመጀመሪያው፡</u> **በነፍስ፡** ማለትም፡ በቀደመው ዘመነ ልደት (ጥንተ ተፈጥሮ) ያገኘችሁት፡ **ኪዳነ ልቦና፥** ወይም፡ **ኪዳነ ነፍስ፥** <u>ኹለተኛው፡</u> **በሥጋ፡** ማለትም፡ በመካከለኛው ዘመነ ኦሪት ያገኛችሁት፡ **ብሉይ ኪዳን፥** ወይም፡ **ኪዳነ ሥጋ፥** <u>ሦስተኛው፡</u> **በመንፈስ፡** ማለትም በፍጻሜ ዘመነ ምሕረት ያገኛችሁት፡ **አዲስ ኪዳን፥** ወይም፡ **ኪዳነ መንፈስ ናቸው።**

ሰባቱ ቃል-ኪዳናት የተባሉትም፡ ኪዳነ አዳም ወሔዋን፥ ኪዳነ ኖኅ፥ ኪዳነ መልከ ጼዴቅ፥ ኪዳነ አብርሃም፥ ኪዳነ ሙሴና ኪዳነ ዳዊት፥ በመጨረሻም፡ በእኔ፡ በኢትዮጵያዊቷ ድንግል ማርያም እና በልጄ በወዳጄ በኢየሱስ መሲሕ፡ የተገኘው **ኪዳነ ምሕረት ናቸው።**

ከእነዚህ፡ ከአንዱ፥ ከሦስቱና ከሰባቱ፡ መለኮታውያት የቃል ኪዳናት መድበል የተነሣ ነው፡ እኒሁ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቻችን፡ ገና ከፍጥረት ጀምሮ፡ **"የእግዚአብሔር ልጆች"** በመባል ተለይተው የታወቁት፤ ኋላም፡ **"የኢትዮጵያ ልጆች"** የሚለው ስም የተሰጣቸው፤ በመጨረሻም፡ ዛሬ፡ በቀላሉ፡ **"ኢትዮጵያውያን እና ኢትዮጵያውያት"** በመባል የሚታወቁት።

(ዘፍጥ. ፯፥ ፩-፬፤ አሞ. ፱፥፯።)

<u>ስድስተኛ፤</u> እውነታው፡ ይህ ኾኖ ሣለ፡ ነገር ግን፡ ከኢትዮጵያዊነት ውጪ በኾኑትና "ክርስቲያኖች ነን!" በሚሉት ዘንድ፡ በክርስትና ስምና በእምነቱ ረገድ፡ በመላው ዓለም እየተካኼደ ባለው፡ የተለያየ፡ አሳፋሪና ነውር የተመላበት፡ የግብዝነት ድርጊት ምክንያት፡ በልጄ በወዳጄ በኢየሱስ ቃል፡ **"እምፍሬሆሙ ተአምርዎሙ! ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ!"** ተብሎ ተነግሯልና፡ የራሱ፡ የክርስትና፡ የስም አጠራሩ ብቻ ሳይኾን፡ የሃይማኖቱና የምግባሩ መልክና ይዘት፥ ክሥተትና ምንነት፡ ምን ያኽል እንደተዋረደና እንደተናቀ፡ አጠያያቂም እንደኾነ፡ በውኑ፡ ኹላችሁም አስተውላችሁታልን? (ማቴ. ፯፥ ፲፮።)

እስኪ፡ በዚህ ረገድ፡ አንድ ምሳሌን፡ ለዓይነት ያኽል ላቅርብላችሁ! ይኸውም፡ እጅግ በዝቶ ከሚገኘውና ከክርስትና ተግባር ጋር ጨርሶ ተዛማጅነት ከማይኖረው፥ ኾኖም፡ በሰዎች ጭካኔ ከተፈጸሙ በርካታ ድርጊቶች መካከል የሚገኘውን፡ አንዱን ዝክረ ነገር ብቻ ነው፡-

ያም፡ በአንድ ወገን፡ በክርስቲያኑ ዓለም ውስጥ፡ እራሷን፡ ከኃያላኑ ክርስቲያን አህጉር፡ አንዷ አድርጋ፥ "ክርስቲያናዊ" በተባለ መንግሥትና በብሔራዊ ቤተ ክርስቲያን የምትመራው፥ የምትተዳደረውም፡ የሕዝበ ክርስቲያን አገር፥ እንዲሁም፡ የጋራ ብልጽግና አገሮች ንግሥተ ነገሥታትና የተባበሩት የደሴቲቱ ነገሥታት፡ የበላይ ገዢ የኾነችው፥ "ታላቋ ብሪታንያ" በመባልም የምትታወቀው እንግሊዝ የፈጸመችውን ያሳያል።

በሌላው ወገን ደግሞ፡ "ሒንዱዎች" በሚባሉት፡ በሕንድ አገር፡ የትእልፊት አእላፋት ሕዝብ ላይ፡ በእንግሊዝ የተፈጸመባቸውን የሚያሳይ ሲኾን፡ እኒህን፡ የድርጊቱን ኹለት ገጽታዎች፡ ከፊት ለፊታችሁ አስቀምጣችሁ፥ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ፍትሕ ሚዛናችሁም፡ አነጻጽራችሁ ተመልክታችሁ፡ ርቱዕ ብያኔያችሁን፡ በየኅሊናችሁ ትሰጡ ዘንድ፡ ከእናንተ የሚጠበቅ ይኾናል።

ይህን በተመለከተ፡ አንድ ቀላል ጥያቄ አቀርብላችኋለሁ፡- እርሱም፡ ከላይ ለተነሣው ጉዳይ፡ በእናንተ በኩል፡ በእየራሳችሁ፡ ያልተዛባና የማያዳላ፡ ሚዛናዊ አእምሮ፡ በትክክል የምትሰጡት መልስ ነው። ጥያቄውም፡ እንዲህ የሚል ነው፡- "በትስብእት፡ የእኔ፡ የድንግል ማርያም ልጅ ኾኖ፡ በሰውነት በተገለጠው፡ በእግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ዓይን፡ <u>እውነተኛው ክርስቲያን፡ የትኛው ነው</u> ትላላችሁ?"

የእኛ የእግዚአብሔር ፍጡራን መኾናቸው ቀርቶ፡ በቅኝ ግዛት ሰለባነት፡ በሕንድ የትውልድ አገራቸው የሚኖሩ፡ የትእልፊት አእላፋት ሒንዱዎችን በመወከል፥ እንዲሁም፡ በክርስቶስ ሰውነት ለተከሠተችው መለኮታዊት እውነት፡ በታማኝነት ጸንቶ በመገኘት፡ ራሱን በሰማዕትነት አሳልፎ የሰጠው፡ መኀትመ ጋንዲ፡ ከወገቡ በታች ብቻ፡ ቍራጭ ጨርቅን አገልድሞ፡ በኅሊና ዳኝነታችሁ ሚዛን ፊት፡ ባዶ እግሩን፡ በአንድ በኩል ቆሟል።

በሌላው በኩል ደግሞ፡ ክርስቲያናዊት የኾነችውን፡ ታላቋ ብሪታንያንና ሕዝቧን በመወከል፡ በእነዚያ ጥቁ ሕዝቦች ላይ፡ የተለያየ ግፍን የፈጸመው፡ ክርስቲያኑ ንጉሥ ጆርጅ፡ በወርቅ የተንቈጠቈጠ የግርማ ሞገስ ልብሱን ተጎናጽፎና ጫማውን ተጫምቶ፥ ዘውዱንም ደፍቶ፡ በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ ይታያል።

ታዲያ! በእናንተ የጎሊና ዳኝነት ሚዛን፡ መዝናችሁ፡ ምን አላችሁ? እስኪ ንገሩኝ? ከኹለቱ ሰዎች፡ የትኛው ነው እውነተኛው ክርስቲያን? ራሱን፡ "ክርስቲያን" በማለት የጠራው፡ እንግሊዛዊው ንጉሥ ጆርጅ ነውን? ወይስ፡ "ክርስቲያን አይደለም!" ተብሎና አለመኾኑ ተረጋግጦ፡ "ሒንዱ" የሚለው፡ መለያ ስያሜ የተሰጠው፡ ሕንዳዊው፡ መኀትመ ጋንዲ? አዎን! ከኹለቱ ሰዎች፡ <u>እውነተኛው ክርስቲያን፡</u> የትኛው እንደኾነ፡ በእውነት ተናገሩ!

እንግዲህ፡ <u>እውነተኛው ክርስቲያን፡</u> ማንኛቸው ስለመኾናቸው፡ ለይቶ ለማወቅ ያስችለን ዘንድ፡ በዚህ ረገድ፡ ልጁ ወዳጁ ኢየሱስ መሲሕ፡ የሰጠውንና አግባብነት ያለውን፡ ከዚህ በታች የተጠቀሰውን፡ መለኮታዊ መመሪያ ልትሰሙት ያስፈልጋችኋል። ይህ፡ የልጇ፡ የእግዚአብሔር ወልድ ቃል፡ <u>እውነተኛው ክርስቲያን፡</u> የትኛው ስለመኾኑ፥ ይኸውም፡ ከብዙዎች መካከል፡ እንዲያው፡ በዳበሳ ዕድል የመረጥነው፡ የስም ክርስቲያኑ፥ ነገር ግን፡ ቅኝ ገዢው፥ ጨቋኙና ጨፍጫፊው፡ እንግሊዛዊው ንጉሥ ጆርጅና እርሱን የወከለው፡ የእንግሊዝ ሕዝብ ስለመኾኑ፥ ወይንም፡ እንዲሁ፡ ከብዙዎች መካከል፡ በዳበሳ መልክ የመረጥነው፡ ታማኙ ሒንዱው የሕንድ መሪ፡ መኀትመ ጋንዲና እርሱ የተወከላቸው፡ ቅኝ ተገዢዎቹ፥ ተጨቋኞቹና ተጨፍጫፊዎቹ፡ ሒንዱዎቹ፡ የሕንድ ሕዝብ ስለመኾናቸው ለይቶ ለማወቅ ያስችላችኋል።

ራቅ ያለውንና የባሰውን ድርጊት ለማስረዳት ያህል፡ ይህን ዝክረ-ነገር፡ ከብዙዎች መካከል፡ እንዲያው ለዓይነት ያህል፡ በዳበሳ መርጬ፡ ለምሳሌነት አቀረብሁላችሁ እንጂ፡ በካቶሊካዊቷ ቤተ-ክርስቲያን መሪዎች ቡራኬ፡ ኢጣልያዊው ካቶሊክ ሙሶሎኒ፡ በፋሺስቱ ወራሪ ጦር ኃይሉና ሠራዊቱ፡ **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥቱ ሕዝብ** ላይ፡ በሚዘገንን ጭካኔና ግፍ፡ የፈጸመውን፡ የቅርቡን ተመሳሳይ ድርጊት ማውሳቱን አጥቼውና ዘንግቼው አይደለም።

ለዚህ ርእሰ-ነገር፡ "አግባብነት አለው!" ብዬ፡ በቅድምና ያመለከትኋችሁ፡ የልጇ የወዳጇ፡ የኢየሱስ መሲሕ፡ መለኮታዊ መመሪያ፡ እንዲህ ይነበባል፡-

**"ተዐቀቡኬ! እምሓሳውያነ ነቢያት፡ እለ ይመጽኡ ኀቤክሙ፡ በአልባሰ አባግዕ፤ ወእንተ ውሥጦሙሰ፡ ተኵላት መሰጥ እሙንቱ። <u>ወእምፍሬሆሙ፡ ተአምርዎሙ።</u>**

**"ይቀሥሙሁ እምአሥዋክ፡ አስካለ!? ወእምአሜከላ፡ በለሰ!? ከማሁኬ! ኵሉ ዕፅ ሠናይ፡ ፍሬ ሠናየ ይፈሪ፤ ወእኩይሰ ዕፅ፡ ፍሬ እኩየ ይፈሪ። ኢይክል፡ ዕፅ ሠናይ፡ ፍሬ እኩየ ፈርየ፤ ወኢዕፅ እኩይ፡ ፍሬ ሠናየ ፈርየ። ኵሉ ዕፅ፡ ዘኢይፈሪ፡ ፍሬ ሠናየ፡ ይገዝምዎ፤ ወውስተ እሳት ይወድይዎ። <u>ወእምፍሬሆሙ እንከ! ተአምርዎሙ።</u>**

"አኮ ኵሉ ዘይብለኒ፡ "እግዚኦ! እግዚኦ!" ዘይበውእ ውስተ መንግሥተ ሰማያት፤ ዘእንበለ ዘይገብር ፈቃዶ፡ ለአቡየ ዘበሰማያት።

"ወብዙኃን ይብሉኒ፡ በይእቲ ዕለት፡- "እግዚኦ! እግዚኦ! አኮኑ በስምከ ተነበይነ? ወበስምከ፡ አጋንንተ አውጻእነ? ወበስምከ፡ ኀይላተ ብዙኀ ገበርነ?"

"ወይእተ ጊዜ፡ እብሎሙ፡- "ግሙራ ኢየአምረክሙ። ረኃቁ እምኔየ ኵልክሙ፡ እለ ትገብሩ ዓመፃ!"

"የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡባችሁ፥ በውስጣቸው ግን፡ ነጣቂዎች ተኵላዎች ከኾኑ፡ ከሐሰተኞች ነቢያት ተጠንቀቁ። ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ።

"ከእሾህ፡ ወይን፥ ከኵርንችትስ፡ በለስ ይለቀማልን? እንዲሁ፡ መልካም ዛፍ ኹሉ፡ መልካም ፍሬ ያደርጋል፤ ክፉም ዛፍ፡ ክፉ ፍሬ ያደርጋል። መልካም ዛፍ፡ ክፉ ፍሬ ማፍራት፥ ወይም ክፉ ዛፍ፡ መልካም ፍሬ ማፍራት አይቻለውም። መልካም ፍሬን የማያደርግ ዛፍ ኹሉ፡ ይቈረጣል፤ ወደእሳትም ይጣላል። ስለዚህም ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ።

"በሰማያት ያለውን፡ የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ፤ "ጌታ ሆይ! ጌታ ሆይ!" የሚለኝ ኹሉ፡ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም።

"በዚያ ቀን፡ ብዙዎች፡ "ጌታ ሆይ! ጌታ ሆይ! በስምህ፡ ትንቢት አልተናገርንምን? በስምህስ፡ አጋንንትን አላወጣንምን? በስምህስ፡ ብዙ ተአምራትን አላደረግንምን?" ይሉኛል።

"የዚያን ጊዜም፡ ከቶ አላወቅኋችሁም፤ እናንተ ዓመፀኞች፥ ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ።" (ማቴ. ፯፥ ፲፭-፳፫።)

እንደ ተጨማሪ ምሳሌም፡ ከኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ጋር፡ የበለጠ ተቀራራቢነት ላለው፥ ለስደት መከራ ተዳርጎ ለሚንከራተተው፡ ለቡድሃ ሃይማኖት፡ ተመሳሳይ የኾነ መግለጫ ሊሰጠው ይችል ይኾናል። በተለይ፡ ስለሕይወት እና ስለመለኮታዊቷ መንግሥት፡ ያለው ጽንሰ ሓሳብ፥ ስለተግባራዊነቱም፡ ከምሥራቅና ከምዕራብ ክርስቲያን አገሮችና ከአብያተ ክርስቲያናቶቻቸው ጋር ሲነጻጸር ማለት ነው።

ሰባተኛ፤ ለዚህ የዐዋጅ ቃሌ መነሻ ከኾነውና አኹን እየነገርኋችሁ ካለሁት ጒዳይ ጋር የተያያዘ በመኾኑ፡ ላነሣላችሁ የሚያስፈልግ፡ አንድ ዋና ቁም ነገር አለ። ይኸውም፡ መሥራቹና መሪው፡ መሓመድ የኾነው፡ የእስልምና ሃይማኖት፡ እንደሌሎቹ ሃይማኖቶች፡ በምድር ላይ የመከሠቱ ምሥጢራዊ ዓላማ ነው።

ይህ ምሥጢራዊ ዓላማ፡ ምን እንደኾነ፥ ለዚሁ ምሥጢራዊ ዓላማም፡ መንሥኤ የኾነው ዓቢይ ምክንያት ምን እንደኾነ፡ ይህን ርእሰ ነገር በሚመለከት ያለውን፡ እግዚአብሔራዊው እውነታ፡ አብራራላችኋለሁና፤ ስሙት!

አዎን! የቀደሙት፡ "ክርስቲያኖች" የተባሉት የዓለም ሕዝብ ወገኖች፡ በአንድ በኩል፡ መንፈሳውያንና ሃይማኖታውያን ተቋማት የኾኑትን አብያተ ክርስቲያኖቻቸውን፥ በሌላው በኩል ደግሞ፡ ሥጋውያንና ዓለማውያን ድርጅቶች የኾኑትን መንግሥቶቻቸውን፡ በአንድነት አስተባብረው ይዘው፡ **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** ላይ፡ ምን ሊያደርጉ፡ ዐቅደውና ዓልመው እንደነበረ፥ ያም ዕቅዳቸውና ዒላማቸው፡ ፈጽሞ ሰይጣናዊ እንደነበረ፥ ዛሬም፡ እየኾነ እንዳለና እንደቀጠለ፡ እውነታውን፡ በእርግጥ ዐውቃችሁትና ተረድታችሁት፥ ጠቅላላ ጉዳዩንም፡ በትኵረትና በማብሰልሰል ተመልክታችሁት፡ በየበኩላችሁ፡ ተገቢውን ልትፈጽሙ ይገባችኋል።

በምድር ላይ፡ ምሥጢራዊ ዓላማ ኾኖ ለተከሠተው፡ ለዚሁ፡ ለእስልምና ሃይማኖት መነሣት፡ ምክንያት የኾኑትና ከላይ የተጠቀሱት፡ የክፉው ውጥን ዓላሚዎችና ደጋፊዎቻቸው፡ ያን፡ እኩይ የዘመቻ ዓላማቸውን፡ **በቅድስት ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** ላይ ለመጀመር ተዘጋጅተው የነበረበት ጊዜ፡ ፩ኛውና ፫ኛው ምእተ ዓመተ ምሕረት ነበር።

ያም ዘመን፡ እነዚያ፡ የክፉው ውጥን ዓላሚዎችና ደጋፊዎቻቸው፡ በትዕቢታቸውና በዕብሪታቸው፡ እየራሳቸውን፡ የእኛ ከኾነችው፡ ከዚችው፡ **ከኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** ውጭ በማድረግ፡ አስነዋሪው የእነርሱ ኃያልነት፡ ከመጨረሻው ከፍተኛ የልዕልና ደረጃ የደረሰበት ጊዜ እንደነበረ፡ በኹላችሁም ዘንድ ይታወሳል።

በዚያ ዘመቻቸውም፡ ዓላማቸው፡ ይህችኑ፡ **የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያን**፡ ቢቻል፡ እንደዛሬው ኹሉ፡ በበጎ ጎኑ አንጻር ሲመለከቱት፡ ሙሉ በሙሉ፡ የእነርሱ የግዛት አካል አድርገው ለመጠቅለል፥ ምናልባት ግን፡ ያ ምርጫቸው ሊሳካላቸው ሳይችል ቢቀር፡ በክፉ ጎኑ አንጻር በተመለከቱበት ዓይናቸው፡ እርሷን፡ ከምድረ ገጽ፡ ፈጽመው ለመደምሰስ ነበረ፤ ዛሬም፡ ዓላማቸው፡ ይኸው ነው።

አኹን፡ በአንድ በኩል፡ እናንተ ልጆቼ፡ እውነተኞቹ ኪዳናውያትና ኪዳናውያን፡ ይህን እውነታ ስትገነዘቡ፡ ከቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችሁ የተነሣ፡ በእርግጥ፡ በውስጣችሁ፡ ከፍተኛ፡ የመንፈስ ማዕበላዊ ነውጥና ሁከት፥ ነበልባላዊ ቅንዓትና ኸብርም ተነሣሥቶ፡ እንደሚያጥለቀልቃችሁና እንደሚያቃጥላችሁ፥ በሌላው በኩል ደግሞ፡ እየራሳችሁን፡ በፈቃዳችሁና በምርጫችሁ፡ ከዚህ የመንፈስ ቅዱስ ልጅነታችሁ ያገለላችሁ ፍጡሮቼ ኹሉ፡ እየራሳችሁን፡ እንደገና፡ በጥልቅ በመመርመር፡ በእውነተኛ የንስሓ ዕውቀት፡ ወደእግዚአብሔሯ እውነትና ወደመንግሥታችን ለመመለስ፡ በመንፈሳዊው ንቃተ-ኅሊና እንደምትነሣሡ አውቃለሁ።

እንግዴህ፡ ሲብላላ የኖረው፥ አኹን የተከሠተውና እየኾነ ያለው እግዚአብሔራዊው እውነታ፡ ይህ በመኾኑ፡ **የዚህ፡ የ፫ተኛው የዓለም ጦርነት፡ እውነተኛው ገጽታ፥ መነሻው ምክንያትና ማስወገጃው መፍትሔ ምን እንደኾነ፡ በተብራራ መልኩና ይዘቱ፡ ይኸው፡ በዚህ የዐዋጅ ቃሌ ቀርቦላችኋልና፡ ጠንቅቃችሁ ስሙት! መስማት ብቻ ሳይኾን፡ በእምነት፡ ሕይወት አድርጋችሁ እየኖራችሁት፡ በምግባር ፈጽሙት።**

## እውነተኞቹ "የእስራኤል ልጆች"
## "የኢትዮጵያ ልጆች" ስለመኾናቸው።

እዚህ ላይ፡ ኹላችሁም፡ ልታውቁት የሚገባችሁ፡ አንድ፡ ሌላ የእግዚአብሔር እውነታ አለ፤ ይኸውም፡ **እውነተኞቹ የእግዚአብሔር ልጆች፥ እውነተኞቹ የአብርሃም ልጆች፥ እውነተኞቹ የእስራኤል ልጆች፡ እነማን እንደኾኑ፡** በትክክል የማወቃችሁና የመገንዘባችሁ ቍም-ነገር ነው። ይኼም ቍም ነገር፡ የሚያሳውቃችሁ፡ ሌላው የእግዚአብሔር እውነታ፡ "**እውነተኞቹ የእግዚአብሔር ልጆች፥ እውነተኞቹ የአብርሃም ልጆችና እውነተኞቹ የእስራኤል ልጆች፡ እኒሁ፡ የእኔዎቹ፡ የቀድሞዎቹ፥ የዛሬዎቹም የኢትዮጵያ ልጆች መኾናቸውን ነው።** የዚህም፡ አጭር ማብራሪያ፡ ይኼውላችሁ!

፩ኛ፡ እየራሳቸውን፡ "እኛ የእግዚአብሔር ልጆች፥ የአብርሃምም ልጆች፥ የእስራኤል ልጆች ነን!" እያሉ፡ የሚመጻደቁት፡ ግብዞቹ "ዕብራውያን"፥ ወይም፡ "አይሁድ" የተባሉት፡ የብሉዩ ዘመን አሪታውያን ወገኖች፡ በአብርሃም ግርዛት፥ በሙሴ ጽላትና በዳዊት ዘር አማካይነት፡ ከእኛ ከእግዚአብሔር የተሰጧቸውን፡ ሦስት ቃል-ኪዳናት፡ አምነውና አጽንተው፥ አክብረውና ጠብቀው ከመፈጸም ይልቅ፡ በእኛ ላይ በሚያካኺዱት፡ ባልተቋረጠው ክህደታቸውና ዓመፃቸው፡ ወደቀደመው የጣዖት አምልኳቸው ቀንበር መመለስን፡ ዋና ዓላማቸውና ግዳጃቸው አድርገው፡ ይህንኑ ፍላጎታቸውን፡ በተግባር ላይ ማዋላቸውን ቀጥለውበት እንደኖሩ፡ በራሳቸው የዝክረ-ነገር መጽሐፋቸው ውስጥ ሳይቀር ተመዝግቦ፡ ሲነገርና ሲነበብ የኖረ እውነታ ነው።

ከዚህ የተነሣ፡ እነዚሁ፡ ሦስቱም ቃል-ኪዳናት፡ እኛ፡ በሰውነት፡ እስከምንገለጽበት፡ እስከዘመኑ ፍጻሜ ድረስ፡ በምድር ላይ በሚርመሰመሱት፡ በሰብአውያኑ ፍጡሮቻችን መካከል፡ በባለአደራነት ተጠብቀው ሊቆዩ የሚችሉት፡ በእኛ ምርጫ፡ ለዚህ ታላቅ መለኮታዊ ኃላፊነት፡ በቅተው ባገኘናቸው፡ ከጥንት ጀምሮ፡ "የእግዚአብሔር ልጆች!" "የኢትዮጵያም ልጆች" ተብለው በሚጠሩት፡ በታማኞቹ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቻችን ዘንድ ብቻ መኾኑን ስለምናውቅ፡ እነሆ፡ እነዚሁ፡ ሦስት ቃል-ኪዳናት፡ ለእኒሁ ልጆቻችን ተሰጥተው፡ በእነርሱ፡ በ"ኢትዮጵያ ልጆቹ" ዘንድ፡ ይኸው፡ ለዝንተ-ዓለም፥ እስከዛሬና ለዘለዓለም፡ ተቀባይነትንና ተፈጻሚነትን አግኝተው ኖሩ፤ ዛሬም፡ እየኖሩ አሉ፤ ወደፊትም፡ ይኖራሉ።

በእኛ ፈቃድ፡ ወደኢትዮጵያ ልጆች፡ በአደራነት የተመለሱት፡ እነዚሁ፡ የግርዛት፥ የታቦትና የሰብኣዊ ዘር፡ ሦስት ቃል-ኪዳናት፡ የአብርሃሙ፡ በኢትዮጵያዊት ሚስቱ፡ በኬጡራ፥ የሙሴዋ፡ በኢትዮጵያዊት ሚስቱ፡ በሲጳራ፥ የዳዊቱ፡ በኢትዮጵያዊት ሚስቱ፡ በቤትሳባ፥ ከዚያም፡ በልጁ፡ በሰሎሞን አማካይነት፡ በኢትዮጵያዊቷ ንግሥት፡ በማክዳና በድንግልና ልጇ፡ በምኒልክ በኩል መኾኑ፡ በይፋ ይታወቃል።

እንዲሁም፡ ከእነዚያ፡ ከቀደሙት፡ "ዕብራውያን"፥ ወይም፡ "አይሁድ" ከተባሉት፡ የብሉዩ ኦሪታውያን ወገኖች መካከል፡ ከጥንት ጀምሮ፡ በየዘመናቱና በየምክንያቱ፡ ከእነዚሁ ቃል-ኪዳናት ጋር፡ ዐብረው የመጡት፥ "እውነተኞቹ የእስራኤል ልጆች"፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖትና ምግባር፥ እንዲሁም፡ በቅዱሱ ኪዳን ጋብቻ ከተገኘው የሥጋ ልደት የተነሣ፡ ከቀደሙት ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ጋር የተዋሓዱ በመኖራቸው፡ ያ ውሕደት፡ ኋለኛውን እስራኤላዊዉን ልጅነት፡ ለቀዳማዊው ኢትዮጵያዊ ልጅነት አብቅቶታል።

፪ኛ፡ አኹን ደግሞ፡ ከዚህ፡ ቀደም ብዬ፡ "እየራሳቸውን፡ 'እኛ የእግዚአብሔር ልጆች፥ የአብርሃምም ልጆች፥ የእስራኤል ልጆች ነን!' እያሉ፡ የሚመጻደቁት፡ 'ዕብራውያን'፥ ወይም፡ 'አይሁድ' የተባሉት፡ የብሉዩ ዘመን ኦሪታውያን ወገኖች፡ በአብርሃም ግርዛት፥ በሙሴ ጽላትና በዳዊት ዘር አማካይነት፡ ከእኛ ከእግዚአብሔር የተሰጧቸውን፡ ሦስት ቃል-ኪዳናት፡ አምነውና አጽንተው፥ አክብረውና ጠብቀው ከመፈጸም ይልቅ፡ በእኛ ላይ በሚያካኺዱት፡ ባልተቋረጠው ክህደታቸውና ዓመፃቸው፡ ወደቀደመው የጣዖት አምልኳቸው ቀንበር መመለስን፡ ዋና ዓላማቸውና ግዳጃቸው አድርገው፡ ይህንኑ ፍላጎታቸውን፡ በተግባር ላይ ማዋላቸውን ቀጥለውበት እንደኖሩ፡ በራሳቸው የዝክረ-ነገር መጽሓፋቸው ውስጥ ሳይቀር ተመዝግቦ፡ ሲነገርና ሲነበብ የኖረ እውነታ ነው።" ስላልኋቸው፡ ስለእነዚህ፡ ሰብኣውያን ፍጡሮቻችን፡ የኾነውንና የተባለውን፡ እስኪ ስሙት!

እነዚህ፡ ሰብኣውያን ፍጡሮቻችን፡ ቀድሞ፡ በሙሴ ዘመን፥ በመጨረሻም፡ በኢየሱስ መሲሕ ጊዜ፡ የእግዚአብሔር ተቃዋሚዎች፥ ከሃዲዎችና ገዳዮች ኾነው በመገኘታቸው፡ "እስራኤል"፥ ወይም፡ "የእስራኤል ልጆች" ሊባሉ የማይቻል መኾኑን በማረጋገጥ፡ በልጄ በወዳጄ፡ በኢየሱስ መሲሕ መለኮታዊ ቃል፡ ምን እንደተባሉ ታውቁ የለምን? በዚህ ረገድ የተመዘገበው፡ የአዲስ ኪዳን መጽሓፋዊ ጥቅስ፡ እንዲህ ይላል፡-

የእኛ የእግዚአብሔር ተቃዋሚዎችና ከሃዲዎች፥ ገዳዮችም ኾነው ለተገኙት፡ ለእነዚያ፡ ለቀድሞዎቹ እና ለእነዚህ፡ ለዛሬዎቹ "ዕብራውያን"፥ ወይም፡ "አይሁድ" ለተባሉት፡ ኦሪታውያን ከሳሾቹና ተከራካሪዎቹ ፈሪሳውያን፡ ልጄ ወዳጄ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ የተናገረው ቃል፡ እንዲህ የሚል ነው፡-

"'ወአንሰ፡ ዘርኢኩ በኀበ አቡየ፡ እነግር። ወአንትሙኒ፡ ዘርኢክሙ በኀበ አቡክሙ፡ ትገብሩ።'

"ወአውሥኡ፥ ወይቤልዎ፡- 'ለነሰ፡ አብርሃም አቡነ።'

"ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ፡- 'ሶበሰ ውሉደ-አብርሃም አንትሙ፡ ግብረ አብርሃም፡ እምገበርክሙ። ወይእዜሰ፡ ተኀሥሡ ትቅትሉኒ፥ ብእሴ ጻድቀ፤ ዘጽድቀ እነግረክሙ፤ ዘሰማዕኩ በኀበ እግዚአብሔር፤ ወአብርሃምሰ፡ ኢገብረ ከመዝ። አንትሙሰ፡ ትገብሩ፡ ግብረ አቡክሙ።'

"ወይቤልዎ፡- 'ንሕነሰ፡ ኢተወለድነ እምዝሙት፤ አላ አሐዱ አብ ብነ፤ ወውእቱ እግዚአብሔር።'

"ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ፡- 'ሶበሰ እግዚአብሔር አቡክሙ፡ እምአፍቀርክሙኒ ኪያየ፤ ወቃልየኒ፡ እምዐቀብክሙ፤ እስመ አነ፡ እምኀበ እግዚአብሔር ወጻእኩ፤ ወመጻእኩ፤ ወአኮ ለልየ ዘመጻእኩ፤ አላ ውእቱ ፈነወኒ። እፎ እንከ፡ ኢተአምኑ ቃልየ? እስመ ኢትክሉ ሰሚዐ፡ ነገረ ዚአየ።

"'አንትሙሰ፡ እምአቡክሙ ሰይጣን አንትሙ፤ ወፍትወቶ ለአቡክሙ ትፈቅዱ ትግበሩ። ወውእቱሰ ቀታሌ ነፍስ ሰብእ ውእቱ እምትካት፤ ወኢይቀውም በጽድቅ፤ እስመ አልቦ ጽድቅ በኀቤሁ፤ ወሶበሂ ይነብብ ሐሰተ፡ እምዚአሁ ይነብብ፤ እስመ ሐሳዊ ውእቱ፤ ወአቡሃ ለሐሰት።

"'ወአንሰ፡ እስመ ጽድቀ እነግር፡ ወኢተአምኑኒ። መኑ እምኔክሙ፡ ዘይዛለፈኒ በእንተ ኃጢአት? ወእመሰ፡ አነ ጽድቀ እነግር፡ ለምንት ኢተአምኑኒ። ዘሰ እምእግዚአብሔር ውእቱ፡ ቃለ እግዚአብሔር ይሰምዕ፤ ወበእንተ ዝንቱ፡ አንትሙሰ፡ ኢትሰምዑኒ፤ እስመ ኢኮንክሙ እምእግዚአብሔር።"

ማለትም፡ "'እኔ፡ በአባቴ ዘንድ ያየሁትን እናገራለሁ። እናንተም ደግሞ፡ በአባታችሁ ዘንድ ያያችሁትን ታደርጋላችሁ።'

"መልሰውም፡- 'አባታችንስ፡ አብርሃም ነው፤' አሉት።

"ጌታችን ኢየሱስም፡- 'የአብርሃም ልጆች ብትኾኑማ፡ የአብርሃምን ሥራ ባደረጋችሁ ነበር። አኹን ግን፥ ከእግዚአብሔርም ዘንድ የሰማሁትን እውነት የምነግራችሁን፡ የእውነት ሰው እኔን፡ ልትገድሉኝ ትፈልጋላችሁ። አብርሃም፡ እንዲህ አላደረገም። እናንተ ግን፡ የአባታችሁን ሥራ ታደርጋላችሁ፤' አላቸው።

"እነርሱም፡- 'እኛስ፡ ከዝሙት አልተወለድንም፤ ነገር ግን፡ አንድ አባት አለን፤ እርሱም፡ እግዚአብሔር ነው፤' አሉት።

"ጌታችን ኢየሱስም አላቸው፡- "እግዚአብሔር፡ አባታችሁ ቢኾንማ ኖሮ፡ እኔን፡ በወደዳችሁኝ፥ ቃሌንም፡ በጠበቃችሁ ነበር፤ እኔ፡ ከእግዚአብሔር ወጥቼ መጥቻለሁና፤ እርሱ፡ ላከኝ እንጂ፡ ከራሴ የመጣሁ አይደለሁም። እንኪያ፡ ቃሌን እንዴት ታምናላችሁ? የምነግራችሁን፡ መስማት አትችሉምና።

"እናንተማ፡ ከአባታችሁ፡ ከሰይጣን ናችሁ፤ የአባታችሁን ፈቃድ ልትፈጽሙ ትወድዳላችሁ። እርሱም፡ ከጥንት፡ የሰው ነፍስ፡ ገዳይ ነው፤ እውነት በእርሱ ዘንድ ስለሌለች፡ ለእውነት አይቆምም። ሓሰትን ሲናገር፡ ከራሱ ይናገራልና፤ ሓሰተኛ፥ የሓሰት አባትም ነውና።

"እኔንማ፡ እውነትን ስለምናገር፡ አታምኑኝም። ከእናንተ፡ ስለኃጢኣት የሚወቅሰኝ፡ ማነው? እኔ ግን፡ እውነትን የምናገር ከኾንሁ፡ ለምን አታምኑኝም? ከእግዚአብሔር የኾነ፡ እርሱ፡ የእግዚአብሔርን ቃል ይሰማል፤ ስለዚህም፡ እናንተ አትሰሙኝም፤ ከእግዚአብሔር አይደላችሁምና።'" (ዮሓ. ፰፥ ፵፬-፵፯።)

እኛ እግዚአብሔር፡ አስቀድመን፡ በነቢያችን በአሞጽ፡ "'አኮ ከመ ደቂቀ ኢትዮጵያ አንትሙ በኀቤየ፡ ደቂቀ እስራኤል!' ይቤ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ ይመልክ ስሙ።"

"ስሙ፡ 'ኹሉን የሚገዛ' የኾነ እግዚአብሔር፡ ‹የእስራኤል ልጆች! እናንተ፡ በእኔ ዘንድ፡ እንደኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁም።› አለ።" ብለን ያናገርነው፡ በዚህ ምክንያት መኾኑን፡ እንድታውቁት ይኹን! (አሞ. ፱፥ ፯።)

አዎን! ከዚህ የተነሣ ነው፡ እውነተኞቹ፡ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት ልጆቼ፡ ላለፉት ሦስት ሺህ ዓመታት፡ የሓሳውያኑን አሪታውያን አይሁድ ቅኝ ገዢነት ከተቀበሉት፡ ከክፉዎቹ ወገኖቻቸው ተለይተው፡ "ይህን፡ የሓሳውያኑን አሪታውያን አይሁድ ቅኝ አገዛዝ አንቀበልም!" በማለት፡ እየራሳቸውን ነጻ አድርገው፡ "እውነተኞቹ እስራኤል፥ የእስራኤልም ልጆች፡ እኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት የኾንነው፡ የኢትዮጵያ ልጆች ነን እንጂ፡ ዛሬ፡ ራሳቸውን፡ 'እስራኤል ነን!' የሚሉት፡ አይሁድ አይደሉም!" እያሉ፡ ምንጊዜም፡ እንዲህ፡ እንደእኔ፡ በዐዋጅ የሚናገሩት።

## የእስልምና ሃይማኖት፡
## በምድር ላይ የመከሠቱ ምሥጢራዊ ዓላማ።

እነዚያ፡ የክፉው ውጥን ዓላሚዎችና ደጋፊዎቻቸው፡ በ፩ኛውና ፫ኛው ምእተ ዓመተ ምሕረት ግድም፡ ተዘጋጅተውበት የነበረው፡ ያ የጥፋት ዘመቻቸው፥ እርሱም፡ ቀደም ብዬ እንደተናገርሁት፡ ይህችኑ፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችንን፡ ቢቻል፡ እንደዛሬው ኹሉ፡ ሙሉ በሙሉ፡ የእነርሱ የግዛት አካል አድርገው ለመጠቅለል፥ ምናልባት ግን፡ ያ ምርጫቸው ሊሳካላቸው ሳይችል ቢቀር፡ እርሷን፡ ከምድረ ገጽ፡ ፈጽመው ለመደምሰስ እንደነበረ፡ የማይታበል እውነታ ነው።

ያም የዘመቻ ዝግጅት የተጀመረው፡ በአንድ ወገን፡ በሮማዊው የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ንጉሠ ነገሥታዊ መንግሥት፥ በሌላኛው ወገን ደግሞ፡ በባዛንቲኑ የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ንጉሠ ነገሥታዊ መንግሥት፡ ጥምር አዝማችነት ሲኾን፥ የእግዚአብሔርና የእኔ፡ የድንግል ማርያም ልጅ የኾነውን፡ ኢየሱስ መሲሕን "አንቀበልም" በማለት፡ ለአረማውያኑ ሮማውያን አሳልፈው፡ ለስቅላት ሞት የዳረጉትን አይሁድን ጭምር ያስተባበረ፥ አረማውያንንም ሳይቀር ያሳተፈ ነበረ።

ከላይ ለተወሳው፡ በመላው የዓለም አብያተ ክርስቲያናትና የዓለም መንግሥታት ኅብረት ለተቀነባበረው፡ ለዚህ፡ "ሃይማኖታዊ" ተብዬው ጠንቀኛና የርኵሰት ዘመቻ፡ በቀዳሚ መሪነት፡ ቀንደኛዎቹ መንገድ ጠራጊዎችና አቀናጆች ኾነው፡ የፊታውራሪነቱን ሚና ይዘው የሚያጋፍሩት፥ ዛሬም፡ እያጋፈሩ ያሉት፡ የግብፅ ቅብጣዊት ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን "ጳጳሳት" የተባሉት፡ የበላይ ኀላፊዎቿ መነኮሳት ናቸው።

በዚያን ጊዜ የተከሠተው ያ ድርጊት፡ ከዚያን በፊት፡ ከብዙ ዘመናት አስቀድሞ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን ላይ፡ ተመሳሳይ የኾነ ውጤትን እንዲያመጣ ታቅዶ፡ የተፈጸመ ሌላ የዘመቻ ሴራ እንደነበረ፣ ያም የዘመቻ ሴራ፡ "በተወሰነ ደረጃ፡ 'ተሳክቷል!' ለማለት የሚያስደፍር፡ በአይሁድ የተካኼደው እንደነበረ፡ እዚህ ላይ፡ ሊጤን ይገባል።

እነዚህ፡ የተጠቀሱት፡ የጥፋት መልእክተኞች፡ ሰላማዊና ታማኝ፥ እግዚአብሔርን አምላኪና አፍቃሪ በኾነው፡ በእኛዪቱ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን ሕዝብ ላይ፡ ይህን መሰል፡ እጅግ ከባድና ተንኮልን ያዘለ፥ በጽኑዕ ኃጢአተኛነትም የሚካኼድ፥ ሥውር የጥቃት ደባን ለመፈጸም፡ እንዲህ፡ በጥምረት ያነሣሣቸው ምክንያት፡ ከቶ ምንድን እንደኾነ ለመረዳት፡ ለእውነተኛ መንፈሳዊ ሰውነት የሚያዳግተው አይደለም።

ለዚህ የከረረ ጥላቻ፡ አሳማኝ የኾነ፡ ብቸኛና ምክንያታዊ ምላሽ ሊገኝ የሚችለው፡ ከሌላ ሳይኾን፡ ከዚህ ከሚከተለው፡ መለኮታዊ እውነት ነው። ይኸውም፦ <u>እኔ ኢትዮጵያ፡</u> ምንጊዜም፡ በማይናወጸው ቀራጥ አቋሜ፡<u>"እስመ ለእግዚአብሔር መንግሥት፤</u> ወውእቱ ይኴንኖሙ ለአሕዛብ።" "<u>መንግሥት፡ ለእግዚአብሔር ናትና፤</u> እርሱም፡ አሕዛብን ይገዛል።" የሚለውን መለኮታዊ ቃል፡ ታማኞቼ ልጆቼ፡ ከኹሉ አብልጠው፥ ያላንዳች ማመንታትም፡ እስከ ዘለቄታው ድረስ ተከትለው እንዲፈጽሙት በማስቻል፥ <u>"የእግዚአብሔር መንግሥት" ኾኜ በተገለጥሁበት እኔነቴ፡ የእኔ የኾነውን ፍጥረታት-ዓለማቴን፡ በመልካም ሕይወት ለማኖር፡ ባለኝ መለኮታዊ ማንነቴና በትስብእታዊው ምንነቴ፡ በመጽናቴ ብቻ ነው።</u> (መዝ. ፳፩፥ ፳፰።)

አዎን! በዚህ፡ በመለኮታዊው የእውነት አቋም መሠረት፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቼ ብቻ፡ እየራሳቸውን፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ምንነታቸውና ማንነታቸው አጽንተው፥ በዚህ አቋማቸውም፡ ፍጹም ታማኞች ኾነው፡ በእውነተኛነታቸው ቀጠሉ።

ነገር ግን፡ ቀደም ብዬ እንደገለጽሁት፡ በምድር ላይ ያለው፡ በአጠቃላይ፡ መላው የሰው ዘር ወገኖች፥ በተለይም፡ የተቀረው፡ የ"ክርስቲያኑ ዓለም" ተብዬዎቹ፡ አሪታውያኑን አይሁድንና ኦርቶዶክሳውያኑን ግብፆችን በማስቀደምና አብነት በማድረግ፡ በእኛ፡ በእግዚአብሔር የተመሠረተውን፡ ይህን፡ መለኮታዊ የሥርዓተ መንግሥት አቋም ትተው፡ ፈጽመው ገሸሽ አሉ።

ይህ ብቻ ሳይኾን፡ ከላይ የተጠቀሱት፡ እነዚያው፡ መላው የክርስቲያኑ ዓለም ሕዝቦች፡ ባለመለያየት ተባብረው፡ በመለኮታዊው ሥርዓት፡ አንዲት የኾነችውን፡ የእኛዪቱን ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ለኹለት በመክፈል፡ አንደኛውን፡ “መንፈሳዊ” ወይም “ቤተ ክርስቲያን” ብለው በመሠየም፡ በቤተ ክህነት የማዕርጋት መዋቅር እንዲመራ ሲያደርጉ፥ ኹለተኛውን ደግሞ፡ “ሥጋዊ” ወይም “ዓለማዊ አገዛዝ” በሚል ስያሜ በመጥራት፡ ኢአማንያን በኾኑ የጨዋዎች መንግሥት እንዲካኼድ አድርገዋል።

"የቀደሙት ክርስቲያኖች" ተብለው የሚጠሩት፡ እነዚያ የክርስቲያኑ ዓለም ወገኖች፡ ያደረጉትን፡ ያን፡ ተመሳሳይ፡ የጥቃት ዘመቻ፡ በሃይማኖታዊ አቋምነታቸው፡ "ኦርቶዶክስ፥ ካቶሊክና ፕሮቴስታንት" የተባሉት የዛሬዎቹ መሰሎቻቸው አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ፡ ባኹኑ ሰዓት፡ የሚያደርጉትን እዩት!

እነዚሁ፡ የዛሬዎቹ አብያተ ክርስቲያናት፡ ከቀደሙት እንደተማሩትና እንዳስለመዱት፡ አቻዎቻቸውና ተባባሪዎቻቸው ከኾኑት፡ ከዓለማውያኑ የመንግሥታቱ ድርጅቶች ጋር በመመሣጠር፡ ተዳምረው፡ የጥፋታቸው ጥንተ ዒላማና ሰለባ በኾነችው፡ በዚችው፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን ላይ፡ በአዲስ መልክና በጽኑ ይዘት ማካኼዳቸውን ቀጠሉበት።

ይህኛውን አዲሱን ዘመቻ፡ ከቀድሞው ለየት የሚያደርገው፥ ደግሞም ለፍጥረት ኹሉ፡ በጣሙን የሚያስገርመው፡ ትብብሩ፡ አይሁድን፥ አሕዛብንና አረማውያንን ብቻ ሳይኾን፡ በይበልጥና በገሃድ፡ በኢትዮጵያ፡ የግብፅ ቅብጣዊት ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቅርንጫፍ የኾነችውን፡ የዛሬዪቱን፡ የኢትዮጵያ ኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ጨምሮ ያካተተ መኾኑ ነው።

በሰው ልጆች ህልውና ውስጥ፡ እስከዛሬ ባለፈው፥ አኹን ባለውና ወደፊትም እየተከታተለ በሚደርሰው የዘመን ኺደት፡ ግፍ የተመላበት፡ የክፋትና የኃጢአት፥ ይህን ዓይነቱም ተመሳሳይ ድርጊት መፈጸሙ፥ ኹኔታውም ከዕለት ወደዕለት እየተባባሰ መቀጠሉ፡ ለምን እንደኾነ ልታውቁት የሚገባ እውነታ ነው።

መልሱ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን ላይ፡ እስከዛሬ ሲፈጸም የኖረውን፥ ዛሬም፡ እየተካኼደ ያለውን ደባና ጥቃት አጋልጦ በሚያሳየው፡ እንዲህ በሚለው፡ በእግዚአብሔር ቃለ ትንቢት ውስጥ ተጽፎ ስለሚነበብ፡ ይህንኑ ቃል፡ በአንክሮና በተዘክሮ፥ በትኵረትና በተመሥጦ አዳምጡት! አስተውሉትም!

"ለምንት አንገለጉ አሕዛብ? ወሕዝብኒ ነበቡ ከንቶ? ወተንሥኡ ነገሥተ ምድር። ወመላእክትኒ ተጋብኡ ምስሌሆሙ ኅቡረ፤ ላዕለ እግዚአብሔር፥ ወላዕለ መሢሑ፡- 'ንበትክ እምኔነ ማእሰሪሆሙ! ወንገድፍ እምላዕሌነ አርዑቶሙ!' ..."ወእግዚአብሔር ይሣለቅ ላዕሌሆሙ፤ ሶበ ይነብቦሙ በመዓቱ፥ ወበመዓቱ የሀውኮሙ። ..."'አንሰ ተሠየምኩ ንጉሠ በላዕሌሆሙ፤ በጽዮን፡ በደብረ መቅደሱ፤ ከመእንግር ትእዛዞ ለእግዚአብሔር። እግዚአብሔር ይቤለኒ፡- ‹ወልድየ አንተ! ወአነ ዮም ወለድኩከ! ሰአል እምኔየ፡ እሁብከ አሕዛበ፡ ለርስትከ። ወምኵናኒከኒ እስከአጽናፈ ምድር። ወትርዕዮሙ በበትረ ኀጺን፤ ወከመንዋየ ለብሓ ትቀጠቅጦሙ።›' "ወይእዜኒ፡ ነገሥት ለብዉ! ወተገሠፁ ኵልክሙ፡ እለ ትኴንንዋ ለምድር! ተቀነዩ ለእግዚአብሔር በፍርሀት! ወተሓሠዩ ሎቱ በረዓድ! አጽንዕዋ ለጥበብ፡ ከመኢይትመዐዕ እግዚአብሔር! ወኢይትትሀጕሉ እምፍኖተ ጽድቅ! ሶበ ነድደት ፍጡነ መዓቱ። "ብፁዓን ኵሎሙ፡ እለ ተወከሉ ቦቱ።"

"አሕዛብ ለምን ጉባኤ አደረጉ! 'የእግዚአብሔር ወገኖች ነን!' የሚሉ ሕዝቦችስ ተሰባሰበው፡ ለምን፡ ስለከንቱ ነገር ይነጋገራሉ? እነዚህ የምድር መንግሥታት፥ ከእነርሱም ጋር ገዢዎችና ባለሥልጣኖች በአንድነት ተባብረው፡- "ኑ! እኛን ያሠሩበትን ገመዳቸውን፡ ከእኛ እንበጥስ! በላያችን ያኖሩትንም ቀንበር፡ አውርደን እንጣል!' እያሉ፡ በእግዚአብሔርና በመሢሑ ላይ፡ በክህደትና በዓመፅ ተነሣሡ!

"በሰማያት የሚኖረው እግዚአብሔር ግን፡ ይሥቅባቸዋል፤ ይሣለቅባቸዋልም። በቍጣው ይናገራቸዋል፤ በመዓቱም ያውካቸዋል። የእግዚአብሔርን ትእዛዙን እነግራቸው ዘንድ፡ የመቅደሱ ተራራ በኾነችው፡ በጽዮን፡ በላያቸው፡ ንጉሥ አድርጎ ለሾመኝ ለእኔ፡ እርሱ እግዚአብሔር፡ እንዲህ ይለኛል፡- 'አንተ፡ እኔ ዛሬ የወለድሁህ ልጄ ነህ! ለምነኝ! አሕዛብን፡ ለርስትህ፥ ግዛትህንም፡ እስከምድር ዳርቻ እሰጥሃለሁ። ደጋጎቹን፡ በመልካሙ በትረ መንግሥትህ ትጠብቃቸዋለህ፤ ክፉዎቹንም፡ እንደሸክላ ሠሪ ዕቃ ትቀጠቅጣቸዋለህ።'

"እንግዴህ፡ እናንተ፡ የዓለም መንግሥታት መሪዎችና ሕግ አስፈጻሚዎች የኾናችሁ ኹሉ፡ ልብ አድርጉ! በምድር ላይ ባሉ አህጉር ኹሉ፡ አማካሪዎችና ሕግ አውጪዎች፥ ሕግ ተርጓሚዎችና ፈራጆች የኾናችሁ ኹሉ፡ ተገሠፁ! ኹላችሁም፡ ለእግዚአብሔር፡ በፍርሃት ተገዙ! በፍርሃት በመገዛታችሁም፡ ደስ ይበላችሁ! ከእርሱ የእውነት መንገድ በመውጣታችሁ፡ እርሱ እንዳይቈጣ፥ ቍጣውም ፈጥና፡ በላያችሁ እንዳትነድድባችሁ፡ የእግዚአብሔርን እውቀትና ጥበብ አጽንታችሁ ያዙ!

"በእግዚአብሔር የታመኑና የተማመኑ ኹሉ፡ ብፁዓን ናቸው።"

(መዝ. ፪፥ ፩-፲፪።)

ይህን በመሰለ ወሳኝ ወቅት ነበረ፡ መሓመድ፡ እስልምናን አንግቦ፥ ኃይልን ታጥቆና ሰይፍን ጨብጦ፡ በዐረብ ምድረ በዳ እንዲነሣ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ፡ ፈጣሪና አምላክ የኾንነው፡ እኛ፡ እግዚአብሔር የፈቀድነው።

ለምን ፈቀድን? <u>መሓመድ፡ በዐረብ ምድረ በዳ፡ እስልምናን አንግቦ፥ ኃይልን ታጥቆና ሰይፍን ጨብጦ፡ ለምን፡ በድንገት ተነሣ? እንዲነሣ፡ መንሥኤ የኾነው ምክንያትስ፡ ከቶ ምንድር ነው?</u>

<u>የእነዚህ ጥያቄዎች መልስ፡ በምንታዌነት የሚገለጽ፡ አንድ እና አንድ ብቻ ነው። እርሱም፡-</u>

<u>ቀዳሚው፡- በቀጥታ፡ በእኛ በእግዚአብሔር ላይ፡ በጠላትነት በመነሣሣት፥ በተለይም፡ በእኔ፡ በቅድስት ድንግል ማርያም እና በተወዳጁ ልጄ፡ በኢየሱስ መሲሕ፡ የሥጋ መሥዋዕትነትና የደም ቤዛነት ታድሳ የጸናችውን፥ ይህችን፡ ለ፯፻፳፱ ዓመታት ዕድሜዋ የበቃችውን፥ ጥንታዊቷን፥ የዛሬዪቷንና ዘለዓለማዊቷን፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችንን፡ በአስፈሪው የዕልቂት ዘመቻቸው፡ ሊያጠፏት ለተዘጋጁት፡ ለእነዚሁ፡ የጥፋት ግብረ-ዐበሮች፡ የእየራሳቸውን የአጥፊነት ዋጋቸውን፡ ለእየራሳቸው የሚከፈሉበትን ቅጣታቸውን እንዲቀበሉ ማድረግ ሲኾን፥</u>

<u>ተከታዩና መጨረሻውም፡ በዚህ ቅጣት አማካይነት፡ ይህችኑ፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችንን፡ ከእነዚሁ፡ የክፋትና የጥፋት አበጋዞች፡ ለምንጊዜውም ሠውሮ ለመጠበቅ እና ተከላክሎ ለማዳን ነው።</u>

እውነታው፡ ይህ መኾኑ፡ "ኢትዮጵያዊ፥ ኢትዮጵያዊት ነኝ!" የሚለውን፡ ይህን፡ የዛሬውን ከሃዲና ዐመፀኛ፥ አመንዝሪና ክፉ ትውልድ ጨምሮ፡ በመላው የዓለም በሚርመሰመሰው፥ ይልቁንም፡ "ክርስቲያን ነኝ!" እያለ በሚመጻደቀው ሕዝብ ዘንድ ኹሉ፡ በይፋ የታወቀ ይኹን!

አዎን! ከዚህ የተነሣ፡ ከይሁዲው ኾነ ከክርስቲያኑ ዓለም መካከል፡ ከሃዲና ዓመፀኛ፥ ክፉና አመንዝራ ኾኖ ለተገኘ የሰዎች ትውልድ ኹሉ፡ መቅጫ በትር ይኾነን ዘንድ፡ ዕድሉ ኾኖ ላዘጋጀነው፡ ለእስልምና ኃይል፡ መሥራችነትና መሪነት የመረጥነው መሓመድ፡ ሃይማኖታዊ ምግባሩን፡ በሥራ ላይ ለማዋል መሠረት ያደረገው ቋሚ መመሪያ፡ "እግዚአብሔር፡ የኹሉ በላይ፥ ገዢና መሪ ነው!" የሚለውን መሠረታዊዉን የመለኮት ሥርዓተ መንግሥት በመከተል ሲኾን፤ ማለትም፡ ራሱ፡ የእስልምና ሃይማኖት፡ የኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥትነትን ተቋም፡ በመሠረቱ፡ እንዳለ ተቀብሎ፡ ሥርዓቱን፡ ለራሱ፡ እንደዋና መመሪያ በማድረግ፡ ሙሉ በሙሉ፡ መጠቀም ብቻ ሳይኾን፡ እስከዛሬ ድረስ፡ ይህንኑ ተልእኮውን፡ እግዚአብሔራዊዉን ሥርዓት፡ በይፋ ያፈረሰውን ክርስቲያኑን ወገን ጨምሮ፡ ወደተቀረው ዓለም በሙሉ፡ እነሆ፡ በሰይፍ ኃይል እያስፋፋ መኾኑ፡ ይኸው፡ በገሃድ የሚታይና የሚታወቅ ነው።

"ለምን፡ እንዲህ ኾነ?" ለሚለው ጥያቄ፡ ምክንያቱን የያዘው መልስ፡ "መሓመድ፡ **ከኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን** ጋር፡ እጅግ ቀደም ያለና ሥር የሰደደ፡ የማንነት መሠረትና የሥጋ ዝምድና ብቻ ሳይኾን፤ ስለእኛዪቱ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት**፡ ጥልቅና ሰፊ የኾነ፡ አጠቃላይ ዕውቀት ስለነበረው ነው!" የሚል ነው።

ለዚህ ነበረ፡ በትውልድ አገሩ፡ በዓረብ ምድር ውስጥ፡ ገና በመጀመሪያ፡ በሃይማኖት ተቃዋሚዎቹ በኩል፡ ጥቃት ሲደርስበት፡ ራሱ ወደሚያውቃትና ወደሚያምንባት፥ ለእነርሱም፡ የተሟላ መጠለያን እንደሚያገኙ ወዳረጋገጠላቸው፡ **ወደኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን** እንዲሸሹ፡ ቤተሰቡንና ተከታዮቹን፡ የመራቸው።

መመሪያው፡ በዚህ ብቻ አላበቃም። መሓመድ፡ በእርሱ ጊዜ ለነበሩት፥ ለወደፊቶቹም ተከታዮቹና አማኞቹ፡ እጅጉን አጥብቆ፡ በጽኑ የአደራ ኑዛዜ፡ የሰጣቸው፡ የትእዛዝና የማስጠንቀቂያ ቃል አለ። ይኸውም፡ "**ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቻችን፡ ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን፡ ያላቸውን እውነተኛነታቸውንና ታማኝነታቸውን እስካላጓደሉ ድረስ፡** በ**ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን** ስም በምትታወቀው ምድር እና በእኒሁ ልጆቻችን ላይ፡ መቼም ቢኾን፡ 'ጂሃድ' የሚሉትን የሃይማኖት ጦርነት እንዳያውጁባቸው፡ የሚያሳስበው ቃሉ ነው።

እንዲያውም፡ ይህንኑ ሃይማኖታዊ ቃሉን በማጽናት፡ እኒሁ፡ **ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቻችን**፡ መለኮታዊው ጥበቃና ጥላ ከለላነት በማይለያት አገራቸው የሚኖሩትን፡ መልካሙን ህልውናቸውን ይቀጥሉ ዘንድ፡ በእግዚአብሔር ሰላም እንዲተዉዋቸው፡ አጥብቆ አሳሰባቸው እንጂ።"

ኢትዮጵያንና የእስልምናን መነሣት በሚመለከት የተገለጸው፡ ይህ መለኮታዊ እውነታ፡ በእርግጥ እውን ኾኖ፡ በገሃድና በግዝፈት የተፈጸመ ስለመኾኑ፡ በማንም ዘንድ፡ ሊካድ የማይቻል፡ ታሪካዊ ክሥተት ነው። ይኸውም፡ የጥፋቱ ዐድመኞች በኾኑት፡ በእነዚያ፡ በክርስቲያኑ ዓለም አገሮች ላይ የተመዘዘው፡ ይህ እስላማዊ ሰይፍ፡ በስሜ ከተጠራችው፡ ከብሔረ-ኢትዮጵያ በቀር፡ እያንዳንዳቸውን፡ በተከታታይ፡ አንድ በአንድ፡ እየቀላ፡ ከሥልጣኑ ሥር ሲያንበረክካቸውና ሲዘርራቸው፡ በይፋ መታየቱና መረጋገጡ ነው።

ለመኾኑ፡ ይህ ዓይነቱ አስደንጋጭ፡ የቅጣት መቅሠፍታዊ ማዕበልና ነበልባላዊ የእሳት ቃጠሎ፡ እያየለ የተካኼደባቸው፡ የየክርስቲያናቱ አገራት ግዛቶችና ይዞታዎች፥ እንዲኹም ከተሞች፥ ማእከላትና ክርስቲያናዊው ከፍተኛ የሥልጣኔ እንቅስቃሴ የሚታዩባቸው መዲናዎች፥ አብያተ ክርስቲያናትና የንጉሠ ነገሥታት መንግሥታት ምድሮች፡ እነማንና የትኞቹ እንደኾኑ፡ በኹላችሁም ዘንድ የታወቁ አይደሉምን? አዎን! ናቸው።

እነርሱም፡ ከየመን ጀምሮ፡ የዐረብ አገርን ያካተተውን፡ የመካከለኛውን ምሥራቅ፥ የሃይማኖት እምብርት የኾነችውን፡ ኢየሩሳሌምን፥ ግብፅንና ዝነኛዋን፡ የክርስትና ትምህርት ማዕከል የኾነችውን፡ የእስክንድርያን ከተማና ልብያን ጨምሮ፡ መላውን፡ የሰሜን አፍሪቃ አህጉርን፥ ደግሞም፡ ፋርስንና አካባቢዎቿን፥ እንዲሁም፡ በከፊል እስከሕንድ የሚዘልቀውን፥ "ታናሽ እስያ" የሚባለውን፡ የቅርብ ምሥራቅን፥ እንዲያውም፡ የሮማ እና የግሪክ፡ ንጉሠ ነገሥታዊ፡ ሰፊ ግዛት የኾነው፡ የባዛንቲን መንግሥት፡ መናገሻ ከተማን፡ ቍስጥንጥንያን፥ እርሷም፡ ኋላ፡ ስሟ ተቀይሮ፡ እስከዛሬ፡ የእስላማዊዋ ቱርክ፡ መዲና የኾነችውን፡ 'ኢስታንቡል'ን፡ አጠቃልለው ይዘው የነበሩት ናቸው።

እነዚያም፡ እንደዛሬዎቹ መሰሎቻቸውና ወራሾቻቸው ኹሉ፡ በሰይጣናዊው ፈሊጣቸውና በረቀቀው ዕብሪታቸው፥ ዐምባ-ገነንነታቸውና ማናለብኝነታቸው፥ ግፋቸውና ጭቆናቸው፡ የዋሁን፡ የእግዚአብሔርን ሰብአዊ ፍጡራችንን፡ ይገዙ የነበሩት፡ እየራሳቸውን፡"ክርስቲያን እና አይሁድ ነን!" የሚሉት ወገኖች ናቸው።

እኒህ ኹሉ አገሮችና የሕዝብ ወገኖች፥ አብያተ ክርስቲያናትና መንግሥታት፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያችንን ለማጥቃትና ለማጥፋት፡ በአንድነት ተባብረው፡ ደባን የፈጸሙ፥ ሊፈጽሙም የተዘጋጁ ኾነው፡ በመለኮታዊው የዳኝነት ዓይንና የፍርድ ሚዛን፡ ተገኝተው እንደነበረ እሙን ነው።

በዚህ ረገድ፡ እኒሁ አገሮችና የሕዝብ ወገኖች፥ አብያተ ክርስቲያናትና መንግሥታት፡ ጥፋተኞች ኾነው ስለተገኙ፡ ርኅራኄና ምሕረት ባልነበረው፥ አኹንም፡ በሌለው፥ ገና እንደተመዘዘና ሊቆራርጥ እየተምዘገዘገ ባለው፥ ምሕረት በሌለውና በጨካኙ እስላማዊ ሠይፍ ሥር፡ አንድ በአንድ፡ በመከታተል ሊወድቁ ችለዋል።

የእኛዪቱ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ግን፡ የዛሬው ትውልዷ ቤተ-ሕዝብ፥ ቤተ-ምልክናና ቤተ-ክህነት፡ በቅዱሱ ኪዳናችን ላይ ከፈጸመው፡ የክህደትና የዓመፅ፥ የምንዝርናና የክፋት ኃጢኣቱ፡ በንስሓ ለመመለስ ካለመፍቀዱ የተነሣ፡ እንዲህ፡ በልዩ ልዩ መከራና ችግር እየተሠቃየ ባለበት ጊዜ እንኳ፡ ይኸው፡ በምንም ሳትነካ፥ እንዲያውም፡ በበለጠ ታውቃ፥ የማንነቷንና የምንነቷን አምላካዊ ህልውናዋን፡ በመለኮታዊው ሥርዓቷ፡ እነሆ! እስከዛሬ ጠብቃና አጽንታ እየኖረች አለች። እንደዚሁ ኹሉ፡ ዛሬና ወደፊት፥ ለዘላለሙም ትኖራለች።

ከዘር ጠላቶቿ ለሚደርስባት፡ ለዚሁ ለማያቋርጠው የግፍ ጥቃቷ፡ ቅዱሱን ኪዳን ጠብቀው ከሚገኙት የልጆቿችን ታማኝነት የተነሣ፡ የእኛ፡ መለኮታዊ የፍትሕ ርትዕ ጥበቃ ስለማይለያት፡ በዚሁ ህልውናዋ ትቀጥላለች። ለዚህ መለኮታዊ እውነታ፡ ሙሉ ማስረጃ የሚኾነው ማረጋገጫ፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን፡ እስካኹን ድረስ፡ ከተቃዋሚዎቿ የሚደርስባትን ጥቃት ተቋቊማ፥ ሙሉ ነጻነቷንና ሰላሟን፡ አጽንታ ለመኖር መቻሏ ነው።

በፀረ-እግዚአብሔርነታቸው፡ ተቃዋሚዎቻችን ኾነው የተገኙት፡ የእነዚሁ፡ የቀደሙት መሰሎቻቸውና አውራሾቻቸው፡ በዚችው፡ **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን** ላይ ስለፈጸሙት፥ ነገር ግን፡ ሳይሠምርላቸው ስለቀረው ጥቃት፡ አንዳችም ጸጸት ሳይሰማቸው፡ ዛሬም፡ ተመሳሳዩን ዓይነት ጥቃት ለመፈጸም ለሚቃጡት፡ በዓለም ዙሪያ፡ "ክርስቲያን ነን!" በማለታቸው ብቻ፡ በዚሁ ማንነታቸው ለታወቁት ሓሳውያን ወገኖች ኹሉ፡ ተደጋግሞ ቢነገራቸውም፡ ሊቀበሉት ያልፈለጉት፡ አንድ ቍም ነገር አለ፤ ይኸውም፡ ይህችው፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን**፡ በዚህ ረገድ፡ ያንኑ፡ መለኮታዊ የዳኝነት ፍርዷን፡ እንዳለፉት ጊዜያት ኹሉ፡ ዛሬም፡ ፍትሓዊና ርቱዓዊ በኾነው መልኩና ይዘቱ፡ መስጠቷን የማታቋርጥ መኾኗ ነው።

እዚህ ላይ፡ በቀላሉ፡ ሊጠቀስ የሚያስፈልገውና የሚገባው፥ አግባብነት ያለውም፡ አንድ፡ ዋናና አንዳኝ የኾነ ጉዳይ አለ፤ ይኸውም፡ አውሮጳ ውስጥ የሚገኘውና ተቀማጭነቱ ጀኔቫ የነበረው፡ የዓለም መንግሥታት ማኅበር፡ "ኦርቶዶክስ፣ ካቶሊክና ፕሮቴስታንት" በሚሉ ስያሜዎች በተከፋፈለችው፡ በቅርቢቱ፡ ቤተ ክርስቲያን ቡራኬ ሰጪነትና "ዩናይትድ ስቴትስ" በተባለችው፡ በሩቂቱ አሜሪካ ተባባሪነት፡ **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን** ላይ ያካኼደውን፡ ተመሳሳይ የወረራ ዘመቻን የሚያወሳውና የአጭር ጊዜ ትዝታ ኾኖ የቆየው ዝክረ-ነገር ነው።

ይህ፡ በዚህኛው ጊዜ፡ በዚህ ረገድ የተከሠተው፡ የመለኮታዊው ዳኝነት እውነታ፡ ያን የሚያህለውንና ያን የመሰለውን፡ ታላቅና አሠቃቂ የሕይወት ዕልቂትንና የንብረት ውድመትን ያስከተለውን፡ **የኹለተኛው የዓለም ጦርነት መነሣትን** የሚመለከት ይኾናል።

አዎን! **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን** ላይ፡ የግፍ ወረራንና ጥቃትን በፈጸሙት፡ በእነዚሁ፡ ክፉ አድራጊዎች ላይ የተገለጠው፡ መለኮታዊው የዳኝነት ፍርድ፡ በሌላ ሳይኾን፡ የራሳቸው በኾኑት፡ በጀርመኑ የናዚ መሪ፡ በአዶልፍ ሂትለርና በጣሊያኑ ፋሺስት መሪ፡ በቤኒቶ ሙሶሎኒ፥ እንዲሁም፡ በአረማዊው የጃፓን ጦር፡ ወታደራዊ ጀብደኞች ኅብረት ተወጥኖና ተካኺዶ፡ መጠናቀቁ ነው።

ከቀድሞው ስሕተቱ ያልተማረው፥ መማርንም ምንጊዜም የማይፈልገው፡ መንፈሳዊውና ሥጋዊው የዓለም ዐቀፍ ኅብረተሰብ፡ ዒላማውና ሰለባው በኾነችው፡ **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን** ላይ፡ ዛሬም፡ ያንኑ፡ የማያቋርጠውን፡ ተመሳሳይ፡ የጠላትነት አጥቂ ዘመቻውን፥ እንዲያውም በጠነከረና በረቀቀ መንገድ፡ በጽኑ እያፋፋመ እንደሚገኝ፡ ይኸውና፡ ፍጥረት ኹሉ፡ የዓይን ምስክር ኾኖ፡ ይመለከታል።

ነገር ግን፡ የዛሬዎቹ ሜረኞች፡ በአንድ በኩል፡ በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን፥ እንዲሁም፡ በግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንና በኢትዮጵያ ምድር፡ የዚችው፡ የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን፡ ቅርንጫፍ የኾነችው፡ የኢትዮጵያ ኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቀንደኛ አባልነት፡ ራሳቸውን "የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት" ብለው በሚጠሩት ሸንጎ ሲደገፉ፤ በሌላ ጎኑ ደግሞ፡ ከዚህ ቀደም፡ "የዓለም መንግሥታት ማኅበር" በመባል ይታወቅ ከነበረውና ከፈረሰው፥ በምትኩ ከተቋቋመው፡ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትም ጋር በመተባበር፡ ኹለቱም፡ ዓይነቶች የዓለም ዐቀፍ ተቋማት፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችንን ለማፈራረስ፡ ጥንቱኑ የተነሡበትን፡ ያንኑ፡ የጥፋት ዓላማቸውን፡ እውን ለማድረግ፡ ባለ፥ በሌላቸው፡ የጋራ ኃይላቶቻቸው፡ በፍጹም ውሕደትና በገሃድ፡ ይኸው፡ ሲጥሩ ይታያሉ።

በዚህ ጊዜ ግን፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን፡ በአሜሪካ ምሥራቃዊ ውቅያኖስ ዳርቻ በምትገኘው፡ በ'ኒው ዮርክ' ከተማ፡ በመስከረም ፩ ቀን፥ ፲፱፻፺፬ ዓመተ ምሕረት፡ (እንደፈረንጆቹ የቀን አቆጣጠር፡ በSeptember 11, 2001)፡ ለቅጣት በተሠነገለው እስላማዊ ሠይፍ፡ በደረሰው አሠቃቂ የዕልቂት አደጋ፡ እንዲከፈት ያደረገችው፡ መለኮታዊው የፍርድ ማኅደር፡ የችሎቱን ብያኔ፡ በተግባራዊነት ፈጽሞ፡ ሠይፉ ተመልሶ፡ ወደዐፎቱ እስኪገባ፥ ማኅደሩም፡ ተዘግቶ፡ ወደዘላለማዊው ቤተ መዛግብቱ እስኪመለስ ድረስ፡ እየራሳቸውን፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታቸው ያበቁት፡ ታማኞቹ ኪዳናውያን ወንዶችና ኪዳናውያት ሴቶች ልጆቻችን፡ በምድር ላይ፡ በእያሉበት ኾነው፡ ምን የሚያደርጉ ይመስሏችኋል?

እየራሳቸውን፡ ወደሰማይ አሻቅበው በማንሣት፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን፡ ለፍጥረተ-ዓለሙ፡ ገዝፋና ገሃድ ኾና የምትገለጥበትን፡ የኺደት ውጤት ይጠባበቃሉ።

ይህች፡ የ'ኒው ዮርክ' ከተማ፡ የእግዚአብሔር ቃል፡ እንዲህ በሚል፡ ሥዕላዊ ማብራሪያ፡ የሚገልጻት ናት፡-

"ወመጽአ አሓዱ፡ እምነ እልክቱ ሰብዓቱ መላእክት፡ እለ ይፀውሩ፡ ሰብዓተ ጽዋዓተ፤ ወይቤለኒ፡- "ነዓ! አርኢከ፡ ደይና፡ ለእንታክቲ ዘማ ዐባይ፡ እንተ ትነብር፡ ውስተ ማያት ብዙኀ። ...ወዛቲ ብእሲት፡ እንተ ርኢካ፡ ሀገር ዐባይ፡ ይእቲ፡ እንተ ትነግሥ፡ ላዕለ መንግሥታተ ምድር።"

"ሰባቱንም ጽዋዎች ከያዙ፡ ከሰባቱ መላእክት አንዱ መጥቶ፡ 'ና! በብዙም ውኃዎች ላይ የተቀመጠችውን፡ የታላቂቱን ጋለሞታ ፍርድ አሳይሃለሁ። ...ያየሃትም ሴት፡ በምድር ነገሥታት ላይ የምትነግሥ፡ ታላቂቱ ከተማ ናት።" (ራእ. ፲፯፥ ፩-፲፰፤ ፲፰፥፩-፳፬.)

ዛሬም፡ ጠብ ወዳጅ በኾነውና ማንነቱ፡ ቀደም ብሎ በተገለጸው፡ በመላው የዓለም ኅብረተሰብ፥ በተለይም፡ "ክርስቲያን ነኝ!" በሚለው ወገን ላይ፡ ከላይ የተወሳው፡ እስላማዊው ሠይፍ፡ የቅጣት በትሩን እያሳረፈና ይህንኑ ተልእኮውን እየቀጠለ ይገኛል። አዎን! በ**ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን** ላይ፡ ወረራንና ጥፋትን ለማድረስ በቃጣውና ፀረ-እግዚአብሔር በኾነው፡ በዚሁ፡ የዓለም ኅብረተሰብ ላይ፥ የእርሱ ደጋፊና ተባባሪ በኾነውም፡ ክርስቲያናዊው ወገን ኹሉ ላይ፡ ይኸው፡ የእስልምና ኃይል፡ የቅጣት ሰይፉን በመምዘዝ፡ የመቅጣት ግዳጁን፡ እነሆ! አኹንም እየፈጸመ መኾኑ፡ በግልጽ ይታያል።

ቀደም ብዬ የጠቀስሁት፡ ያ መለኮታዊ ፍርድ፡ የተፈጸመባት ዕለት፡ መስከረም ፩ ቀን፥ ፲፱፻፺፬ ዓመተ ምሕረት መኾኑ፥ ይህም፡ Ethiopia: The Classic Case በተሰኘውና በ**ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን** ኅላፊነት፡ ባገልጋዩ ልጃችን፡ በኤርምያስ ተዘጋጅቶ፡ ለኅትመትና ለሥርጭት በበቃው መጽሐፍ ውስጥ የተነገረው፡ የማስጠንቀቂያ መልእክት፡ እንዲህ፡ ቀደም ብሎ በተላለፈ፡ በሰባተኛው ዓመት መቃረብያ ላይ መከሠቱ፡ አመልካችነቱ፡ የባለራእዩ የዮሓንስ ቃል፡ ጊዜውን ጠብቆ መፈጸሙን የሚያረጋግጥ ኾኗል።

## መለኮታዊ ዓላማውን፡ ከግቡ እያደረሰ ያለው፡ የእስልምና ሠይፍ።

እንግዲህ፡ እስልምና፡ መለኮታዊ ለኾነው ዓላማ እንዴት እንደዋለ፥ ግቡን እስኪመታም፡ እንዴት፡ ወደፊት እንደሚቀጥል ማስተዋል ነው። ይኸውም፡-

፩ኛ. በአንድ ጎኑ፡ በአጠቃላይ፡ በመላው ዓለም የሚኖሩ፡ አረማውያን፥ ጣዖት አምላኪዎችና አሕዛብ፤ በተለይ ግን፡ እየራሳቸውን፡ እንደሃይማኖተኞች ሕዝቦች በመቍጠር፥ ከሰብአውያን ፍጡሮች መካከል፡ "እኛ፡ 'አይሁዳውያንና ክርስቲያኖች' ተብለን፡ የምንጠራ ነን!" እያሉ፡ በግብዝነት የሚመጻደቁት ዐገገተ-ደንዳኖች ኹሉ፡ በ**ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን** ላይ፡ በግትርነት ለሚያካኺዱት፡ የክህደትና የዓመፅ፥ የአምልኮ ምንዝርናና የሥልጣን ብልግና ኃጢአታቸው፡ ተገቢውን ተግሣፅና ቅጣት ለመስጠት ነው።

፪ኛ. በሌላ ጎኑ ደግሞ፡ ከዚህ የሚከተለው፡ የተቀደሰ ዓላማ እንዳለው፡ ማስተዋል ነው። ይኸውም፡ እኒሁ የክፋት ሠራዊት፡ የዓለማቱ ኹሉ ፈጣሪና ባለቤት፥ ጠባቂና መጋቢ በኾነችው፡ በ**ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን** ላይ ስለሠሩት በደል፡ በየበኩላቸው፡ እየራሳቸውን በመመርመር፡ ንስሓ የመግባት ምግባርን ይፈጽሙ ዘንድ፥ ከዚያ በመቀጠልም፡ እውነተኛዎቹን፡ የቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖቷንና ሕይወቷን፡ በእምነት ይቀበሉ ዘንድ፥ በመጨረሻም፡ በዚህ ረገድ፡ ኹሉም፡ የሚገባቸውን ግዳጅ፡ በተግባር ላይ በማዋል፡ የእርሷ ወደኾነው፡ ወደቀድሞውና ወደእውነተኛው፡ ተፈጥሮአዊና እግዚአብሔራዊ ሥርዓቷ እንዲመለሱ፥ ይህም፡ በመላዋ የምድር ገጽ እንዲሰፍን፡ በአጽንዖትና ባስቸኳይ ለማሳሰብ ነው። እናም፡-

፫ኛ. እግዚአብሔር፡ ለመላው የሰው ዘር፡ መልካም ህልውና እና ተድላ ሲል፡ *መሥርቶ፡* እንዲህ ያቋቋማትና ለዓለሙ ኹሉ ገሃድ ያደረጋት፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን፡** በተቀደሰው የምንነት አቋሟና የማንነት ህልውናዋ፡ ምንም ዓይነት ጥቃት ሳይደርስባት፡ ተከልላና ተጠብቃ፡ ለመኖር እንደምትችል፡ ይህችን፡ የእግዚአብሔር እውነት፡ አምነው ለመቀበል፥ በተግባርም ለመፈጸም፡ "እምቢ!" ላሉት ኹሉ፡ በአጽንዖት ለማስገንዘብ ነው።

ነገር ግን፡ እነዚሁ፡ ከላይ የተጠቀሱት፡ የኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን ተፃራሪዎች፡ ይህን የማስጠንቀቂያ ደወል ሰምተው፡ ተገቢውን ለመፈጸም፡ አኹንም፡ ፈቃደኛ ባይኾኑ፥ ማለትም፡ በዚኹ፡ በተጠመዱበት፡ የጥፋት ዓላማቸው፡ እንደጸኑ ኾነው፡ የተነሣሡበትን የደባ ተግባር፡ እስካኹን እየኾነ በሚታየው መልክና ይዘት፡ በእርሷ ላይ፡ በእምቢተኝነት፡ መቀጠላቸውን ባያቆሙ፡ መጨረሻቸው፡ ምን እንደሚኾን፡ አስቀድመው ሊያውቁትና ሊገነዘቡት ይገባቸዋል።

ይኸውም፡-

በጠንቀኛውና በመሠሪው፡ የክፋት ኃይል የሚካኼደው፡ የመላው የክርስቲያኑ ዓለም፡ ግብዝነት፤ ደግሞም፡ የፀረ-እግዚአብሔርና የጭካኔ አበጋዝ የኾነው፡ የዓለም ዐቀፉ ይሁድና፡ ልበ-ደንዳናነት፤ እንዲሁም፡ ሃይማኖተ-ቢሱና ሥርዓተ-አልበኛው ሰብአዊው ወገን፡ በምድር ኹሉ፡ እያስፋፋና እየጎዳበት ያለው፡ የአምልኮተ እግዚአብሔር ንቀት፡ እነዚህ ኹሉ፡ የክፋው ዲያብሎስ የተግባር ውጤቶች፡ የሚጠብቃቸው ጽዋ፡ ፈጽሞ በማያጠያይቅና በማያጠራጥር ኹኔታ፡ የመጨረሻው መደምሰስ መኾኑ ነው።

ይህንም እውነታ፡ የእግዚአብሔር ቃል፡ እንዲህ ሲል ያረጋግጠዋል፡-

"ወሶበ ኀልቀ ፲፻ ዓመት፡ ይትፈታሕ ሰይጣን፡ እምነ ሞቅሑ። ወይወፅእ፡ ያስሕቶሙ ለአሕዛብ፡ እለ ውስተ አርባዕቱ መአዝኒሃ ለምድር፤ ወያስተጋብአሙ፡ ለጎግ ወለማጎግ፡ ከመ ያስተቃትሎሙ፤ ወኍልቆሙሰ፡ ከመ ኆጻ ባሕር። ወዐርጉ፡ ውስተ ስፍሓ ለምድር፤ ወዐገትዋ ለትእይንቶሙ፡ ለቅዱሳን፤ ወለሀገር ቅድስት [ኢትዮጵያ፡ ዘመንግሥተ እግዚአብሔር]። ወእምዝ፡ ወረደት እሳት፡ እምሰማይ፥ እምኀበ እግዚአብሔር፤ ወበልዐቶሙ። ወለዘክቱኒ ሰይጣን፡ ዘያስሕቶሙ፡ ወደይዎ ውስተ ዐዘቅተ እሳት፥ ወተይ፡ ኀበ ሀሎ፡ ዝክቱ አርዌ፤ ወሓሳዌ ነቢይ፡ ከመ ይደየኑ፡ መዐልተ፥ ወሌሊተ፤ እስከ ለዓለመ ዓለም።"

"ሺሁም ዓመት ሲፈጸም ሰይጣን ከእሥራቱ ይፈታል፤ በአራቱም በምድር ማዕዘን ያሉትን አሕዛብ፥ ጎግንና ማጎግን እንዲያስታቸው፥ ለሰልፍም እንዲያስከትታቸው ይወጣል፤ ቍጥራቸውም እንደ ባሕር አሸዋ የሚያህል ነው። ወደምድርም ስፋት ወጡ፤ የቅዱሳንንም ሠፈርና የተወደደችውን ከተማ [ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥትን] ከበቡ። እሳትም ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ወርዳ በላቻቸው። ያሳታቸውም ዲያብሎስ፡ አውሬውና ሐሰተኛው ነቢይ ወዳሉበት፡ ወደእሳቱና ወደዲኑ ባሕር ተጣለ። ለዘላለምም እስከ ዘላለም፡ ቀንና ሌሊት ይሠቃያሉ።" (ራእ. ፳፥ ፯-፲።)

ከዚህ በኋላ፡ እስላማዊው ሃይማኖት፡ መለኮታዊ ተልእኮውን፡ እንዲህ፡ ፈጽሞ ሲያበቃ፡ በመሣሪያነቱ፡ ጠቃሚ፥ በአገልግሎቱም፡ ውጤታማ ኾኖ የተገኘውን፡ የተመዘዘ ኃያል ሠይፉን፡ ወደሰገባው ይመልሳል። ተአማኒነቱንና ተገዢነቱንም፡ በመጨረሻ፡ በራሱ የፍላጎትና የስምምነት ውሳኔ፡ ራሱን፡ ለመለኮታዊው ፈቃድና ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን፡ የቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖት በማብቃት፡ እንግዴህ ወዲህ ወደማይታሰብበት፡ ወደ"ኀበ አልቦነቱ"፤ ማለትም፡ ወደ"አለመኖርነቱ" ይጎዳኛል። በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን መቅደስም ሥር፡ በሰላምና ለዘላለም ይሠወራል።

የትንቢቱና የተስፋው፥ የሕልሙና የራእዩ ኹሉ ፍጻሜ በኾንነው፡ በእኔ፡ በእግዚአብሔር እም፡ ድንግል-ማርያምና በልጇ በወዳጇ፡ በእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ ትስብእትና ቤዛነት፡ የዛሬ ኹለት ሺህ ስምንት ዓመት፡ ለፍጥረታተ-ዓለማቱ የተከሠተችው፥ ይህችው፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፦

- በዚህ ምንነቷና ማንነቷ፡ በሥጋዊውና በነፍሳዊው፥ በመንፈሳዊውና በኹለንተናዊው ህልውናዋ፡ ጥንቱኑ፡ በመነሻው፡ በመለኮታዊው ኀሊና ታስባና በዕውቀቱ ተዘጋጅታ፤ በጥበቡም ተመሥርታ፡ እስከዛሬ በጸናችበትና ወደፊትም፡ ለዘለዓለም በምትቀጥልበት አቋሟ፡ በማይታየው፡ ረቂቁ ዓለም በኩል፡ የሚጠብቋትና የሚከላከሉላት፡ ቅዱሳኑ የሰማይ ሠራዊተ መላእክት ናቸው።

- በሚታየው፡ በግዙፉ ዓለም በኩል ደግሞ፡ የሰዎች፡ የዓለም መንግሥታት እንደሚያደርጉት፡ በጦር መሣሪያ ሳይኾን፡ እርሷ፡ ለሕዝቧ፡ ሰላማዊ አገልግሎትን፡ ያለአንዳች የኃይል መሣሪያ፡ በፍጹም ፍቅረኛነትና አንድነት፥ ግልጽነትና እውነተኛነት ብቻ ከሚያበረክቱት፡ የደኅንነት ጥበቃ፥ የሥርዓት አስከባሪና የረድኤት ሰጪ ካህናት ዘበኞቿ ጋር፡ በተጨማሪ፡ ተመሳሳዩን፡ የልማትና የዕድገት ሰላማዊ አገልግሎታቸውን፡ ያለአንዳች የኃይል መሣሪያ፡ በፍቅር ብቻ፡ ለሕዝቧና ለፍጥረቷ፡ ሥጋዊ፥ ነፍሳዊና መንፈሳዊ አገልግሎቶችን የሚያበረክቱላት፡ እነዚሁ፡ የከተማና ብሔራዊ፤ የሕግና የክብር፤ የምድርና የአየር፥ የባሕርና የጠረፍ፡ ጠቅላላ፡ የአገር ጥበቃ እና መከላከል፥ እንክብካቤ እና ልማት ኪዳናውያንና ኪዳናውያት ሠራዊቶቿ ናቸው።

ከዚህ የተነሣ፡ ክፉዎቹ ሰዎች፡ አቋቁመው እንደሚያካኺዷቸው፡ የዓለም መንግሥታት ጦር ኃይሎች፡ ለዚህ ዓላማ ማስፈጸሚያና ለተግባሩ ማካኼጃ፡ ያስፈልጓት የነበሩትን፡ ልዩ ልዩ የጦር መሣሪያ ምርትን በማሳደግ ረገድ፡ ይደርስ የነበረውን፡ የጥበብ ሙስናን፥ የሰው እልቂትንና፤ የገንዘብ ብክነትን ለማስወገድ ችላለች። ለእነዚሁ ሰዎች፡ የዓለም መንግሥታት፡ የጦር ኃይሎች ግዳጅ ማካኼጃና ማስፈጸሚያ፡ ሊመደብ የሚያስፈልገው ዕውቀቱና ጥበቡ፥ ሰውና ጉልበቱ፥ ገንዘቡና ንብረቱም፡ ለእርሷ፡ አላስፈለጓትም፤ አያስፈልጓትምም።

ከዚያ ይልቅ፡ *ያን ኹሉ ዕውቀትና ጥበብ፥ ሰውና ጕልበቱንም፥ ገንዘቡንና ንብረቱን ጭምር፡ ይህችው፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን፡- በሦስቱ የአገልግሎት ዘርፎቿ፡ እነርሱም፡ በቤተ-ሕዝቧ፥ በቤተ-ምልክናዋና በቤተ-ክህነቷ አማካይነት፡ ኹሉንም፡ ነፍሳዊዉን፥ ሥጋዊዉንና መንፈሳዊዉን፡ ሙሉ ግልጋሎቷን፡ ለሕዝቧ፡ ሥጋዊና ነፍሳዊ፥ መንፈሳዊና ኹለንተናዊ ሕይወት ማዳበሪያ፤ ለሥነ ፍጥረቷም እንክብካቤ ብቻ እንዲውል አድርጋለች፤ ታደርጋለችም።*

## የዐዋጅ ቃሌ፡ ማጠቃለያ ስለኾነው የመፍትሔ መልእክቴ።

እንግዴህ፡ በኹለንተናዊው ማንነታችሁና ምንነታችሁ ላይ ባለኝ፡ እግዚአብሔራዊና ትስብእታዊ እናትነቴ፡ እናንተን እያንዳንዳችሁን፡ በየግል፥ በኅብረትም፡ በጋራ በሚመለከት፡ እስካኹን ባሰማኋችሁ ምዕዳኔ ውስጥ፡ ለገለጽኋቸው ጽኑ ችግሮቻችሁ፡ ፍጹም መፍትሔ የሚኾኑትን ፍሬ-ነገሮች፡ ለዚህ የዐዋጅ ቃሌ ማጠቃለያና መደምደሚያ አድርጌ፡ ይኸው፡ ባጭር አቅርቤላችኋለሁና ስሟቸው!

የምትሰሟቸውም፡ እጅግ ብዙዎቹ መሰሎቻችሁ ፍጡሮቻችን እንደሚያደርጉት፡ እየራሳችሁን፡ ለሓሰተኛው የሰዎች እውነት ሳይኾን፡ ለአማናዊቷ የእግዚአብሔር እውነት፡ በሰማዕትነት በመሠዋት፥ በጨከነ ልቦናና በቆራጥ መንፈስም ኾናችሁ፡ ይህንኑ እየራሳችሁን፡ ለእውነተኛው የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ለማብቃት፡ ሊኾን ይገባል። አዎን! **የዚህ የዐዋጅ ቃሌ፡ ዓላማውና ግቡ፡ እናንተ፡ እያንዳንዳችሁ፡ በየግል፥ በኅብረትም፡ በጋራ፡ ለእየራሳችሁ ዘለዓለማዊ መልካም ሕይወት ስትሉ፡ ሰብኣዊ ፈቃዳችሁን፡ ከእኛ መለኮታዊ ፈቃድ ጋር ታስማሙ ዘንድ፡ ምርጫችሁ እንዲኾን መምከርና መርዳት ነውና።**

እስካኹን እንደገለጽሁላችሁ፡ በአንድ በኩል፡ በመጠናቸው፡ የተወሰኑ ይኹኑ እንጂ፡ በኖኅ ዘመን የደረሰውን የሚመስሉ፡ የተለያዩ የተፈጥሮ መቅሠፍቶች፡ የጥፋት ኃይላቸውን መፈጸማቸውን እንደቀጠሉበት ይታያል፤ በሌላው በኩል ደግሞ፡ ሰው-ሠራሽ በኾኑ ጠንቆች ምክንያት፡ ከሚፈጠሩ አደጋዎችና አኹን እየተካኼደ ካለው፥ በተለይ፡ "ክርስቲያን ነኝ" የሚለው ዓለምና የእርሱ ተባባሪ የኾነው ወገን ኹሉ፡ ተሠንግሎ እየቀላ ካለው እስላማዊ ሠይፍ ለመዳን፡ ከሚያካኺደው፡ ከሦስተኛው የዓለም ጦርነት የተነሣ፡ የእርስ በርሱ ዕልቂት፡ ይኸው፡ እየተባባሰና እየተጠናከረ በመኼድ ላይ ይገኛል።

ታዲያ! ልጆቼ! ይህ ኹሉ የሚኾነው፡ እንዲያው ዝም ብሎ፡ በዘልማድ፥ ወይም፡ በእየራሱ ዐውቆ፥ ወይም፡ በድንገት፥ ወይም፡ በአጋጣሚ ይመስላችኋል? አይምሰላችሁ! አይደለም። ልጄ ወዳጄ ኢየሱስ መሲሕ፡ "አኮኑ ክልኤቲ አዕዋፍ ይሠየጣ፡ በ፩ኤ ጸሪቀ-አሶርዮን፤ ወአሓቲ እምኔሆን፡ ኢትወድቅ ውስተ ምድር፡ ዘእንበለ ያእምር አቡክሙ ሰማያዊ። ወለክሙሰ፡ ሥዕርተ ርእስክሙኒ፡ ኵሉ፡ ኍሉቅ ውእቱ።"

**"ኹለት ድንቢጦች፡ በ፩ ጸሪቅ፡ የሚሸጡ አይደለምን? ከእነርሱ፡ አንዲቱ፡ ያለሰማዩ አባታችሁ ፈቃድ፡ በምድር ላይ አትወድቅም፤ አትሸጥምም። የእናንተማ፡ የራሳችሁ ጠጉር ኹሉ እንኳ ሳይቀር፡ ተቆጥሮአል።" እንዳላችሁ፡ እንኳንስ፡ እንደእኛ አድርገንና የእኛ የኾነውን ኹሉ ሰጥተን በፈጠርናችሁ፡ በእናንተ ይቅርና፡ ለእናንተ አገልግሎትና ደስታ፡ በደመ-ነፍስ ብቻ፡ ባስገኘናቸው ፍጡራን ላይ እንኳ፡ እኛ ሳናውቀው፥ ያለእኛም ፈቃድ፡ አንዳችም፡ የሚኾን፥ የሚደረግም ነገር እንደሌለ፡ በእርግጥ ልታውቁት ይገባችኋል። (ማቴ፣ ፲፣ ፳፱-፴፩።)**

ስለዚህ፡ በሥነ ፍጥረት ቊጣዎችና በሰው-ሠራሹ ጥፋቶች ረገድ፡ በእውን እየኾነና በግዘፍ እየደረሰ ስላለው ነገር ኹሉ፡ በግልጥ ልንገራችሁ! የምነግራችሁም፡ ልጄ ወዳጄ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ አምነው ለተከተሉት ደቀ መዛሙርቱና ሓዋርያቱ፡ በአኹኑ ጊዜ፡ በእውን እየኾነና በግዘፍ እየደረሰ ስላለው፡ ስለዚህ ኹሉ የተፈጥሮ መቅሠፍትና ሰው-ሠራሽ ዕልቂት፡ አስቀድሞ የሰጣቸውን፡ እንዲህ የሚለውን፡ መለኮታዊ ማስጠንቀቂያ፡ መሪና ምስክር አድርጌ ነውና፡ እናንተም፡ ይህንኑ ቃሌን፡ በአንክሮና በተዘክሮ ሰምታችሁ፡ ልትፈጽሙት የሚያስፈልጋችሁ መኾኑን፡ አበክሬ አሳስባችኋለሁ።

**"ዑቁ! ኢያስሕቱክሙ! ...ወዝንቱ ኵሉ፡ ቀዳሚሁ ለሕማም። ...ዑቁ! ኢትደንግፁ! እስመ ግብር ይከውን ዝንቱ፤ ወባሕቱ፡ አኮ በጊዜሃ ዘየኀልቅ። ...ወአሜሃ፡ የዐልዉ ብዙኃን ሃይማኖቶሙ፤ ወይጸልኡ በበይናቲሆሙ፤ ወይትቃተሉ። ውይትነሥኡ፡ብዙኃን ሓሳውያነ ነቢያት፤ ወለብዙኃን ያስሕትዎሙ። ወእምብዝኀ ዓመፃ፥ ወእከይ፡ ትሴኵስ ፍቅር እምብዙኃን፤ ወብዙኃን የዓልዉ ሃይማኖቶሙ፥ ወፍቅሮሙ። ...እስመ ይከውን ይእተ አሚረ፡ ዐቢይ ሕማም ወምንዳቤ፣ ዘኢኮነ ከማሁ፣ እምአመ ተፈጥረ ዓለም፡ እስከዮም፤ ወኢይከውንሂ። ወሶበ አኮ ዘአኅጸሮን፡ ለእማንቱ መዋዕል፡ እምኢድኅነ መኑሂ፡ ኵሉ ዘሥጋ፤ ወባሕቱ፡ በእንተ ኅሩያን፡ የኀጽራ፡ እማንቱ መዋዕል።...ወዘሰ፡ አዝለፈ ትዕግሥቶ፡ ውእቱ ይድኅን። ወይሰበክ ዝ ወንጌለ መንግሥተ እግዚአብሔር፡ ውስተ ኵሉ ዓለም፡ ከመ ይኩን ስምዐ፡ ላዕለ ኵሉ አሕዛብ። ወይእተ አሚረ፡ ይበጽሕ ኅልቀት። ...ወበእንተሰ ይእቲ ዕለት፥ ወኪያሃ ሰዓት፡ አልቦ ዘየአምራ፣ ኢመላእክተ ሰማይ፥ ወኢወልድ፣ ዘእንበለ አብ ባሕቲቱ። ወበከመ ኮነ፡ በመዋዕለ ኖኅ፣ ከማሁ ይከውን ምጽአቱ፡ ለወልደ ዕጓለ እመሕያው። ...ከማሁ አንትሙሂ፡ ድልዋኒክሙ ሀልዉ! እስመ በጊዜ ኢተሓዘብክሙ፡ ይመጽእ ወልደ ዕጓለ እመሕያው።**

**"ማንም እንዳያስታችሁ፡ ተጠንቀቁ! ...እነዚህ ኹሉ፡ የምጥ ጣር መጀመሪያ ናቸው። ...ይህም ኹሉ ሊኾን፡ ግድ ነውና፡ ተጠበቁ! አትደንግጡ! ዳሩ ግን፡ መጨረሻው፡ ገና ነው። ...በዚያን ጊዜ፡ ብዙዎች፡ ሃይማኖታቸውን ይክዳሉ፤ እርስ በርሳቸውም፡ ይጣላሉ፤ ይገዳደሉማል። ብዙ ሓሰተኞች ነቢያትም ይነሣሉ፤ ብዙዎችንም፡ ያስታሉ።**

ከዓመፃና ከክፋት ብዛት የተነሣ፡ የብዙ ሰዎች ፍቅር ትቀዘቅዛለች፤ ብዙዎችም፡ ሃይማኖታቸውን ይክዳሉ፤ ፍቅራቸውንም ይተዋሉ።...በዚያን ጊዜ፡ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ፡ እስከዛሬ ድረስ ያልኾነ፥ እንግዲህ ወዲህም፡ ከቶ የማይኾን፡ ታላቅ መከራና ችግር ይኾናልና። እነዚያ ቀኖችስ ባያጥሩ፡ ሥጋ የለበሰ ኹሉ፡ ባልዳነም ነበር፤ ነገር ግን፡ እነዚያ ቀኖች፡ ስለተመረጡት የበቁ ሰዎች፡ ያጥራሉ። ...እስከመጨረሻ የሚጸና ግን፡ እርሱ ይድናል። ለአሕዛብም ኹሉ፡ ምስክር እንዲኾን፡ ይህ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ምሥራች፡ በዓለም ኹሉ ይሰበካል። በዚያን ጊዜ፡ መጨረሻው ይመጣል።" ...ስለዚያች ቀንና ስለዚያች ሰዓት ግን፡ ከአባት ብቻ በቀር፡ የሰማይ መላእክትም ቢኾኑ፥ ልጅም ቢኾን፡ ማንም የሚያውቅ የለም። በኖኅ ዘመን እንደኾነው ኹሉ፡ የማርያም ልጅ የኢየሱስ መሲሕም፡ ዳግም አመጣጥ፡ እንዲሁ ይኾናል። ...ስለዚህ፡ እናንተ ደግሞ፡ ተዘጋጅታችሁ ኑሩ! የማርያም ልጅ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ድንገት፡ ባላሰባችኋት ጊዜ ይመጣልና።" (ማቴ. ምዕ. ፳፬።)

ልጆቼ! አትመለከቱትም? "ለአሕዛብም ኹሉ፡ ምስክር እንዲኾን፡ ይህ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ምሥራች፡ በዓለም ኹሉ ይሰበካል። በዚያን ጊዜ፡ መጨረሻው ይመጣል።" ያለው፡ የማይታበለውና የማይቀረው፡ የልጄ የወዳጄ፡ መለኮታዊ የምልክት ቃል፡ ይኸው፡ በዚህ፡ በእኔ የዐዋጅ ቃሌ ሲፈጸም፡ በዓይናችሁ እያያችሁት፥ በጆሮአችሁም እየሰማችሁት አይደለምን? አዎን ነው እንጂ።

ደግሞም፡ ስለእኛዪቱ፡ የእግዚአብሔር መንግሥትና ስለምሥራቿ፥ የዓለም ሕዝቦች ኹሉ፡ በመጨረሻው የፍርድ ቀን፡"አልሰማንም!" እንዳይሉ፡ ምስክር ይኾንባቸው ዘንድ፡ ይህን መለኮታዊ መልእክት፡ ቀድሞም ኾነ ዛሬ፡ በመላው ዓለም ላይ፡ ለመላው የዓለም አሕዛብ እንዲህ፡ በዐዋጅ መልክ ሳይቀር እያደረሰች፥ እየሰበከችም ያለችው፡ ይህችው፡ የእኛዪቷ፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ብቻ አይደለችምን? ሌላ፡ ማን አለ? የለም፤ እርሷ ብቻ ነች እንጂ።

እውነታው፡ ይህ ከኾነ፡ ታዲያ! "በዚያን ጊዜ፡ መጨረሻው ይመጣል።" ያለው ምልክታዊ ቃሉ፡ "ተፈጸመ!" ማለት አይደለምን? አዎን! በእርግጥ ተፈጽሟል። ስለዚህ፡ ይህ፡ አኹን፡ እናንተ፡ በሕይወተ ሥጋ እየኖራችሁበት ያለው ጊዜ፡ የመጨረሻው፥ እኔና ልጄ ወዳጄ የመጣንበትና የተገለጥንበት ሰዓት መኾኑን እንድታውቁት ይኹን!

እንግዲህ፡ እናንተ፡ በእየበኩላችሁ፡ እየራሳችሁን፡ ለቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ዜግነታችሁ ዐብቁ እንጂ፡ ስለሌላው ኹሉ አትፍሩ! አትጨነቁ! ብቻ፡ አኹንም፡ ልጄ ወዳጄ ኢየሱስ መሲሕ፡ "ወናሁ እመጽእ ፍጡነ፤ ወዕሤትየኒ ምስሌየ ውእቱ፡ ከመ እፍድዮ፡ ለለአሓዱ፤ ወእኩንኖ፡ በከመ ምግባሩ።""

"እነሆ፡ ፈጥኜ እመጣለሁ፤ ለእያንዳንዱም፡ እንደየሥራው ዓይነትና መጠን እየፈረድሁ፡ የሚገባውን እከፍለው ዘንድ፡ ዋጋዬ፡ ከእኔ ጋር አለ።" ብሎ የተናገረውን፡ መለኮታዊ ቃሉን፡ አትርሱ! አስታውሱ! (ራእ. ፳፪፥ ፲፪።)

ልጆቼ! አታዩምን? አዎን! ታያላችሁ። ልጇ ወዳጇ፡ በዚህ የተስፋ ቃሉ፡ እኛ፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡ ለሥነ-ፍጥረት፡ የሰጠናትን፡ የማይናወጽ ፍጹም ሥርዓቷን ተከትላ፡ በእርሷ በኩል፡ በምታካኺደው ተልእኮዋ፡ እየፈጸመች ያለውን ግዳጇን የምትመለከቱት አይደላችሁምን? አዎን! በእውንና በእርግጥ ትመለከቱታላችሁ። ታዲያ! በእያንዳንዱ ሰብአዊ ፍጡራችን ላይ፥ በእናንተም ላይ ጭምር፡ ፈጥኖ እየመጣላችሁ፥ እየመጣባችሁም ያለው፡ ከቶ፡ ምንድር ነው? ሥነ-ፍጥረት፡ ለክፉው፡ ስለጥፋት ድርጊቱ፡ የቅጣት ፍዳውን፥ ለደጉም፡ ስለበጎ ምግባሩ፡ የውለታ ስጦታውን፡ ለኹሉም፡ እንደየሥራው፡ ተገቢ ዋጋውን፡ ይኸው፡ እየከፈለችው አይደለምን? አዎን! እየከፈለችው ነው።

ሥነ ፍጥረት፡ ከእኛ በተሰጣት፡ ቋሚ ሥርዓቷ መሠረት፡ የትዕግሥቷ ጽዋ ሲሞላ፡ በተለይ፡ በአጥፊዎች ክፉዎች ሰዎችና በኃጢአተኛው ዓለም፥ በእያንዳንዱ ፍጡርም ላይ ሳይቀር፡ በነፍስና በሥጋ፥ በመንፈስና በኹለንተና ሊደርስ የሚገባውን፡ የቅጣት ዋጋ ለመክፈል፡ እንዲህ የምታደርግ ከኾነ፡ ታዲያ፡ እናንተ፡ እየኾነ ያለውን ይህን ኹሉ ስትመለከቱ፡ ምን እየጠበቃችሁ ነው? ይህ ኹሉ፡ ለእናንተ፡ እንደማስጠንቀቂያ የቀረበላችሁ እንደኾነ ቈጥራችሁ፡ እየራሳችሁን፡ በነፍስ ወከፍ፡ ልታዘጋጁ ይገባችኋል። እንዲህ፡ እየራሳችሁን ካላዘጋጃችሁ፡ ዕጣ ፈንታችሁ፥ ጽዋ ተርታችሁ በደረሰ ጊዜማ፡ ምን ልታደርጉ ይቻላችኋል? ከመጥፋት በቀር፡ ምንም ልታደርጉ አይቻላችሁም።

እንግዴህ፡ እንዲህ፡ እያስጨነቋችሁ ካሉት ጽኑ መከራዎችና ችግሮቻችሁ ኹሉ፡ እየራሳችሁን በሚያስተማምን ኹኔታ፡ ፍጹም ነጻ ልታወጡ ይቻላችሁ ዘንድ፡ ቀደም ብዬ በሰጠኋችሁ መመሪያዬ መሠረት፡ "መፍትሔ ይኾናችኋል!" ብዬ፡ ባጭር ያቀረብሁላችሁ ፍሬ-ነገሮች፡ እኒኼውላችሁ!

አንደኛ፡- እያንዳንዳችሁ፡ በልጇ በወዳጇ፡ በኢየሱስ መሲሕ ቀኝ ተሰቅሎ እንደነበረው ወንበዴ፡ በእየራሳችሁ፡ ቅጽበታዊው የንስሓ ውሳኔያችሁ፡ እዚያው፡ በያላችሁበት፡ በእኛዪቱ፡ የእግዚአብሔር እውነትና በመንፈስ ቅዱስ አምልኳችሁ፡ እየራሳችሁን፡ አኹኑኑ፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት በማብቃት፡ የኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን ዜጎች ኹኑ! በዚችው አፍታ፡ ያለአንዳች ውጣ-ውረድና የክፍያ ዋጋ፡ በነጻ ምርጫችሁ፡ ወዲያው፡ የእግዚአብሔር ልጆችና ነጋሢዎች፥ ካህናት [አገልጋዮች] እና የመንግሥታችን ባለቤቶች መኾናችሁን፡ በፍጹም ታውቃላችሁ፤ ታረጋግጣላችሁም። ከዚህ አስቀድሜ የነገርኋችሁን አጭር ሥርዓት፡ በጊዜውና ለጊዜው ለመፈጸም፡ ካልቻላችሁና ካልተመቻችሁ ማለት ነው። (ሉቃ. ፲፰ እና ፳፫፥ ፴፱-፵፫።)

በዚሁ ጊዜና ከዚህ በኋላ፡ የምድር አገሮችን አጠቃልሎ የያዘው ዓለሙ ኹሉ አገራችሁ ይኾናል። ስለዚህ፥ በወደዳችሁትና በፈለጋችሁት አገር እየተዘዋወራችሁ መኖር ትችላላችሁ።

ይህም የሚኾነው፡ ከጌታዬ ከእግዚአብሔር አብ፥ ከልጇ ወዳጇ ኢየሱስ መሲሕና ከሕይወቴ መንፈስ ቅዱስ ጋር፡ የሰማይና የምድር፡ [የማይታየውና የሚታየው፥ የረቂቁና የግዙፉ፥ የመንፈሳዊዉና የሥጋዊው ፍጥረታተ-ዓለማት] ፈጣሪና ባለቤት፥ መጋቢና ጠባቂ፥ እናትና ንግሥት በኾንሁት፡ በእኔ፡ በድንግል ማርያም ኢትዮጵያነት በማመናችሁ ምክንያት ነው።

በዚሁ ጊዜና ከዚህ በኋላ፡ እውን የሚኾንላችሁ፡ ይህ ትንግርት ብቻ አይደለም፤ የዓለሙን የሰዎች መንግሥታት ኹሉ፡ በሥሯ አድርጋና አጠቃልላ የምትቆጣጠረው፡ **የኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** ባለቤት ስለኾናችሁ፡ ከኪዳናዊ ኢትዮጵያዊነታችሁና ከኪዳናዊት ኢትዮጵያዊትነታችሁ እምነት ጋር የሚስማማውን፡ የሰብአዊዉን መንግሥት ሕግ ኹሉ፡ በትክክል እየፈጸማችሁ፡ ያለአንዳች ተፅዕኖ፡ በሥጋዊውና ነፍሳዊው፥ መንፈሳዊውና ኹለንተናዊው ፍጹም ነጻነት የምትኖሩ ከመኾናችሁ በቀር፥ ያ ሰብአዊው መንግሥትም፡ እናንተን የሚያገለግል ከመኾኑ በቀር፡ ማንኛውም የሰዎች መንግሥት፡ በእናንተ ላይ፡ ምንም ዓይነት ሥልጣን አይኖረውም።

ኹለተኛ፡- በምድር ላይ፡ እንዲህ በምትኖሩበት ጊዜ፡ እየራሳችሁን፡ ከማናቸውም አገዛዝ፡ ፍጹም ነጻ ማውጣትና ከክፉው ኹሉ ማዳን ብቻ ሳይኾን፡ እስካኹን ዜጎቻቸው ኾናችሁ ስትገዙላችሁ የኖራችሁባቸውን፡ ሰብአውያን መንግሥቶቻችሁን ጭምር፡ ከእነዚህ፡ ከማይቀሩት የተፈጥሮ መቅሠፍቶችና ሰው-ሠራሽ የቍጣ ዕልቂቶች ለማትረፍ የምትችሉበት መለኮታዊው ሥልጣንና ኃይል፡ ከእኛ ይሰጣችኋል። በዚያን ጊዜና ከዚያ በኋላ የሚኾነውን ሌላ ትንግርት ልግለጥላችሁ፡-

እናንተ፡ እያንዳንዳችሁ፡ ዐብራችሁት ከምትኖሩት ሰብአዊ መንግሥት ጋር፡ በተለያየ መልክና ይዘት፡ በእውነተኛነትና በትክክለኛነት፡ በሚኖራችሁ አግባብነት ምክንያት፡ አመቺ ጊዜንና ኹኔታን የሚያበረክትላችሁን ዕድልን ስታገኙ፡ በዚያ በመጠቀም፡ እንዲያ፡ በመንፈስ ቅዱስ በተላበሳችሁት፡ መለኮታዊው ሥልጣንና ኃይል፡ ለዚያ ሰብአዊ መንግሥት ተጠሪ፥ ወይም ተጠሪዎች፡ የእኛን፡ **የኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ የምሥራች መልእክታችንን ታደርሳላችሁ።**

እናንተ፡ እንዲህ፡ የበኩላችሁ ድርሻ የኾነውን፡ ይህን ተልእኮ በምትፈጽሙበት ጊዜ፡ ያ ሰብአዊ መንግሥት ደግሞ፡ የራሱ ድርሻ የኾነውን ግዳጅ፡ ለመፈጸም ዕድል ይኖረዋል። ያም ዕድል፡ እኔን፡ **የኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥትን**፡ በእምነት ለመቀበል፡ ፍጹም ፈቃደኛ ኾኖ መገኘት ነው።

ይህ ፈቃደኛነት፡ እውን ኾኖ፡ በተግባር በሚፈጸምባት አፍታ፡ ለሦስተኛው የዓለም የዕልቂት ጦርነት ምክንያት የኾነው፡ ሃይማኖታዊው ጠንቅ ይወገድና፡ ክርስቲያኑን ዓለም ሊቀጣ የተመዘዘውና በሰዎች ደም የታለለው፡ እስላማዊው ሠይፍ፡ ወዲያው፡ ወደአፎቱ ይመለሳል።

በዚህ ጊዜ፡ በተዋጊዎቹ ብቻ ሳይኾን፡ በመላው የዓለም ሕዝቦቻችን ዘንድና መካከል፡ ፍጹም ጸጥታ፥ ፍጹም ዕርቅ፥ ፍጹም ሰላም ይኾናል! ተያይዞም፥ ፍጹም ፍቅርና ፍጹም ደስታ፥ ፍጹም ዕረፍትና ፍጹም ብልጽግና ይሰፍናል።

በኖኅ ዘመን ደርሶ ከነበረው የጥፋት ውኃ ተርፎ፡ ለዚህ ለዛሬው ዘመን የበቃው፡ ከመላው የሰው ዘር መካከል፡ በተለይ የክፋቱ ወገን የኾነው ዓለም፡ ከዚያን የጥፋት ውኃ ከባሰው፥ እየተቃረበ ካለው፡ የተፈጥሮና ሰው-ሠራሽ ከኾነው፡ ታላቅ መቅሠፍታዊ ቍጣና ጥፋት፡ ራሱን ለማዳን፡ እኔ፡ ራሴ፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ በዚህ የዐዋጅ ቃሌ ካሰማኋችሁ፡ ከዚህ ምዕዳኔ በቀር፡ እንግዴህ ወዲህ የሚመጣላችሁ፥ የምትጠብቁትም ሌላ <u>የመፍትሔ መልእክት</u> እንደሌለ፡ እንድታውቁት ይኹን! ይህን ተረድታችሁ፡ ለእየራሳችሁ ደኅንነትና መልካም የዘለቄታ ሕይወት ስትሉ፡ አምናችሁበት ፈጽሙት!

## ይህን የዐዋጅ ቃሌን ለመፈጸም፡ የሚረዱ ሰነዶች።

ከዚህ ምዕዳናዊ የዐዋጅ መልእክቴ ጋር፡ በዚችው፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ኃላፊነት፡ ለኅትመት የበቁትን መጻሕፍት፥ እንዲሁም፡ በኀዋ ሰሌዳዋና በፌስቡክ መድረኳ ላይ ሠፍረው የሚገኙትን፡ የቅዱሱ ኪዳን መልእክቶችና ሰነዶች፥ ደግሞም፡ በቀላሉ ልትገነዘቧቸው ለሚቻሉና ማስተዋልን ለሚጠይቁ፡ ከባድና በርካታ ጥያቄዎች፡ የተሰጡትን መልሶች፡ ከእናንተ መካከል፡ ያልተመለከታችሁና ያላነበባችሁ ብትኖሩ፡ እንድትመለከቷቸውና እንድታነብቧቸው፡ በድጋሚ አደራና በአጽንዖት ቃል አሳስባችኋለሁ።

ምናልባት፡ ይህን ማሳሰቢያዬን፡ ተግባራዊ ማድረግ፡ የሚያዳግታችሁ ብትኖሩ፡ ለእየራሳችሁ ጊዜያዊ እና ዘለዓለማዊ፥ ምድራዊና ዓለማዊ፥ ሥጋዊና ነፍሳዊ፥ መንፈሳዊና ኹለንተናዊ፡ የጤናና የሰላም፥ የደስታና የብልጽግና መልካም ሕይወት ስትሉ፡ አኹን፡ እኔው ራሴ፡ ከዚህ አስከትዬ፡ በዚህ የዐዋጅ ቃሌ ከማሰማችሁ ጋር፡ ቢያንስ ቢያንስ፡ በኀዋ ሰሌዳችን ዋና ገጽ ላይ፡ “ሃይማኖት” በሚለው ክፍል ውስጥ፥ አራቱን የጸሎት ክታቦች፣ ከነቃል ኪዳን ምስክርነቱ፡ አዋሕዶ አካትቶ የያዘውን መድበል ሰነድ፡ መስማቱና መመልከቱ፡ እጅግ ይጠቅማችኋል። እነዚህም፡-

፩ኛ. "የኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያውያት የሃይማኖት ጸሎት"

፪ኛ. "የኢትዮጵያውያትና የኢትዮጵያውያን፡ የቃል ኪዳን ጸሎት"

፫ኛ. "ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት፡ የምስጋና ጸሎት"

፬ኛ. "ኢትዮጵያውያትና ኢትዮጵያውያን፡ ለድንግል ማርያም የሚያቀርቡት፡ የሰላምታ ጸሎት" በሚል አርእስት፡ የታወቁ ሲኾኑ፣

ከእነዚህ በተጨማሪ፡ እስካኹን፡ ከአንድ እስከዐሥር ቊጥር፡ ለይፋ ምንባብ፡ በተከታታይ የወጡትንና ወደፊትም፡ የሚወጡትን ቃለ ዐዋዲዎች (የዐዋጅ ቃሎች) ያጠቃለለው መዝገብ ይገኛል።

ቀደም ብዬ የዘረዘርኋቸው፡ የእግዚአብሔራዊው ዕውቀት ጽሑፎች፡ ለእያንዳንዱ ሰብኣዊ ፍጡራችን ግለሰብ፡ ስለኢትዮጵያ፥ ስለኢትዮጵያ ልጆችና ስለኢትዮጵዊነት፡ ወሳኝ የኾኑ ቁምነገሮችን በሚመለከት፡ የበለጠ ግንዛቤን ለማስጨበጥ የሚያስችሉ ከመኾናቸው በላይ፡ በዚሁ ዙሪያ፡ የተሟላ ዕውቀትን የሚያስገኙም ናቸውና፡ በዚህ ረገድ፡ የተገኘውን ዕውቀት፡ ተግባራዊ በማድረግ፡ እየራሳችሁን፡ ለ<u>"ፍጹሙ ኢትዮጵያዊነት"</u> ማብቃት ይቻላችኋል።

## ይህን እውነታ የሚያጸድቅ ዜናን
## ለማዘከር ያህል

ይህን ታላቅ ርእሰ-ነገር በሚመለከት፡ ከጥቂት ዓመታት በፊት፡ የደረሰና የኾነ አንድ እውነታ ስላለ፡ ያን እገልጥላችኋለሁ። ይህም እውነታ፡ በመንፈሳዊ ስሙ፡ ኪዳናዊ "ኃይለ-ኢየሱስ" ከተባለውና በቅርቡ፡ ወደእኛ ጠርተነው፡ በኣኹኑ ጊዜ፡ በእኛ ዘንድ ከሚገኘው፡ ከታማኙ ኢትዮጵያዊ ልጃችን ሕይወት ጋር በተያያዘው ዝክረ-ነገር የተከሠተው ነው።

ይኸው ዝክረ-ነገር፡ ኪዳናዊ ኃይለ-ኢየሱስን፡ ወደእኛ ልንወስደው መኾኑን፡ ቀደም አድርገን አስታውቀነው፡ በዚሁ ጥሪያችን መሠረት ከመጣ በኋላ፡ ዐብሮን ሣለ፡ ባለአደራችን ወላጁ፡ እርሱ፡ ከእርሷ፡ በአካለ-ሥጋ በመለየቱ፡ የደረሰባት ኀዘን ስለጸናባት፡ ከዚያ ሥቃይዋ ትጽናና ዘንድ፡ እርሱን፡ ወደእርሷ፡ በመንፈስ መልሰን በላክነው ጊዜ፡ ለእርሷና በእርሷ አማካይነት፡ ለሌሎቹ ኹሉ እንዲያደርስ የሰጠነውን፡ የምሥራች ዜናን ያካተተውን መልእክታችንን ይመለከታል።

ኪዳናዊ ልጃችን ኃይለ-ኢየሱስ፡ ይህን ተልእኮውን፡ ለኀዘነተኛዋ ወላጁ አድርሶ ለመፈጸም፡ በመንፈስና በራእይ የተገለጠላት፡ በምድር ላይ፡ በሕይወተ-ሥጋ ሣለ፡ በእውነተኛ ኪዳናዊነቱ፡ ያገለግልበት በነበረው ቤተ-መቅደስ ነበር፤ ይኼው መገለጡ የኾነውም፡ ወላጁን፡ በአካለ-ሥጋ ከተለያት፡ ከወራት በኋላ ቆይቶ፡ ለመጀመሪያ ጊዜ መኾኑ ነበር። እርሱም፡ በዚያ ቤተ-መቅደስ እንዳለ ኾኖ፡ ያን መልእክቱን፡ ለወላጁ በሚነግራት ጊዜ፡ ኢትዮጵያዊዉን ነጭ ልብሱን ተጐናጽፎና ኩታውን አደግድጎ ነበር።

በእርሱ አማካይነት የላክነውን፡ ይህንኑ መልእክት፡ ኹላችሁም ልታውቁት የሚያስፈልግ በመኾኑ፡ ቀደም ብለው፡ ይህን የምሥራች ዜና፡ በቀጥታ፡ ከወላጁ አንደበት ለመስማት እንደበቁት፡ እንደጥቂቶቹ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት ልጆቻችን ኹሉ፡ እናንተም፡ ሰምታችሁት፡ በመፈጸም ትጠቀሙበት ዘንድ፡ እዚህ ላይ፡ ይኸው ገልጬላችኋለሁ።

"የምወድድሽ ወላጇ ሆይ! በአካለ-ሥጋ ስለተለየሁሽ፡ ለምን ይህን ያህል አብዝተሽ አዘንሽ? ተይ! አይኾንም። እኔ፡ አኹን ህልውናዬን ቀጥዬ ያለሁት፡ በምድር ላይ፡ በሕይወተ-ሥጋ፡ ዐብሬሽ ሣለሁ፡ በትንሣኤ ሕይወት አሸናፊነትና በተድላ ገነት፡ እኖርባት በነበርሁባት፡ በዚያችው፡ **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** ውስጥ ነውና፡ በዚህ ተጽናኚ!

"ይህም የኾነው፡ ዘወትር ማለዳ፡ በየግላችን የምንደግማቸውን፥ በሥርዓተ-ቅዳሴያችንም ላይ የምናሰማቸውን፥ "የኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያውያት የሃይማኖት እና የቃል ኪዳን ጸሎቶች፥ ደግሞም፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት፡ የምስጋና ጸሎት እና ለድንግል ማርያም የሚያቀርቡት፡ የሰላምታ ጸሎት" የተባሉትን፡ አራቱን ጸሎቶች፡ በእውነት አምኜባቸው፡ በእየጊዜያቱ፡ ያለማቋረጥ፡ በቃሌ ስለምጸልያቸው ነው።

"አኹንም፡ አንቺም፥ የቀሩት መሰሎቻችን ኪዳናውያትና ኪዳናውያንም፥ ሌሎቹም ሰዎች ኹሉ፡ በምድር ላይ፡ በሕይወተ-ሥጋ እስከቆያችሁ ድረስ፡ እነዚህኑ ጸሎቶች፡ አምናችሁባቸው፡ በእግዚአብሔር እውነትና በምንፈስ ቅዱስ አምልኳችሁ ኾናችሁ፡ ከቻላችሁ፡ እንደእኔ፡ በቃላችሁ፥ ካልቻላችሁ ደግሞ፡ በጽሑፍ በመድገም፡ ሳታቋርጡ፡ በየቀኑ ጸልዩዋቸው!

"ይህን ካደረጋችሁ፡ ቀድሞ፡ እኔ፡ በሕይወተ-ሥጋ እያለሁ፡ **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** ውስጥ፡ ከክፋት፥ ከኃጢአትና ከሞት፡ ነጻ ኾኜ፡ በተድላ ገነት፡ እኖርበት በነበረው፡ በቅድስቲቱ የትንሣኤ-ሕይወትና በዘለዓለማዊቷ የሰንበት ዓለም፡ እናንተም ትኖራላችሁ።

"ወደፊት፡ ነፍሳችሁ፡ ከሕይወተ-ሥጋችሁ በምትለይበት ጊዜ ደግሞ፡ ይህንኑ የትንሣኤና የሰንበት ህልውናችሁን ለመቀጠል፡ ኹላችሁም የምትመጡት፡ እኔ፡ አኹን ወደምገኝባት፡ ወደዚችው፡ ወደ**ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** ይኾናል።

"ስለዚህ፡ አንቺ፡ አኹንም፡ በዚሁ የእምነት ጸሎትሽ ጸንተሽ ከቀጠልሽ፥ ወደፊት፡ **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** ውስጥ፡ በሕይወተ-ነፍስ የምንገናኝ መኾናችን ብቻ ሳይኾን፡ አኹንም እንኳ፡ እኔ፡ ይኸው፡ በዚችው፡ **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** ውስጥ፡ በመንፈስ፡ ዐብሬሽ እንዳለሁ ኹሉ፥ ወዳንቺ መጥቼም፡ እንዳየሁሽና እንዳነጋገርሁሽ ኹሉ፡ አንቺም፡ እንዲሁ፡ ከእኔ ጋር፡ ምንጊዜም፡ በመንፈስ፡ ዐብረሽኝ ስለምትገኚ፡ በአንቺ ዘንድ የሚኖረው ሕይወት፡ እንደእኔው፡ የደስታ እንጂ፡ የኀዘን አይኾንብሽም።"

## መፈጽም።

የምወድዳችሁ ልጆቼ ሆይ!

እንግዴህ፡ እኔ፡ የዘለዓለም እናታችሁ፡ እግዚአብሔር እም ኢትዮጵያ ድንግል ማርያም፡ በመንበረ-ጻባዖት ቅድስት ሥላሴነቴና እና በእግዚአብሔር መንግሥትነቴ፡ ከጌታዬ ከእግዚአብሔር አብና ከልጄ ከወዳጄ፡ ከእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ ጋር፡ ከመጀመሪያው፡ ለእያንዳንዳችሁና ለእየራሳችሁ፡ በተፈጥሮ ባስጌጥናችሁ፥ በመካከሉም፡ በቤዛነት ባጎናፀፍናችሁ፥ በፍጻሜው ዘመንና ዛሬም፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ዘውድነት፡ ባቀዳጀናችሁ፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ህልውናችሁ ዘንድ፡ በአጠቃላይ፡ የእኛ፡ **"የእግዚአብሔር ልጆች!"**፥ በተለይም፡ የእኔ፡ **"የኢትዮጵያ ልጆች"** ተብላችሁ በምትታወቁበት ማንነታችሁ፡ በዚህ፡ አኹን በምትገኙበት ምድራዊው ዓለም ውስጥ፡ የምትኖሩት፡ ይህ ሕይወታችሁ፡ ምን ዓይነት እንደሚኾን፡ በዚህ፡ በመለኮታዊው የዐዋጅ ቃሌ መፈጽም ላይ፡ እየነገርኋችሁ ላሳያችሁ!

**እኛ ያስገኘነው፡ የሥነ ፍጥረት ጸጋ [ስጦታ] የኾነው፡ ኹሉም ነገር፡ ፍጹም እውን ብቻ ነው፤ ፍጹም ቅዱስ ብቻ ነው፤ ፍጹም ንጹሕ ብቻ ነው፤ ፍጹም መልካም ብቻ ነው፤ ፍጹም ያማረ ብቻ ነው፤ ፍጹም የገነት ተድላ ብቻ ነው፤ ፍጹም ዘለዓለማዊ ነው።**

ሞትን የሚያስከትለው፡ ሓሰትና ክፉው፥ ከንቱ የኾነውም ነገር ኹሉ፡ አንዱም፡ በዚህ፡ የትንሣኤ ሕይወታችሁ እና የሰንበት ዓለማችሁ ዘንድ፡ ጨርሶ የለም።

ስለዚህ፡ በዐዋጅ መልክ ያቀረብሁላችሁን፡ ይህን መለኮታዊ ምዕዳኔን፡ ለእየራሳችሁ መዳንና ጥቅም ስትሉ፡ ተቀብላችሁ ትፈጽሙት ዘንድ፡ "አደራ!" እላችኋለሁ።

ይህንኑ የእናትነት አደራዬን በማጥበቅ፡ ለጊዜው የማሰናብታችሁ፡ ከእናንተ፡ ከእያንዳንዳችሁ፡ መልካሙን የንስሓ ፍሬአችሁን እንደማይ በማመን፡ የተለመደውን የኪዳነ ምሕረት በረከቴን፡ በኹላችሁም ላይ በማሳደር ብቻ አይደለም። የእኛ፥ የእኔና የእናንተም በኾነችው፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን ውስጥ ለምትኖሩት፡ ለዚህ፡ ለሚጠብቃችሁ፡ የትንሣኤ ሕይወታችሁ እና የሰንበት ዓለማችሁ የሚያበቃችሁን፡ የቅዱሱን ኪዳን ኢትዮጵያዊነት፡ የእምነትና የምግባር መመሪያ ሥርዓት የሚያሳውቋችሁን፡ ቀደም ብዬ የጠቀስሁላችሁን የጽሑፍ ሰነዶች፡ እኔው ራሴ፡ በዚሁ የዐዋጅ ቃሌ፡ ለእናንተ፡ ለልጆቼ፡ በማሰማትም ጭምር ነውና፡ አድምጡኝ! አድምጣችሁኝም፡ ለንስሓችሁ ፍሬያማነትም አብቁቸው!

የመጀመሪያው፡ በግእዙ፡-

## ጸሎተ ሃይማኖት፡ ዘኢትዮጵያ።

ንሕነ ኢትዮጵያውያን፥ ወኢትዮጵያውያት፡-

ነአምን፡ በአሓዱ አምላክ፡ እግዚአብሔር አብወእም፡ አኀዜ ኵሉ፥ ገባሬ ሰማያት ወምድር፡ ዘያስተርኢ፥ ወዘኢያስተርኢ።

ወነአምን፡ በትሥልስተ አሓዱ አምላክ፡ ዘግህደ በተዋሕዶ ህላዌሃ፥ ወበአካላ ለድንግል ማርያም፡ እንተ ይእቲ፡ መንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ፥ ወኢትዮጵያ፡ መንግሥተ እግዚአብሔር።

ወነአምን፡ በእግዚአብሔር ወልድ፡ አሐዱ እግዚእ፥ ወልድ ዋሕድ፡ እምእግዚአብሔር አብወእም፥ ዘህልው ምስሌሁ፡ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም፤ ውእቱ ኢየሱስ መሲሕ፥ ብርሃን፡ ዘእምብርሃን፥ አምላክ፡ ዘእምአምላክ፡ ዘበአማን፤ ዘተወልደ፡ ወአኮ ዘተገብረ፥ ዘዕሩይ ምስለ አብወእም፡ በመለኮቱ፤ ዘቦቱ፡ ኵሉ ኮነ፤ ወዘእንበሌሁሰ፡ አልቦ ዘኮነ፥ ወኢምንትኒ፥ ዘበሰማይኒ፥ ወዘበምድርኒ። ዘበእንቲአነ ለሰብእ፥ ወበእንተ መድኃኒትነ፡ ወረደ እምሰማያት፤ ተሰብአ፤ ወተሠገወ፤ ወኮነ፡ ብእሴ ፍጹመ፡ በነሢአ ሥጋ፡ እምሥጋሃ፥ ወነፍስ፡ እምነፍሳ፡ እምማርያም፡ እምቅድስት ድንግል፡ ዘተዋሓደት እግዚአብሔር አብወእም፡ በግብረ መንፈስ ቅዱስ ዘበቅድም። በመዋዕለ ጲላጦስ ጴንጤናዊ፡ ተሰቅለ፤ ወሓመ፥ ወሞተ፤ ወተቀብረ በእንቲአነ። ወተንሥአ እሙታን፡ አመ ሣልስት ዕለት። ዐርገ በስብሓት፡ ውስተ ሰማያት። ወነበረ፡ በየማነ አቡሁወእሙ፥ በመንበሩ ዘበዕሪና። ዳግመ ይመጽእ በስብሓት፤ ይኰንን፡ ሕያዋነ፥ ወሙታነ። ወአልባቲ ማኅለቅት ለመንግሥቱ፡ ዘተሰምየት፡ "ኢትዮጵያ"።

ወነአምን፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ። ውእቱ መንፈሰ ጽድቅ፥ ማኅየዊ ዘበአማን፥ ዘሠረፀ እምእግዚአብሔር አብወእም፥ ዘንሰግድ ሎቱ፥ ወንሰብሖ፡ ምስለ አብወእም፥ ወወልድ፥ ወዘነበበ በነቢያት፥ ዘወረደ ላዕለ ሓዋርያት፥ ወጸጋሁ፡ ዘመልዓ ዓለመ፡ በቤዛ መስቀሉ፡ ለኢየሱስ መሲሕ።

ወነአምን፡ በአሓቲ ቅድስት ኢትዮጵያ፡ መንግሥተ እግዚአብሔር፡ እንተ ይእቲ፡ ዘመሠረታ ኢየሱስ መሲሕ፡ እምጥንት፡ በኪዳነ ልቦና፡ ዘሰብአውያን ቀደምት፥ ወዘአጽንዓት፡ በቃለ ነቢያት፥ ወዘፈጸማ፡ በላዕለ ኵሉ ጉባኤ ዘሓዋርያት። በውስቴታ፡ ያቁርቡ ካህናት፡ መሥዋዕተ ሥጋሁ ቅዱስ፥ ወደሞ ክቡረ፡ ለኢየሱስ መሲሕ፤ ወባቲ ይትዌከፉ ምእመናን፥ ወምእመናት፡ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ዘዘዚአሁ።

ወነአምን፡ በአሓቲ ጥምቀት፡ ለስርየተ ኃጢአት።

ወነአምን፡ በትንሣኤ ሙታን፤ ወሕይወተ፡ ዘለዓለም። ለዓለመ ዓለም፤ አሜን።

በኢትዮጵያኛው፡-

## የኢትዮጵያ: የሃይማኖት ጸሎት።

እኛ ኢትዮጵያውያን እና ኢትዮጵያውያት፡-

ኹሉን በያዘ፥ ሰማይንና ምድርን፥ የሚታየውንና የማይታየውን በፈጠረ፡ አንድ አምላክ በሚኾን፡ በእግዚአብሔር አብወእም እናምናለን።

መንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴና የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ በኾነችው፡ በድንግል ማርያም፡ የተዋሕዶ አኗኗርና አካል በተገለጠው፡ በእግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት እናምናለን።

ዓለም ሳይፈጠር፡ ከእርሱ ጋራ በነበረ፥ አንድ የእግዚአብሔር አብወእም ልጅ፥ አንድ ጌታ በሚኾን፡ በእግዚአብሔር ወልድም እናምናለን። እርሱም፡ ከብርሃን የተገኘ ብርሃን፥ ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ አምላክ፥ የተወለደ እንጂ፡ ያልተፈጠረ፥ በመለኮቱ፡ ከአብወእም ጋራ የሚተካከል፥ ኹሉ፡ በእርሱ የኾነው፡ ኢየሱስ መሲሕ ነው። በሰማይ ካለው፥ በምድርም ካለው፡ ያለእርሱ፡ ምንም ምን የኾነ የለም። ስለእኛ ስለሰዎች፥ እኛን ለማዳን፡ ከሰማይ ወረደ፤ በመንፈስ ቅዱስ ቀዳሚ ግብር፡ እግዚአብሔር አብወእም ከተዋሓዷት፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም፡ ከሥጋዋ፡ ሥጋን፥ ከነፍሷም፡ ነፍስን ነሥቶ፡ ፍጹም ሰውን ኾነ። በጴንጤናዊው ጲላጦስ ዘመን፡ ስለእኛ መከራን ተቀበለ። ተሰቀለ። ሞተ። ተቀበረ። በሦስተኛውም ቀን፡ ከሙታን ተለይቶ ተነሣ። በክብር በምስጋና ወደሰማይ ዐረገ። በአባቱና እናቱም ቀኝ፡ በእኩያ ዙፋኑ ተቀመጠ። ዳግመኛም፡ በሕያዋንና በሙታን ለመፍረድ፡ በምስጋና ይመለሳል። "ኢትዮጵያ" ለተባለችው መንግሥቱም፡ ፍጻሜ የላትም።

በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም እናምናለን። እርሱም፡ ሕይወትን የሚሰጥ፥ ከእግዚአብሔር አብወእም የሠረፀና በነቢያት ዐድሮ የተናገረው፥ በሓዋርያት ላይ የወረደውና በኢየሱስ ክርስቶስ፡ የመስቀሉ ቤዛነት፡ ዓለሙን፡ በጸጋው የሞላው፡ ቅዱሱ የእውነት መንፈስ ነው። ለእርሱም፡ ከአብወእም እና ከወልድ ጋር እንሰግድለታለን፤ እናመሰግነዋለንም።

ኢየሱስ መሲሕ፡ ጥንት፡ በቀደሙት ሰዎች ኪዳነ ልቦና በመሠረታት፥ በነቢያት ቃል ባጸናትና በሓዋርያት ጉባኤ በፈጸማት፥ ካህናት፡ የእርሱን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም፡ ለመሥዋዕትነት በሚያቀርቡባት፥ ምእመናንና ምእመናትም፡ የመንፈስ ቅዱስን ጸጋዎች በሚቀበሉባት፡ በአንዲት ቅድስት ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት እናምናለን።

ኃጢአት በሚሰረይባት፡ በአንዲት ጥምቀት እናምናለን።

በሙታን ትንሣኤ፥ በዘለዓለምም ሕይወት እናምናለን። ለዘለዓለሙ፤ አሜን።

ኹለተኛው፡ በግእዙ፡-

## ጸሎተ ኪዳነ ቃል፡ ዘኢትዮጵያ።

**ንሕነ ኢትዮጵያውያን እና ኢትዮጵያውያት፡-**

*ነአምን በኢትዮጵያውናነ፡ ዘኪዳን ቅዱስ፥ ህልው በዓቂበ ቃላት ኪዳናውያት፥ እለ ወሀቦን እግዚአብሔር፡ ለውሉደ ሰብእ።*

*አምላክነ፡ ሣረረ ዝንቱ ሰብእና ኢትዮጵያዊ፡ በኪዳነ ልቦና፡ በዘኮነ እምሥርዓተ ሰብሳብ፡ ዘአዳም፥ ወሔዋን፡ በዘመነ ፍጥረት ቀዳማዊ፤ ወመትሎሁ፡ አዕረጎ ለዝ ሕንፃ፡ በቀስተ ደመናሁ፡ ለኖኅ፥ ወበቍርባኑ፡ ዘመልከ-ጼዴቅ፥ ወበግዝረቱ፡ ዘአብርሃም፤ ወበዘመነ ሕግ ማእከላይ፡ ነደቆ ማኅፈዱ፡ በጽላተ ሙሴ፥ ወበመንበረ ዳዊት ፡ ዘግህደ በፅምረተ አሥራወ ዘርያሙ፡ ለንግሥት ማክዳ ኢትዮጵያዊት፥ ወለንጉሥ ሰሎሞን እስራኤላዊ፣ ከመ ያስተሰነአዎ ኵለንታሁ፡ በኪዳነ ኦሪት።*

*ወእምድኅረ አጽንዖቱሰ፡ በሥጋሁ ወደሙ ለኢየሱስ መሲሕ፡ ወልዱ፡ ዘተወልደ እምድንግል ማርያም፡ እንተ ሠረፀት፡ እምዛቲ ሥርው ምልዕት፡ አስተቄጸሎ አክሊል ዘለዓለም፡ በፍጻሜ ዘመን፡ ዘሕይወት፡ በኪዳነ መንፈስ ቅዱስ።*

*በእንተዝ ነአምን፡ ከመ ይእቲ ኢትዮጵያ፡ መንግሥተ እግዚአብሔር፡ እንተ ገዝፈት በሰብእናሁ ለኢትዮጵያዊ፡ ዘኪዳን ቅዱስ፡ እንዘ በኅቤሁ የኀብሩ፡ ቤተ ሕዝባ፥ ወቤተ ክህነታ፥ ወቤተ ምልክናሃ፡ በአሠረ ተዋሕዶ።*

*ንሕነ፡ እለ ተሠየምነ "ክርስቲያን"፡ በስመ ዚአሁ፡ ዘተብህለ "ክርስቶስ"፡ ነአምን፡ ከመ ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ካህንነ፥ ወንጉሥነ ዘለዓለም፡ በሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊ፡ ዘአስተርአየ በመዋዕል ቀዳማዊ፤ ወዘኮነ አርአያሁ ለክርስቶስ፣ በልደቱ ዘኮነ እምትሥልስተ ዘርዕ፡ ዘእምአንጋደ ሴም፥ ወካም፥ ወያፌት።*

*ንሕነ፡ እለ ተሠየምነ "ደቂቀ ኢትዮጵያ"፡ በስመ ዚአሃ፡ ዘተብህለት፡ "ኢትዮጵያ"፡ ነአምን፡ ከመ ይእቲ ድንግል ማርያም፡ ዕፀ ሕይወት፥ ወእመ-ሕያዋን አማናዊት፥ ወታቦተ ጽዮን ዘለዓለማዊት፥ ወንግሥተ-ሰማያት ወምድር፡ በዘወሊዶታ ለአምላክ።*

*ነአምን፡ በቀስተ ደመና፡ ዘተሠርገወ፡ በሠለስቱ ዓበይት ኅብረ ቀለማት፡ ዘውእቶን፡ ሓመልሚለ፥ ወወርቀ፥ ወቀይሓ፡ ዘተውህበ ለነ እምእግዚአብሔር፡ እንተ በኀበ ኖኅ፡ ከመ ውእቱ ይኩነነ፡ ትእምርተ ኪዳን ዘለዓለም።*

*ነአምን፡ በማኅተምነ ዘለዓለም፡ ዘረከብነ እምአምላክነ፡ ወበዘውእቱ ዘተነግረበእንተ ኢየሱስ መሲሕ፡ መፈጽም ለኪዳኑ ቅዱስ፡ በዝንቱ ቃል ዘመለኮት፡ እንዘ ይብል፡ "ሞአ አንበሳ፡ ዘእምነገደ ይሁዳ!"፥ ወበቃለ ትንቢት ዘተነግረ፡ በእንተ ማርያም ድንግል፡ እንዘ ይብል፡ "ኢትዮጵያ ታበጽሕ፡ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር!"።*

ነአምን፡ ከመ ንሕነ፡ ወራስያነ መንግሥቱ፥ ወካህናቲሁ ለእግዚአብሔር፡ በእንተ ወልድናነ፡ በዘውእቱ ዘተከለልነ፡ በክብረ ልደት እምእግዚአብሔር፡ በመንፈስ፡ እንበይነ ጸጋሁ፡ ዘኪዳኑ ቅዱስ።

ነአምን፡ ከመ ብነ ይደልወነ፡ ንሄሉ በንስሓ፡ እንበለ ፅርዓት፡ ለስርየተ ኃጢኣት፥ ወበተመጥዎተ ሥጋሁ፥ ወደሙ፡ ለኢየሱስ መሲሕ፡ ለአጽንዖተ ዝንቱ ወልድናነ፥ ወለትውክልተ ውርስናነ ዘመንግሥቱ፥ ወለዝልፈተ ተልእኮትነ ንጹሕ።

ነአምን፡ ከመ ውእቱ ሃይማኖትነ ዘኢትዮጵያውና፡ ገሃደ ይወጽእ፥ ወቅድስናሁ ይትአወቅ በምግባሪነ፡ ዘኢትዮጵያውና፡ ዘንፈጽም፡ በተዋሕዶተ ፍቅርነ፡ ለኢየሱስ መሲሕ፥ ወለድንግል ማርያም።

ነአምን፡ ከመ እግዚአብሔር ውእቱ፡ ዘጸሓፈ ኢትዮጵያውናነ፡ ዘኪዳን ቅዱስ፡ በልቦናነ፤ ወመሀረነ፤ ወረሰየነ፡ ንዕቀቦ በህልዎትነ፡ በእንተ ቃለ ኪዳኑ። ለዓለመ ዓለም፤ አሜን።

**በኢትዮጵያኛው፡-**

## <u>የኢትዮጵያ፡ የቃል ኪዳን ጸሎት።</u>

**እኛ ኢትዮጵያውያን እና ኢትዮጵያውያት፡-**

እግዚአብሔር፡ ለሰው ልጆች የሰጣቸውን ቃል ኪዳናት፡ ጠብቆ በኖረው፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችን እናምናለን።

አምላካችን፡ ይህን ኢትዮጵያዊ ሰውነት፡ **በመጀመሪያው የፍጥረት ዘመን፡** በአዳምና ሔዋን ሥርዓተ ጋብቻ፡ **በኪዳነ ልቦና መሠረተው፤** ከዚያም፡ በኖኅ ቀስተ ደመና፥ በመልከ ጼዴቅ ቍርባንና በአብርሃም ግርዛት፡ **ገንብቶ አሳደገው፤ በመካከለኛውም የሕግ ዘመን፡** በሙሴ ጽላትና በዳዊት ዙፋን አዋቅሮ፥ የኢትዮጵያዊቷን ንግሥት፡ የማክዳንና የእስራኤላዊዉን ንጉሥ፡የሰሎሞንን የዘር ሓረጎች በማዋሓድ፡ **በኪዳነ ኦሪት አከናወነው፤ በመጨረሻውም የሕይወት ዘመን፡** ከዚህ ምሉእ ትውልድ ከተገኘችው፡ ከድንግል ማርያም በተወለደው ልጁ፡በኢየሱስ መሲሕ ሥጋና ደም አጽንቶና ዘለዓለማዊዉን ዘውድ አቀዳጅቶ፡ በኪዳነ መንፈስ ቅዱስ ፈጸመው።

ኢትዮጵያ፡ እንዲህ በቀጠለው፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊው ሰውነት፡ ቤተ ሕዝቧን፥ ቤተ ክህነቷንና ቤተ ምልክናዋን፡ አንድ አድርጋ የኖረች፡ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደኾነች እናምናለን።

እርሱ፡ "ክርስቶስ" ተብሎ፡ እኛን፡ "ክርስቲያን" ያሰኘን፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ በቀደመው ዘመን፡ ምሳሌው ኾኖ በተገለጠው፡ በመልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊነትና ሹመት፡ ከሴም፥ ከካምና ከያፌት ዘሮች ተወልዶ፡ የዘለዓለም ካህናችንና ንጉሣችን እንደኾነ እናምናለን።

እርሷ፡ "ኢትዮጵያ" ተብላ፡ እኛን፡ "የኢትዮጵያ ልጆች" ያሰኘችን፡ ድንግል ማርያም፡ አምላክን በመውለዷ፡ አማናዊቷ የሕይወት ዛፍ፥ የሕያዋን እናትና፥ ዘለዓለማዊቷ ታቦተ ጽዮን፥ የሰማይና የምድር ንግሥትም እንደኾነች እናምናለን።

አረንጓዴ ብጫ ቀይ የኾነው፡ የቀስተ ደመና ምልክት፡ በኖኅ አማካይነት፡ ከእግዚአብሔር የተቀበልነው፡ የዘለዓለም ሰንደቅ ዓላማችን እንደኾነ እናምናለን።

የቅዱሱ ኪዳን ፍጻሜ ለኾነው፡ ለኢየሱስ መሲሕ የተነገረው፡ "ከይሁዳ ነገድ የኾነው አንበሳ፡ ድል ነሣ!" የሚለው መለኮታዊ ቃልና ለድንግል ማርያም የተነገረው፡ "ኢትዮጵያ፡ እጆቿን፡ ወደእግዚአብሔር ትዘረጋለች!" የሚለው ትንቢታዊ ቃል፡ ከአምላካችን ያገኘነው፡ የዘለዓለም ማኅተማችን እንደኾነ እናምናለን።

በቅዱሱ ኪዳን ጸጋ፡ ከእግዚአብሔር፡ በመንፈስ የመወለድን ክብር ስላገኘን፡ በዚህ ልጅነታችን፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ወራሾችና አገልጋዮች እንደኾንን እናምናለን።

ይህን ልጅነታችንን፡ አጽንተን ለመጠበቅ፥ የመንግሥቱ ወራሽነታችንን፡ ለማረጋገጥና ንጹሕ አገልግሎታችንን ለመቀጠል፡ ኃጢኣታችንን፡ ዘወትር በንስሓ እያጠራንና የኢየሱስ መሲሕን ሥጋና ደም እየተቀበልን፡ መኖር እንዳለብን እናምናለን።

የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታችን፡ በይፋ የሚገለጠውና ተለይቶ የሚታወቀው፡ በኢየሱስ መሲሕና በድንግል ማርያም የተዋሓደ ፍቅር ኾነን በምንፈጽመው፡ የኢትዮጵያዊነት ምግባራችን እንደኾነ እናምናለን።

የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችንን፡ በየልቦናችን ጽፎ ያስተማረን፥ ጠብቀነው እንድንኖር ያደረገም፡ እንደቃል ኪዳኑ፡ እግዚአብሔር እንደኾነ እናምናለን። ለዘለዓለሙ፤ አሜን።

ሦስተኛው፡ በግእዙ፦

## ጸሎተ ስባሔ ለእግዚአብሔር፡
## ዘደቂቀ ኢትዮጵያ።

አ አቡነ እግዚአብሔር! ነአኵተከ እግዚኦ፥ ወንሴብሓከ፤ ንባርከከ እግዚኦ፥ ወንትአምነከ፤ ንገኒ ለከ እግዚኦ፥ ወንትቀነይ ለስምከ ቅዱስ፤ ንሰግድ ለከ፤ አ ዘለከ! ይሰግድ ኵሉ ብርክ፤ ወለከ ይትቀነይ፡ ኵሉ ልሳን።

አንተ ውእቱ፡ አምላከ አማልክት፤ ወእግዚአ አጋእዝት፤ ወንጉሠ ነገሥት። አምላክ አንተ፡ ልኵሉ ዘሥጋ፤ ወለኵላ ዘነፍስ። ወንዔውዐከ፣ በእንተ ዘተወከፍከ ዝንቱ ጸሎትነ፡ በቤዝዎቱ ለወልድከ፡ ዘመሀረነ ለሊሁ ኢየሱስ መሲሕ፡ እንዘ ይብል፡ "አንትሙሰ፡ ሶበ ትጼልዩ፡ ከመዝ በሉ፦ 'አቡነ ዘበሰማያት! ይትቀደስ ስምከ! ትምጻእ መንግሥትከ! ወይኩን ፈቃድከ፡ በከመ በሰማይ፡ ከማሁ በምድር! ሲሳየነ፡ ዘለለዕለትነ፡ ሀበነ ዮም! ሕድግ ለነ፡ አበሳነ፥ ወጌጋየነ፣ ከመ ንሕነኒ ንሕድግ ኵሎ፡ ለዘአበሰ ለነ!

ኢታብአነ እግዚኦ፡ ውስተ መንሱት! አላ አድኅነነ፥ ወባልሃነ፡ እምኵሉ እኩይ! እስመ ዚአከ፡ ይእቲ መንግሥት፥ ኃይል፥ ወስብሓት፤ ለዓለመ ዓለም።'"

ወበእንተ ዘአብዛኅከ ለነ፡ ኂሩትከ፤ ወዘገበርከ ለነ፡ ምሕረትከ፤ ወዘፈጸምከ ለነ፡ ፍቅርከ፤ ወዘወሀብከነ ጸጋከ፡ ለከዊነ ነፍስነ፥ ወሥጋነ።

ወረደ ለነ፡ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ፡ ውስተ ኵሉ ዓለም፡ በምክንያተ ቤዛ ወልድከ መድኅን፡ ዘተወልደ እምቅድስት ድንግል ማርያም። በእንተዝ ኮነ ይእዜ፡ ዘትሄሉ አንተ በምድር፣ አኮ በሰማይ ባሕቲቱ። ወዓዲ፡ ተቀደሰ ስምከ በምድር። ወመጽአት መንግሥትከ። ፈቃድከ፡ ዘኮነ በሰማይ፡ ከማሁ፡ ኮነ በምድርኒ።

አስተዳለውከ በሥነ ፍጥረት፡ምግበ ሥጋነ፡ ዘይበቍዕ ለመፍቅደ ኵሉ ሀልዎትነ፤ ወአኮ ሲሳይ ዘለለዕለትነ ባሕቲቱ። ወመጦከነ በኵሉ ጊዜ፡ ሥጋ ወልድከ ቅዱስ፥ ወደሞ ክቡረ፣ ዘኮነ ለነ፡ ምግበ ነፍስ፥ ወመድኃኒት፣ ዘይረስየነ ሕያዋን ዘለዓለም፤ ወበውእቱሰ፡ ደምሰስከ፥ ወኃደግከ ለነ፡ ኵሎ ኃጢአተነ፥ ወአበሳነ ግሙራ፥ ወዘኢማእዜ፤ ወከማሁ አባሕከነ፡ ከመ ንሕነኒ ንኅድግ ኵሎ፡ ለዘአበሰ ለነ።

ወዐልዓልከነ፡ በልደተ መንፈስ ቅዱስ፡ ዘጥምቀት፡ በዘውእቱ በጻሕነ፡ ከመ ንኩን ውሉድከ፥ ወአዋልድከ፤ ወበጸጋከ፡ ዘንስሓ።

ወአውጻእከነ፡ እመንሱት ዘዘዚአሁ፤ ወአድኃንከነ፡ እምኵሉ እኩይ፤ ወሞዕክዎ፡ ለዲያብሎስ፤ ወአሰሰልከ፡ ለሞት፤ ወበእንተ ዝንቱ፡ አሠለጥከነ፡ ንሄሉ፡ በሕይወተ ትንሣኤከ።

ኦ እግዚኦ! ንሴብሓከ ወትረ፡ በእንተ ኂሩትከ፥ ወምሕረትከ፥ ወፍቅርከ፥ ወጸጋከ፡ ዘአወፈይከነ፡ በዘኢይትከሃል ይትነገር መጠኖሙ፤ ወዓዲ፡ በእንተ ዘትሁበነ፡ ኵሎ ዘንፈቅድ፡ እንዘ አኮ ዘንሰአለከ።

ንጸንሕ፡ በከመ አሰፈውከነ፡ ለምጽአተ ዛቲ መዋዕል፡ እንተ ባቲ ትኄንን መንግሥትከ አማናዊት፡ ዘንጉሥነ ኢየሱስ መሲሕ፥ ዘተብህለ፡ "ሞ'አ አንበሳ፡ ዘእምነገደ ይሁዳ!"፥ ወንሄሉ ንሕነ ይእዜ በውስቴታ፡ ከመ ትትረአይ፥ ወትሰፍን በገሃድ፥ በዝንቱ ዓለም፡ እምድኅረ ትሜርዎሙ፡ ለእከይ፥ ወለኃጢአት፥ ወለሞት። እስመ ለከ፡ ኃይል፥ ወስብሓት፥ ወመንግሥት። ይእዜኒ፥ ወዘልፈኒ፥ ወለዓለመ ዓለም፤ አሜን።

በኢትዮጵያኛው፡-

## የኢትዮጵያ ልጆች፡
## ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት፡ የምስጋና ጸሎት።

አባታችን እግዚአብሔር ሆይ! እናመሰግንሃለን፤ አቤቱ እናወድስሃለን፤ እንቀድስሃለን፤ አቤቱ እንታመንብሃለን፤ እናገንንሃለንም፤ ጕልበት ኹሉ፡ ለአንተ ይሰግዳል፤ አንደበትም ኹሉ፡ ወደአንተ ይጮሃል። አንተ፡ የአማልክት አምላክ ነህ፤ የገዢዎች ገዢ ነህ፤ የንጉሦችም ንጉሥ ነህ። አንተ፡ የሥጋዊው ኹሉ፥ የነፍሳዊዉም ኹሉ ወገን ፈጣሪ ነህ።

"እናንተ ስትጸልዩ፡ 'የሰማዩ አባታችን ሆይ! ስምህ ይቀደስ!መንግሥትህ ትምጣ! ፈቃድህ በሰማይ እንደ ኾነ፡ በምድርም፡ እንዲሁ ይኹን! የየዕለቱን ምግባችንን፡ ስጠን ለዛሬ! ኃጢአታችንንና በደላችንን፡ ይቅር በለን! እኛም የበደሉንን፡ ይቅር እንደምንል! አቤቱ ወደፈተና አታግባን! ከክፋው ኹሉ፡ አድነን እንጂ! መንግሥት፡ የአንተ ናትና፥ ኃይልና ምስጋናም፤ ለዘለዓለሙ።' በሉ!" ብሎ፡ ልጅህ ኢየሱስ መሲሕ፡ ያስተማረንን ጸሎታችንን፡ በእርሱው ቤዛነት ተቀብለህ፡ ለነፍሳችንና ለሥጋችን፡ ቸርነትህን አበረከትህልን፤ ምሕረትህን አደረግህልን፤ ፍቅርህን ፈጸምህልን፤ ጸጋህንም ሰጠኸን። ስለዚህ፡ ይኸው አኹን እኛም፡ እንደዚሁ፡ ስምህን እየጠራን፡ እናመሰግንሃለን።

ከቅድስት ድንግል ማርያም በተወለደው ልጅህ መድኃኒትነት፡ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ፡ በዓለሙ ኹሉ ወረደልን። ስለዚህ፡ በሰማይ ብቻ ሳይኾን፡ ዛሬ በምድርም፡ የምትኖር ኾንህ። ስምህ፡ በምድርም ተቀደሰ። መንግሥትህም መጣችልን። በሰማይ የኾነው ፈቃድህ፡ በምድርም፡ እንዲሁ ኾነ።

የዕለት እንጀራችንን ብቻ ሳይኾን፡ በዕድሜያችን ኹሉ፡ የሚያስፈልገንን ምግበ ሥጋ፡ በሥነ ፍጥረት አዘጋጀህልን። ለዘለዓለም ሕያዋን የሚያደርገንን፥ መድኃኒትና ምግበ ነፍስ የኾነንንም፡ የልጅህን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም፡ ለዘወትር ሰጠኸን። በእርሱም፡ ኃጢአታችንንና በደላችንን ኹሉ፡ ለመቼውም ጊዜ ደምስሰህ" ፈጽመህ ይቅር ቅልኸን። እኛም፡ የበደሉንን ኹሉ፡ ይቅር እንድንል አስቻልኸን።

የአንተ ልጆች ለመኾን የምንበቃበትን፡ የጥምቀትን ልደትና የንስሓን ጸጋ አደልኸን። ከማናቸውም ፈተና አውጥተኸንና ከክፋው ኹሉ አድነኸን፥ ዲያብሎስንና ሞትንም፡ ድል አድርገህ፡ በትንሣኤህ ሕይወት ለመኖር አበቃኸን።

ጌታ ሆይ! ሊነገር ስለማይቻል ቸርነትህና ምሕረትህ፥ ፍቅርህና ጸጋህ፥ እንዲሁም፡ የሚያስፈልገንን ኹሉ፡ ሳንለምንህ ስለምትሰጠን፡ ዘወትር እናመሰግንሃለን።

"ከይሁዳ ነገድ የኾነው አንበሳ፡ ድል ነሣ!" በተባለው፡ በንጉሣችን፡ በኢየሱስ መሲሕ፡ ዛሬ የምንኖርባት፡ የእውነት መንግሥትህ፡ ክፋትን፥ ኃጢአትንና ሞትን፡ ፈጽማ አጥፍታ፡ ለግዙፉ ዓለም፡ በገሃድ የምትገለጥበትንና በይፋ የምትሰፍንበትን ጊዜ፡ እንደተስፋ ቃልህ እንጠብቃለን።

ኃይልና ምስጋና፥ መንግሥትም፡ የአንተ ናቸው፤ ዛሬም፡ ዘወትርም፤ ለዘለዓለሙ፤ አሜን።

አራተኛው፡ በግእዙ፡-

## ጸሎተ ሱላሜ፡ ለድንግል ማርያም፡
## ዘደቂቀ ኢትዮጵያ።

ኦ ማርያም እምነ! ንብለኪ፡ "ሰላም ለኪ!" በሰላመ ቅዱስ ገብርኤል መልአክ። ድንግል በኅሊናኪ፤ ወድንግል በሥጋኪ። ይደልወኪ ዝ ሱላሜ፣ እስመ አንቲ፡ እሙ ለእግዚአብሔር ጸባዖት፡ በእንተ ዛቲ ንጽሓ ባሕርይኪ።

አንቲ ይእቲ ሔዋን ቅድስት፤ ወቡርክት፡ እምኵሎን አንስት፡ በእንተ ዘአሥረፀ ማሕፀንኪ፡ ፍሬሁ፡ ዘዕፀ ሕይወት፣ በዘውእቱ ኮነ፡ አዳምሁ ቅዱሰ።

ተፈሥሒ! ኦ ንግሥትነ፡ በሰማይ፥ ወበምድር! እስመ ዘተወደስኪ ጥንት፡ በአፈ ነቢያት፡ እንዘ ይብሉኪ፡ "ኢትዮጵያ ታበጽሕ፡ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር!"፥ ወንሕነኒ በዘሀልዎትነ፡ እንዘ ንብለኪ፡ "እምነ ጽዮን!"

ንቄድሰኪ ወትረ፡ እንዘ ንብል፡ "ብፅዕት አንቲ፡ ኦ ምልዕተ ጸጋ!" እስመ ዐተበ እግዚአብሔር፡ ኪዳኖ ዘምሕረት፡ ለዓለመ ዓለም፡ በዘአጥረየኪ አንቲ፡ ለምክንያተ ድኅነትነ።

ነአምን፡ ከመ ኢተግሕሠ ክመ እምኔነ፡ ማሕፀንተኪ፡ በአምጣነ እንተ ኢተግሕሠ፡ እምፍቁር ወልድኪ፤ እስመ አንቲ ይእቲ፡ እምነ ዘምሕፀና፤ ወንሕነ፡ ውሉድኪ፥ ወአዋልድኪ፡ ዘምሕፅና፡ በቃለ አማሕፅኖ ዘወልድኪ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ አምላክነ፥ ወመድኃኒነ።

ነአኵቶ ለእግዚአብሔር ልዑል፡ አቡነ ኄር፡ በእንተ ዛቲ ኂሩቱ፡ ዘተገብረት ለነ። ለዓለመ ዓለም፤ አሜን።

በኢትዮጵያኛው፡-

## የኢትዮጵያ ልጆች፡
## ለድንግል ማርያም የሚያቀርቡት፡ የሰላምታ ጸሎት።

እናታችን ማርያም ሆይ! በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል ሰላምታ፡ "ሰላም!" እንልሻለን። በአሳብሽ፡ ድንግል ነሽ፤ በሥጋሽም፡ ድንግል ነሽ። በዚህ የንጽሕና ባሕርይሽ፡ የአሸናፊው የእግዚአብሔር እናት ኾነሻልና፡ ሰላምታ፡ ለአንቺ ይገባል።

ማሕፀንሽ፡ የሕወት ዛፍ ፍሬ የኾነውን፡ ቅዱሱን አዳም ስላስገኘ፡ አንቺ፡ ከሴቶች ኹሉ ተለይተሽ የተባረክሽ፡ ቅድስቲቱ ሔዋን ነሽ።

ቀድሞ በነቢያት፡ "ኢትዮጵያ፡ እጆቿን፡ ወደእግዚአብሔር ትዘረጋለች!" የተባልሽ፥ እኛም፡ "እናታችን ጽዮን!" ስንልሽ የኖርን፡ በሰማይና በምድር ንግሥታችን ሆይ! ደስ ይበልሽ!

እግዚአብሔር፡ አንቺን፡ የድኅነታችን ምክንያት አድርጎ፡ ኪዳነ ምሕረቱን፡ ለዘለዓለም ፈጽሚልና፡ "ጸጋን የተመላሽ፡ ብፅዕት ነሽ!" እያልን፡ ዘወትር እናወድሻለን።

በአምላካችንና በመድኃኒታችን፡ በኢየሱስ መሲሕ፡ አንቺ፡ ለእኛ፡ የአደራ እናታችን፥ እኛም፡ ለአንቺ፡ የአደራ ልጆችሽ ነንና፡ ከተወደደው ልጅሽ ያልተለየው እናትነትሽ፡ ከእኛም፡ ምንጊዜም፡ እንደማይለየን እናምናለን። ይህን ያደረገ ቸሩ አባታችን ልዑል እግዚአብሔርን፡ እናመሰግነዋለን። ለዘለዓለሙ፤ አሜን።

**አምስተኛው፡ በግእዙ፡-**

**ቃለ አሚኖት፡ ዘደቂቀ ኢትዮጵያ**



**ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ**
**ኢየሱስ መሢሕ**
**ካህኑ ለዓለም፡ በከመ ሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊ**
**ንጉሠ ጽዮን፥ ወንጉሠ ነገሥት**

The Triumphant Lion of the Tribe of Judah
Jesus Christ
Eternal Priest in the Order of Melche-Zedeq the Ethiopian
King of Zion and King of Kings of Ethiopia

**ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር**
**ድንግል ማርያም**
**እሙ ለአምላክነ፥ ወእምነ ዘዚአነ**
**ንግሥተ ጽዮን ወንግሥተ ነገሥታት ዘኢትዮጵያ**

Ethiopia stretches out Her Hands to God
The Virgin Mary
Mother of God and Our Holy Mother
Queen of Zion and Ethiopia

---

**አነ____________________________________________________፥ ወስምየ ዘክርስትና _______________________________________________________________፥ ወልደትየ ዘኮነ በወርኃ__________________፥ በ________ዕለት፥__________________ዓ. ም. በሀገረ ________________________________________________፤ ዮም፡ በዝ ወርኃ__________________፥ በ________ዕለት፥__________________ዓ. ም. እቀውም፡ በቅድመ መንበሮሙ ለኢየሱስ ክርስቶስ ወለድንግል ማርያም፡ በአምልኮተ ጽድቅ ዘመንፈስ ቅዱስ፡ ወናሁ አሰምዕ ስምዕየ በአጽንዖት፣ እንዘ እብል፡-**

**"አነ ውእቱ ኢትዮጵያዊ/ት ዘኪዳን ቅዱስ፡ ዘእሄሉ፡ በዐቂበ ርትዕት ሃይማኖትየ፡ ጽሪት፡ በምሥጢረ ተዋሕዶ፡ እንተ ተመሥረት፡ በዝንቱ ኪዳን ቅዱስ፡ ዘውእቱ መዝገቦሙ ለሰብዓቱ ኪዳናት፡ ዘተካየዶን እግዚአብሔር ምስለ ሰብእ፣ እላንቱ፡ ዘተወጥና በአዳም ወሔዋን፥ ወተሓደሳ በሰብእናሆሙ ለኖኅ፥ ወለመልከ ጼዴቅ፥ ወለአብርሃም፥ ወለሙሴ፥ ወለዳዊት፡ እስከልደተ ኢየሱስ ክርስቶስ እምድንግል ማርያም፡ ዘተፈጸማ በዛቲ ትስብእት፥ ወዘተግህደት በምግባርየ፥ ወዓዲ ዘእሄሉ በአንጽሖተ ርእስየ፡ በንስሓ፥ ወበአጽድቆተ ሰብእናየ፡ በተመጥዎተ ሥጋሁ ቅዱሰ ወደሞ ክቡረ።**

**"ኦ አምላኪየ ወመድኃኒየ፥ ካህንየ ወንጉሥየ ኢየሱስ ክርስቶስ! እሰግድ በቅድመ መንበርከ ወእሴብሓከ፡ እስመ አብቍዐተኒ ከመ በክሡት አሰምዕ፡ ዝ ስምዕ፡ በተአምኖትየ ዘቃልከ መለኮታዊት፡ ዘትብል፡ 'ኵሉ ዘየአምን ብየ፡ በቅድመ ሰብእ፡ አነሂ አአምኖ፡ በቅድመ አቡየ ዘበሰማያት፤ ወዘሰ ክሕደኒ በቅድመ ሰብእ፡ አነሂ እክሕዶ፡ በቅድመ አቡየ ዘበሰማያት።'"** (ማቴ. ፲፥ ፴፪-፴፫።)

**"ኦ ቅድስት ድንግል ማርያም፥ ሃይማኖትየ ወሀገርየ፥ እምየ ወንግሥትየ እምኀበ ኢየሱስ ክርስቶስ! አበርክ ቅድመ መንበርኪ ወአቀርብ ለኪ፡ አምኃየ ዘስባሔ፡ በቃለ ገብርኤል መልአክ ቅዱስ፡ እስመ በፍቅርኪ ወበረድኤትኪ፡ ኮንክኒ ማሕፀንትየ፡ ከመ እጽናዕ በኢትዮጵያውናየ ዘቅዱስ ኪዳን፡ በኵሉ መዋዕልየ። አሜን።"**

**በኢትዮጵያኛው፡-**

**<u>የኢትዮጵያ ልጆች፡ የታማኝነት ማረጋገጫ ቃል</u>**



ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
ኢየሱስ መሢሕ
ካህኑ ለዓለም፡ በከመ ሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊ
<u>ንጉሠ ጽዮን፥ ወንጉሠ ነገሥት</u>

The Triumphant Lion of the Tribe of Judah
Jesus Christ
Eternal Priest in the Order of Melche-Zedeq the Ethiopian
King of Zion and King of Kings of Ethiopia

ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር
ድንግል ማርያም
እሙ ለአምላክነ፥ ወእምነ ዘዚአነ
<u>ንግሥተ ጽዮን ወንግሥተ ነገሥታት ዘኢትዮጵያ</u>

Ethiopia stretches out Her Hands to God
The Virgin Mary
Mother of God and Our Holy Mother
Queen of Zion and Ethiopia

---

እኔ፡ ______________________ ፥ በክርስትና ስሜ ______________________ የተባልሁ፥ በ ________________ ቀን፥ ______________ ዓ. ም. በ ______________________ የተወለድሁ፡ ዛሬ፡ በዚህ በ ________________ ቀን፥ ____________ ዓ. ም. በኢየሱስ መሲሕና በድንግል ማርያም መንበር ፊት፡ በእውነተኛው የመንፈስ ቅዱስ አምልኮ ቆሜ፡ እንዲህ እያልሁ፡ የምስክርነት ቃሌን በማረጋገጥ እሰጣለሁ።

“እኔ፡ በኢትዮጵያ የሃይማኖትና የቃል ኪዳን ጸሎቶች ውስጥ እንደተገለጸው፡ በአዳምና ሔዋን ተጀምሮ፡ በኖኅ፥ በመልከ ጼዴቅ፥ በአብርሃም፥ በሙሴና በዳዊት በኩል እየታደሱ፡ እስከኢየሱስ መሲሕና ድንግል ማርያም ደርሶ በተፈጸመው፥ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የተደረጉትን፡ ሰባቱን ኪዳናት በአጠቃለለው፡ በቅዱሱ ኪዳን ተመሥርታ የቆመችውን፥ በምሥጢረ ተዋሕዶ የጠራችውንና የቀናችውን ሃይማኖቴን ጠብቄና በምግባር አጽንቼ፡ ራሴን፡ በንሥሓና በሥጋ ወደሙ እያጸደቅሁ የምኖር፡ **የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊ/ት ነኝ።**

“አምላኬና መድኃኒቴ፥ ካህኔና ንጉሤ ኢየሱስ መሲሕ ሆይ!"**በሰው ፊት፡ በእኔ አምኖ ለሚመሰክርልኝ ኹሉ፡ እኔ ደግሞ፡ በሰማያት በአለው አባቴ ፊት፡ ስለታማኝነቱ እመሰክርለታለሁ። በሰው ፊት የሚክደኝንም፡ እኔ ደግሞ፡ በሰማያት በአለው አባቴ ፊት፡ ስለክህደቱ እመሰክርበታለሁ።"** ያልከውን መለኮታዊ ቃልህን አምኜ፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነቴ፡ ይህን የምስክርነት ቃል፡ በይፋ እንድሰጥ ስላበቃኸኝ፡ በመንበርህ ፊት እየሰገድሁ አመሰግንሃለሁ። (ማቴ. ፲፥ ፴፪-፴፫።)

“በኢየሱስ መሲሕ፡ ሃይማኖቴና አገሬ፥ እናቴና ንግሥቴ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ! በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነቴ ጸንቼ እኖር ዘንድ፡ በፍቅርሽና በረድኤትሽ ስላልተለየሽኝ፡በመልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ቃል፡ በመንበርሽ ፊት ሰግጄ፡ የምስጋና ሰላምታዬን አቀርብልሻለሁ። አሜን።

\+ \+ \+

**ተዐውደ፡ በታኅሣሥ ፲፮ ቀን፥ ፳፻፰ ዓመተ ምሕረት ታወጀ።**

**ላእከ ኢትዮጵያ፡ ዘመንግሥተ እግዚአብሔር፣**
**የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ አገልጋይ፣**
**ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ፤**
**ስመ ጥምቀቱ፡ ኂሩተ-ወልድ።**